ስምዐ ተዋሕዶ

በአባ ወልደ ትንሣኤ አያልነህ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
አስተምህሮ መሠረት

ወንጌል በአሪት ላይ ስላላት ሥልጣን

እና

ስለ ዶግማና ቀኖና

ድንግል ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
ሎስ አንጀለስ ፤ ካሊፎርኒያ
ጥር 2007 ዓ. ም.

ስምዐ ተዋሕዶ

የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው © 2007 ዓ. ም.

Simea Tewahedo

Copyright © 2015 by Aba Wolde Tensae Ayalneh.
All rights reserved. This book or any portion thereof
may not be reproduced or used in any manner whatsoever
without the express written permission of the author
except for the use of brief quotations in a book review.

Printed in the United States of America

First Printing, 2015

የመጽሐፉ ርዕስ

ይህ መጽሐፍ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊ አስተምህሮ መሠረት በእምነትና በሥርዓት (በዶግማና በቀኖና) ፣ በወንጌልና በአሪት ፣ በሕግና በጸጋ ፣ በጥላና በአካል እንደዚሁም በአምሳልና በአማናዊ መካከል ያለውን ልዩነትና አንድነት ገልጾ የሚያስተምር ስለሆነ ስምዐ ተዋሕዶ ወይም የተዋሕዶ ምስክር ተብሎ ተሰየመ ።

ጥያቄ ካለዎት በሚከተለው አድራሻ ይጻፉልን።

abawtensae@gmail.com

ወይም

Aba Wolde Tensae Ayalneh
Virgin Mary Ethiopian Orthodox Tewahedo Cathedral
4907 S. Main Street, Los Angeles, CA 90037



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ
ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ

ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

መታሰቢያነቱ

በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአጼ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት ምዕራባውያን ሚሲዮኖች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን አሪታዊት እንጂ ወንጌላዊት አይደለችም በማለት ላቀረቡት ክስ ፤ እውነተኛውን የተዋሕዶ አስተምህሮ መሠረት በማድረግ የቤተ ክርስቲያን ምስክርም ጠበቃም ሆነው በቤተ ክርስቲያናችን ላይ የቀረበውን ክስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃ በማቅረብ አሳፍረው ለመለሱት ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ይሁንልኝ ።

ምስጋና

ለተጠራሁበት የወንጌል አገልግሎት በዓለም ዙሪያ ተዘዋውሬ ወገኖቼን እንዳገለግል ሁልጊዜ አስፈላጊውን ድጋፍ ለምትሰጡኝ ፤ እንዲሁም ይህ መጽሐፍ ለሕትመት እንዲበቃ ላገዛችሁኝ ለሎስ አንጀለስ ድንግል ማርያም የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናት እና ምእምናን ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። የእግዚአብሔር አብ ጸጋ ፤ የእግዚአብሔር ወልድ ቸርነት ፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን ። አሜን ።

መክሥተ አርእስት

መቅድም 1
መግቢያ 4

ምዕራፍ አንድ
ዶግማ 5
ምሥጢረ ሥላሴ 5
ትምህርተ ድኅነት (ነገረ ሥጋዌ) 10
የኒቅያ ጉባኤ 15
የቀኖስጥንጥንያ ጉባኤ 16
አንቀጸ ሃይማኖት (የሃይማኖት መግለጫ) 16
ማጠቃለያ 22

ምዕራፍ ሁለት
ቀኖና 23
ቀኖና ለምን አስፈለገ ? 24
የቀኖና ዓላማ 29
የዶግማ ዓላማ 32

ምዕራፍ ሦስት
ወንጌል በአሪት ላይ 43
ባለበት የጸና 48
ፍጹም የሆነ 48
የተሻሻለ 49
የተሻረ 50
ፈጽሞ የተሻረ 52
ቢሻርም በልማድ ወይም በሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን የሚከናወን 55
ማጠቃለያ 65
መደምደሚያ 68
መረጃ 69
ዋቢ መጻሕፍት 105

ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ በተለያዩ ጊዜዎችና ቦታዎች በቀጥታ ከአውደ ምኅረት ላይ የተቀዱ ትምህርቶችን በመውሰድ ለአንባቢያን በሚመች መንገድ በመጽሐፍ መልክ ተዘጋጅቶ የቀረበ ነው ።

መቅድም

ዶግማና ቀኖና የተሰኘውን ትምህርት ማስተማር ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት ብዙዎች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ምዕመናን በዶግማ ፣ በቀኖና እና በባሕል መካከል ያለውን ልዩነት ለይተው እንደማያውቁ ስለተረዳሁና ማሳወቁ እጅግ መልካም ሆኖ ስለተገኘ ነው ። ምክንያቱም እነዚህ ሦስቱ የተደባለቁባቸውና ግራ የተጋቡ ምዕመናን እንዳሉ ስገነዘብ እኔ ራሴ ያለፍኩበት የልጅነት የከርስትና ሕይወቴ ትዝ ይለኛል ።

ዲቁና የተቀበልኩበት ጊዜ እንደ ብዙዎቻችን ሁሉ ገና በልጅነት ነው ። ሃይማኖታዊ ጥያቄውም ወደኔ የጎረፈው በዚያው ወቅት ነው ። ጥያቄ ሲመጣ "ልጅ ነው" ብሎ አይንቅም ። በነበርኩበት ኩተማ የኦርቶዶክስን ሥርዓት የሚቃወሙ የበዙበት ዘመን ነበር ። ለምሳሌ ከገጠሙኝና ግራ አጋብተውኝ ከነበሩ ጥያቄዎች ውስጥ ጥቂቶቹን እዘረዝራለሁ፦

1ኛ) "አሑድን ሰንበት የሚል ቃል በብሉይም በአዲስም ካለ አስረዳን ፤ ሰንበት ቅዳሜ እንጂ አሑድ አይደለም ።"

2ኛ) "ልደትን ፣ ጥምቀትን ፣ ስቅለትን ፣ ትንሣኤንና እርገትን ሌሎችንም ብዛት ያላቸውን በዓላት በየቀናቸው አክብሩ የሚል የት ተገኘ?"

3ኛ) -"በሳምንት ሁለት ቀን ረቡዕ እና ዓርብን ፤ 55 ቀን ዐቢይ ጾምን ፣ በአጠቃላይ ሰባቱን አጽዋማት ጹሙ የሚል በአዲስ ኪዳን የት ይገኛል?"

4ኛ) "ጾም ሲሆን ውላችሁ ፤ ፍስክ ሲሆን በጠዋት ፤ በአምስት ካህናት ከዚያም በላይ ሆናችሁ ቀድሱ የሚል በወንጌል ውስጥ ምን መረጃ ይገኛል?"

5ኛ) "ወንድ ልጅ በ40 ሴት በ 80 ቀን ይጠመቁ የሚል በወንጌል የት ይገኛል?"

6ኛ) "ከርስቲያኖች ሲሞቱ ጸሎተ ፍትሃት አስፈላጊ እንደሆነ ከየት መጣ?"

7ኛ) "በአዲስ ኪዳን የታቦት አገልግሎት ለምን አስፈለገ? ለምንስ የማርያም፣ የሚካኤል፣ የገብርኤል ... ታቦተ ተባለ?"

8ኛ) "የሰው እጅ የቀረጸውን መስቀል ሳሙት ተሳለሙት የሚል መረጃ ካለ?"

9ኛ) "በአዲስ ኪዳን የሥዕል አገልግሎት ፤ ማለትም በሥዕል ፊት ጸልዩ ስገዱ የሚል ማስረጃ ይገኛል?"

10ኛ) "በትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፍ 3 እና ምዕራፍ 66 ውስጥ አጣንን የሚያጥንልኝ ጣዖትን እንደምመለከ ነው ፤ እጣኑም በፊቴ አጸያፊ ነው እያለ

የሰው እጅ የቀረጸውን ትልቅ መስቀል በሁለት እጅህ ይዘህ በቁሱ ፊት ለፊት በመሆን እጣንን እንዴት ታሳጥናለህ?"

11ኛ) "በወንጌል ከተጠቀሱት ከቁስና ከዲያቆን በቀር ፓትርያርክ ፣ ጳጳስ ፣ መነኩሴ የሚል ከየት ተፈጠረ?"

12ኛ) "በቅዱሳን ስም ዝክር መዘከርና በጽዋ ማኅበር ስም እየተሰበሰቡ መብላት መጠጣት ከየት መጣ?"

13ኛ) "በበዓላት ቀን ገበሬው ሲያርስና ልዩ ልዩ ሥራ ሲሠራ ቁሱ የሚያወግዙት ለምንድን ነው?"

14ኛ) "ከብሉይና ከአዲስ ኪዳን ሌላ በድርሳናት በገድላት እና በተዓምራት መጽሐፍት ተጠቀሙ የሚል የት አለ?"

15ኛ) "በስመ ሥላሴ ተጠምቃችሁ ወዲያውኑ በቅዱሳን ስም የክርስትና ስያሜ ለምን አስፈለገ?"

እነዚህን የመሳሰሉ ጥያቄዎች 14 ዓመት ባልሞላ የዕድሜ ክልል ውስጥ ወደ እናንተ ቢጎርፉባችሁ ምን ይሰማችኋል? ከሁሉ ለእኔ ከባድ የነበረው ለምጠየቀው ጥያቄ መልስ ለማግኘት የተለያዩ አባቶችን ስጠይቅ መልሳቸው "አንተ ልጅ ምን ነካህ?" ... "ከእንደነዚህ ዓይነት ሰዎች ጋር ለምን ትገናኛለህ?" ... "ይህ የመናፍቃን ጥያቄ ነው ፤" ... የሚል ነበር ።

አንዳንዶች የማውቃቸው ልጆች ወደ ሌላ እምነት በመሄዳቸው እፈርድ ነበር ። በኋላ ግን ለጥያቄያቸው መልስ አጥተው እንደሆነ ስረዳ ፍርዴ እየቀነሰ ሄደ ።

ወላጅ አባቴ ካህን እንድሆንላቸው እጅግ የሆነ ጉጉት ነበራቸው ። ለኔ ሞራል ለመስጠት ይመስለኛል ማዕድ ሲቀርብ "አንተ ዲያቆን ስለሆንክ ባርክልን" ይሉኛል ። ለተወሰኑ ቀናት እንደ ሙሽራ ማፈር ጀምሬ ነበር ። ቀሰ በቀስ ግን ተለማመድኩትና የወጣለት ማዕድ ባራኪ ሆንሁ ። አባቴ በሌሉ ጊዜ ግን ወላጅ እናቴ እንደመሳቅ እያሉ "በል እስኪ የኛ ቄስ ባርከው" ይሉኛል ። በዚህ ዓይነት የፍቅርና መከባበር ዓለም ውስጥ በመሆኔ ግራ ቢገባኝም እምነቴን ሳልለቅቅ አገልግሎቴን በትዕግሥት ተያያዝሁት ። እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግን የራሱ የሆነ አምላካዊ የማስተማሪያ ጥበብ ስላለው :-

1ኛ) የመልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ መጽሐፍ ማለትም "ኰኵሐ ሃይማኖት" የሚለው መጽሐፍ በእጄ እንዲገባ አደረገ ። ምንም እንኳን የግእዝ ምንባብ ቢበዛበትም ብዙ ጠቀመኝ ። እንዲያውም ግእዝን ለማወቅ ወደ ቅኔ ትምህርት ቤት እንድሄድ መነሻ የሆነኝም ይህ መጽሐፍ ነበር ።

2ኛ) ብጹዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የሚባሉ የሸዋ ሐገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ በዝዋይ የካህናት ማሰልጠኛና ገዳም መስርተው በማስተማር ላይ እንደሚገኙና ጥያቄ ተጠይቀው የማይመልሱት እንደሌለ ሰማሁ ። በደርግ ጊዜ እንኳን ከከፍለ ሃገር ወደ ከፍለ ሃገር፤ ከአንድ ከተማ ወደ ሌላ ከተማ ለመሄድ መታወቂያና የይለፍ ወረቀት ያስፈልግ ስለነበር የይለፍ ወረቀት ለማግኘት ለእኔ እንደ አሜሪካ ቪዛ ከባድ ቢሆንም መንፈስ ቅዱስ አከናወነልኝና ሄድሁ ። ነፍሳቸውን ይማርና ብጹዕ አቡነ ጎርጎርዮስም ተቀበሉኝ ። በኋላም ወደ ማሰልጠኛው ገብቼ እንድማር ፈቀዱልኝ ። አስታውሳለሁ ብጹዕ አባታችን አቡነ ጎርጎርዮስ እኛን የሚያስተምሩበት ከፍለ ጊዜ ደረሰና ወደ ከፍል ገቡ ። ቀይነቱ ያልደመቀ ቀይ የግሪክ ሱፍ ቀሚስ ለብሰዋል ። እንደበረዶ የነጣ ጋቢ በቀሚሱ ላይ ደርበዋል ። ቀኝ እጃቸውን በማውጣት ማስተማር ጀመሩ ። እኔም ለመስማት ከጉጉቴ የተነሳ እንኳን ሁለቱ ጆሮዎቼ መላ አካሌ ሁሉ ጆሮ የሆነ መሰለኝ ። በአርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያናችን የክርስትና ትምህርት ዶግማና ቀኖና ተብሎ በሁለት እንደሚከፈል ነገሩን። በሦስተኛ ደረጃም በዶግማ እና በቀኖና ውስጥ የማይመደብ (የማይካተት) ሃይማኖታዊ የሀገር ልማድ እንዳለ አስረዱን ። ለምሳሌ የወንድ ልጅ ግዝረት ፣ በብሉይ ኪዳን እንዳይበሉ የተከለከሉ እንስሳት እና አዕዋፍ የመሳሰሉትን ማለት ነው ።

እስከዚያ ጊዜ ድረስ ሦስቱም ነገሮች ተደባልቀውብኝ በጨለማ እንደሚጓዝና በመስቀልኛ መንገድ ግራ እንደተጋባ ሰው ስለነበርኩ እንደ ፓውዛ መብራት በአእምሮዬ ውስጥ ብልጭ አለ ። በዓይነ ልቡናዬ ሦስቱም መንገዶች እንደየድርሻቸው ታዩኝ ። የቀኖና እና የባሕል መንገዶች የዶግማ መንገድ እየመሰሉኝ ለዘመናት ስጓዝባቸው ብዙ እንቅፋት ገጥሞኝ ከመጠን በላይ ቆስዬ ነበር። አሁን ግን ዶግማን በዶግማነቱ ፤ ቀኖናንም በቀኖናነቱ ፤ ባሕልንም በባሕልነቱ መጠቀም ስችል ቁስሌ ከመድረቁም በላይ የመዳኔ ቁልፉ በዶግማ መሆኑን ስረዳ አእምሮዬ እረፍት አገኘ ። ለቀኖናና ለባሕልም ምዕራፍ ቁጥር ብዬ መረጃ ለማግኘት መጽሐፍ ቅዱስን ስቆፍር አባቶቼንም መልሱን ውለዱ እያልኩ የኖርኩበትን ዘመን ሳስብ እጅግ ይገርመኛል ። ዛሬም እንደኔ እንደድሮው አእምሮአቸው የሚንገላታ ብዙዎች እንዳሉ ግልጥ ነው ። ለብዙዎች ቀላል መስሎ ቢታይም ለቤተ ክርስቲያናችን ቁልፍ ትምህርት በመሆኑና ምዕመናን እንደ ጠፍ ከብት እየተነዱ ተዘርፈው እንዳያልቁ ይህ ትምህርት አስተዋጽኦ ስለሚያደርግ የዚህ መጽሐፍ አስፈላጊነት አያጠያይቅም ። የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ፍቃዱ ሆኖ በዚህ መጽሐፍ አንባብያን ተጠቃሚ እንዲሆኑ እጋብዛለሁ።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

አባ ወልደ ዮሐንስ አያልነህ

መግቢያ

ዶግማ እና ቀኖና

በጥንታዊቷ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የክርስትና ትምህርት በሁለት ይከፈላል ። ይህንን ሁሉም ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን ማወቅ አለበት ። አንደኛው የዶግማ ትምህርት ፥ ሁለተኛው የቀኖና ትምህርት ነው ። ዶግማ የግሪክ ቃል ነው ። ቀኖና የግእዝም የግሪክም ሊሆን ይችላል ። በግእዝ "ቀነነ ፣ ሕግ ሠራ ፥ ሥርዓት አወጣ" ከሚለው ግሥ ቀኖና የሚል ስም ሲገኝ ፣ በግሪክ «ካኖን» ይላል ። ዶግማ ማለት «እምነት» ማለት ነው ። እነዚህን ሁለቱን ለይቶ የማያውቅ አማኝ ፣ መሪ የሌለው ዓይነ ስውር ማለት ነው ። ወይም መብራት ሳይይዙ በጨለማ መጓዝ እንደ ማለት ነው ። እነዚህን ነገሮች እንደ አንድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታይ ለይተን ካላወቅን ምንም እንኳን አዘውትረን በቤተ ክርስቲያን ብንሰባሰብ ፣ ምንም እንኳ የጥሩ ባሕል ፣ የታሪክ እና የመልካም ወግ ባለቤቶች ብንሆንም ፣ ሳናስበው በድቡሽት ላይ የተሠራ ቤት ነው የምንሆነው ።

በማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 7 ከቁጥር 24 እስከ 72 እንደተጻፈው « ስለዚህ ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል ። ዝናብም ወረደ ጎርፍም መጣ ነፋስም ነፈሰ ያንንም ቤት ገፋው ፥ በዓለት ላይም ስለ ተመሠረተ አልወደቀም ። ይህንም ቃሌን ሰምቶ የማያደርገው ሰው ሁሉ ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራ ሰነፍ ሰውን ይመስላል ። ዝናብም ወረደ ጐርፍም መጣ ነፋስም ነፈሰ ያንም ቤት መታው ፥ ወደቀም ፥ አወዳደቁም ታላቅ ሆነ» ።

ስለዚህ የዶግማንና የቀኖናን ትምህርት ለይተን ሳናውቅ ለቤተ ክርስቲያናችን የምናቀርበው አገልግሎትና በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ መሰባሰባችን ብቻውን በቂ አይደለም። በድቡሽት ላይ እንደተሠራው ቤት ዕድሜ ሊኖረው አይችልም ። ወንጌል የማንኛውም ነገር መሠረት ነው። በወንጌል ያልተመሠረተ ክርስቲያናዊ ሕይወት በምድርም በሰማይም ዋጋ የለውም ። አገልግሎታችን መሠረት ሊኖረው የሚችለውና በዓለት ላይ የተመሠረተውን ቤት መስለን የምንጓዘው በቃለ እግዚአብሔር የታነጽን ከሆነ ብቻ ነው። በተለይም እነዚህን ሁለት የክርስትና ትምህርት ክፍሎች አጥብቀን ማወቅና ልዩነታቸውን መገንዘብ አስፈላጊ ነው።

ምዕራፍ አንድ

ዶግማ

ዶግማ ማለት እምነት ፣ ቀኖና ማለት ደግሞ ሥርዓት ማለት እንደሆነ ከላይ ተጠቅሷል ። ዶግማን ያገኘነው ከራሱ ከእግዚአብሔር ነው ። ዶግማ ማለት ነገረ እግዚአብሔር ማለት ነው ። ዶግማ እግዚአብሔርን ማመንና ከቃሉ የወጣ የእርሱ ትምህርት ስለሆነ ሊሻሻል አይችልም ። በመሆኑም ቅዱስ ሲኖዶስም ሆነ ሊቀ ጳጳስ ፣ ወይንም የሊቃውንት ጉባኤ ዶግማን ሊቀንስም ሊጨምርም አይችልም ፤ እስከ ሞት ድረስ የሚጠበቅ ነው ።

ዶግማ ማለት ከላይ እንዳየነው እምነት ማለት ነው ። እምነት ደግሞ ሰማይና ምድርን ፥ የሚታየውንና የማይታየውን ፍጥረት ሁሉ የፈጠረ እግዚአብሔርን አምኖ መቀበል ማለት ነው ። ይህን የሚታየውንና የማይታየውን ዓለም ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ የፈጠረ አምላክ እግዚአብሔር ነው ። በትምህርተ እግዚአብሔር (ዶግማ) ውስጥ ደግሞ ዋናው ትምህርት ምሥጢረ ሥላሴ እና ምሥጢረ ሥጋዌ ስለሆኑ በአጭሩ እንደሚከተለው እናብራራለን ።

ምሥጢረ ሥላሴ

ሰማይንና ምድርን የፈጠረ አንዱ እግዚአብሔር እኛን ሲፈጥር «ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ - ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር» (ዘፍ. ፩፥26) ነው ያለው ። ስለዚህ በዚህ ጥቅስ ላይ እግዚአብሔር በአካል ከአንድ በላይ መሆኑን ያሳያል ። ሁለት ይሁን ፥ ሦስት ፥ አራት አይታወቅም ነበር ። ቡቡይ ኪዳን ትምህርተ ሥላሴ ቢገለጥም ሦስትነቱ በማያሻማ ሁኔታ የተገለጠው ጌታ ስለ እኛ በተጠመቀበት ሁላችንም በምናስታውሳት በዚያች ቅድስት ዕለት በዮርዳኖስ የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት ገደማ ነው ። ከዚያም በፊት በጽንሰቱ፣ በኋላም በትምህርቱ መድኃኒታችን የአንድነቱን እና የሦስትነቱን ነገር አስተምሮናል ። ከዚያ በፊት ከአንድ በላይ ነው ፣ ግን ብዛቱ አይታወቅም ። ሆኖም ግን «ንግበር - እንፍጠር [እንሥራ] አለ» የሚለውን ስናይ ማሠሪያ አንቀጹ «አለ» አንድ ነው ። "ንግበር በአርአያነ ወበአምሳሊነ - በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር" ሲል ግን ከአንድ በላይ ነው ። አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይከበር ይመስገንና እኛ መጠመቅ እንደሚገባን ለማሳየት ለአርአያነት በእደ ዮሐንስ በፈለገ ዮርዳኖስ በተጠመቀ ጊዜ ፣ ያን ጊዜ ሦስትነቱ ተገልጦአል ።

ስለዚህ ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱስ ወንጌሉ እንዳስተማረን ፥ አባቶቻችንም መንፈስ ቅዱስ ገልጾላቸው ብልዩ ልዩ ምሳሌ እንዳስረዱን ፤ ያ አንዱ እግዚአብሔር ፤ አምላክ ፈጣሪ የሚለው የአንድነት ስሙ ሆኖ ነገር ግን ያ አንዱ ፈጣሪ አንዱ አምላክ ፤ ያ አንዱ እግዚአብሔር <u>በስም</u> ፤ <u>በአካል</u> ፤ <u>በግብር</u> ሦስት እንደ ሆነ ተገለጠ ። ያ አንዱ እግዚአብሔር የስም የአካል የግብር ሦስትነት እንዳለው በጌታ ጥምቀት ዕለት ነው ያወቅነው ። (ማቴ. 3፥16-12)

<u>የስም ሦስትነቱ</u> አብ ፥ ወልድ ፥ መንፈስ ቅዱስ ነው ።

<u>የአካል ሦስትነቱ</u> አብ የራሱ አካል አለው ፤ ግን የአብን አካል ይህን ይመስላል ፤ ይህን ያክላል ብለን ልንናገር ፥ ልንዳስሰው ፥ ልንጨብጠው አንችልም ። የሚወሰንም አይደለም ፤ ከአእምሮአችን በላይ ነው ።

የወልድም እንደዚሁ ከኛ ሥጋ ጋር ከመዋሐዱ በፊት የራሱ አካል አለው ፤ ግን ይህን ያክላል ብለን መወሰን አንችልም ። ምልዓቱም በሁሉም ቦታ ነው ። አይዳሰስም ፥ አይጨበጥም ። ከሰውም አእምሮ ከመላእክትም በላይ ምጡቅ ነው ፤ ግን አካል አለው ።

መንፈስ ቅዱስም የራሱ አካል አለው ። ይህን ያክላል ብሎ ለመናገር አይቻልም ፥ ከኛ አእምሮ በላይ ነው ፤ አይዳሰስም ፥ አይጨበጥም ። እንኳን መንፈስ ቅዱስ ፤ ቅዱሳን መላእክትም አይዳሰሱም አይጨበጡምም ። እንደዚሁ ሁሉ የኛም ነፍስ አትዳሰስም አትጨበጥም ። ሃይማኖትም ያስፈለገው ይህንን ረቂቁን የማይታየውን እንደሚያዩት አድርጎ ማመን የሚቻለው በእምነት ብቻ ስለሆነ ነው ። ስለዚህ አብ የራሱ አካል አለው ፤ ይህን ያክላል ፤ ይህን ይመስላል ማለት ግን አንችልም ። ወልድም መንፈስ ቅዱስም እንደዚሁ ።

<u>የግብር ሦስትነቱ</u> አብ ወላዲ ፥ አሥራጺ ይባላል ። ወልድ ተወላዲ ይባላል ፤ መንፈስ ቅዱስ ሠራጺ ይባላል ። የአብ ግብሩ ወላዲ ፥ አሥራጺ ነው ። ወላዲ ማለት ወላጅ አባት ማለት ነው ። አሥራጺ ማለት አስገኝ ማለት ነው ። ስለዚህ አብ ወልድን ወለደ ፤ መንፈስ ቅዱስን አሠረፀ ፥ አስገኘ ።

የወልድ ግብሩ ተወላዲ ነው ። ተወላዲ ማለት የሚወለድ ማለት ነው ። ስለዚህ ወልድ ልጅ ነው ።

የመንፈስ ቅዱስ ግብሩ መሥረጽ ነው ። በመሆኑም መንፈስ ቅዱስ ሠራጺ ይባላል ። የአብ ስም ፥ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ መጠሪያ አይሆንም ። የወልድም ስም ለአብ ፥ ለመንፈስ ቅዱስ መጠሪያ አይሆንም ። የመንፈስ ቅዱስም ስም ለአብ ፥ ለወልድ መጠሪያ አይሆንም ፤ ስማቸው አይፋለስም ።

አብ ፤ አብ እንጂ ወልድ ፥ መንፈስ ቅዱስ አይባልም ። ወልድም ወልድ እንጂ ፤ አብ ፥ መንፈስ ቅዱስ አይባልም ። መንፈስ ቅዱስም እንዲሁ መንፈስ ቅዱስ እንጂ ፤ አብ ፥ ወልድ አይባልም ።

ይህን አንዱን እግዚአብሔር ፤ በስም በአካል በግብር ሦስት አልነው ። ነገር ግን ምንም እንኳ በስም በአካል በግብር ሦስት ቢሆኑም ፤ በመለኮት ፥ በመፍጠር ፥ በጌትነት ፥ በእግዚአብሔርነት ፤ አንድ ነው ። "ለምንድነው አንድ የሆነው?" ቢባል ፦ አብን ፈጣሪ እንለዋለን ። ወልድንም ፈጣሪ እንለዋለን ፤ መንፈስ ቅዱስንም ፈጣሪ እንለዋለን ። ስለዚህ አብ ፈጣሪ ከሆነ ፤ ወልድ ፈጣሪ ከሆነ መንፈስ ቅዱስ ፈጣሪ ከሆነ ፤ ለምንድነው ሦስት ፈጣሪዎች ያላልነው ? አብ እግዚአብሔር ከሆነ ፤ ወልድም እግዚአብሔር ከሆነ ፤ መንፈስ ቅዱስም እግዚአብሔር ከሆነ ፤ ለምንድነው ሦስት እግዚአብሔር የማንለው ? ይህንን ለማለት የማንችልበት ምክንያት አብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ፤ ወልድም በአብና በመንፈስ ቅዱስ ፤ መንፈስ ቅዱስም በአብና በወልድ በከዊን ጎልዋን ስለሆነና በኩነት ስለሚገናዘቡ በመለኮትም አንድ ስለሆኑ ነው ። ይህም ማለት በቀላል አባባል አንዱ አንዱን አልቦ ሥራ ስለማይሠራ ነው ። አንዱ አካል ከሁለቱ አካላት ፤ ሁለቱ አካላት ከአንዱ አካል ተለይተው ሥራን አይሠሩም ። ልዩ ሦስትነት ያለው እግዚአብሔር ሥራን ሲሠራ በአንዲት መላኮታዊ ከሂል ስለሆነ ነው ።

አባቶቻችን በቀላል ምሳሌ አስረድተውናል ። መቼም የምንመስለው ምሳሌ ሁሉ ለሥላሴ በቂ መግለጫ ይሆናል ማለት አይደለም ። ግን የግድ ለመግቢያ ፥ ለመንደርደሪያ ያህል ምሳሌ ያስፈልጋል ። አሱም ምሳሌ ዘየሐጽጽ ይባላል ። ጎዶሎ-ምሳሌ ማለት ነው ። እንኳን ለሥላሴ ፤ ለወላዲተ አምላክ ለድንግል ማርያም ምሳሌ አናገኝም ። ሆኖም ግን አባቶቻችን መንፈስ ቅዱስ በገለጸላቸው መሠረት አእምሮአችን የሚረዳውን ያህል ፤ ለመግቢያ ለመንደርደርያ ፍንጭ ሰጥተው ሄደዋል ። ያም ምንድን ነው ፤ የአብ ምሳሌ ልብ ነው ፤ የወልድ ምሳሌ ቃል ነው ፤ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ እስትንፋስ ነው ። በእያንዳንዳችን ሕይወት ውስጥ ልብ አለ ፤ እስትንፋስ አለ ፤ ቃል አለ ። ልብ የሚሉት አባቶቻችን በአሁኑ አነጋገር አእምሮ የምንለው ነው ። "እገሌ ልብ አለው ፤ እንዴት ያስተውላል?" ይባላል ። አስተዋይ አእምሮ አለው ማለት ነው ። ስለዚህ የአብ ከዊን ልብነት ፤ የወልድ ከዊን ቃልነት ፤ የመንፈስ ቅዱስም ከዊን እስትንፋስነት ሕይወትነት ነው ።

አንድ ሰው ሙሉ ሰው ነው ፤ ጤነኛ ነው ከተባለ ፤ ልብ ፥ ቃል ፥ እስትንፋስ ሊኖረው ይገባል ። ነገር ግን ልብ ፥ ቃል ፥ እስትንፋስ ያለው ሰው አንድ እንጂ ሦስት ሰዎች አይባልም ። አባቶቻችን ይህን ቀላል ምሳሌ ሰጥተውናል ።

እግዚአብሔር አብ ይህን የሚታየውንና የማይታየውን ዓለም ፈጣሪ ነው ። ነገር ግን "እንዴት አድርጎ ፈጠረው?" የሚል ጥያቄ ቢነሣ መልሱ "በራሱ ልብነት

አስቦ ፤ በመንፈስ ቅዱስ ሕይወትነት ሕያው ሆኖ ፤ በወልድ ቃልነት ተናግሮ ይህን ዓለም ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ ፈጠረ" የሚል ይሆናል ።

እግዚአብሔር ወልድም የሚታየውንና የማይታየውን ዓለም ፈጣሪ ነው ። እሱም እንዴት አድርጎ ፈጠረ ? ቢባል መልሱ በአብ ልብነት አስቦ ፤ በመንፈስ ቅዱስ ሕይወትነት ሕያው ሆኖ ፤ በራሱ ቃልነት ተናግሮ ይህን ዓለም ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ ፈጠረ የሚል ይሆናል ።

እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም የሚታየውንና የማይታየውን ዓለም ፈጣሪ ነው ። እሱም እንዴት አድርጎ ፈጠረው ? የሚል ጥያቄ ቢነሣ መልሱ በአብ ልብነት አስቦ ፤ በራሱ ሕያውነት ሕያው ሆኖ ፤ በወልድ ቃልነት ተናግሮ ይህን ዓለም ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ ፈጠረ ማለት ይሆናል ።

ስለዚህ አብ ለራሱ ፤ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ ልብ ነው ። ወልድም ለራሱ ፤ ለአብና ለመንፈስ ቅዱስ ቃል ነው ። መንፈስ ቅዱስም ለራሱ ፤ ለአብና ለወልድ የሕይወት እስትንፋስ ነው ።

በዚህም ምክንያት አንዱ አንዱን ወይም ሁለቱን አልቦ ሥራን አይሠራም ። ይህም ማለት አብ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ ተለይቶ ፤ ወልድም ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ተነጥሎ ፤ መንፈስ ቅዱስም ከአብና ከወልድ ተለይቶ ሥራን ስለማይሠራ ፤ እግዚአብሔር በሰም ፥ በአካል ፥ በግብር ሦስት ። በባሕርይ ፥ በሕልውና ፥ በአገዛዝ ፥ በመለኮት አንድ ነው ብለን እናምናለን ። ዶግማ ማለት ይህ ነው ።

አንዳንድ ሰዎች እንዴት እግዚአብሔር አንድ ሲሆን ሦስት ፤ ሦስት ሲሆን አንድ ሊሆን ይችላል ? የሚል ጥያቄ ያነሣሉ ። ነገር ግን እግዚአብሔር በእምነት እንጂ ፥ በሰው ጥበብ ተሰፍሮ ተቆጥሮ የሚገኝ አይደለም ። ስለሆነም የእግዚአብሔርን አንድነት ሦስትነት በእምነት ልንቀበለው ይገባል። ሐዋርያው እንዳለው «እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ ፥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው» (ዕብ ፲፩ ፥ ፩-40) ።

እንግዲህ ከላይ እንደተጠቀሰው እግዚአብሔር «ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ - ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር" አለ ሲባል ፤ እግዚአብሔር እንደ እኛ ቀጭን ወይም ወፍራም ወይም ቀይ ወይም ጥቁር ነው ለማለት አይደለም ። እግዚአብሔር ረቂቅ ስለሆነ አይዳሰስም አይጨበጥም ። በአርግጥ ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል ወልድ በተለየ አካሉ ፍጹም ሰው በሆነ ጊዜ በሰውነቱ ተዳስሶአል ፤ ስሙም ኢየሱስ ተብሎ ተጠርቶአል ። ሰው ከመሆኑ በፊት ግን የሚዳሰስ የሚጨበጥ አልነበረም ። እንዲህ ከሆነ ለምንድነው ሰው በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል ተፈጠረ የተባለው ?

እግዚአብሔር ቅዱስ ነው ። ቅድስናውም የባሕርዩ ነው ። ሰውም መጀመርያ የተፈጠረው ቅዱስ ሆኖ ነው ። በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠር ማለት ያ ነው ። እግዚአብሔር ሕያው ነው ። እኛም በነፍስ ሕያዋን ነን ። እግዚአብሔር ልዩ ነው ። እኛም ልዩ ሆነን ነው የተፈጠርነው ። እግዚአብሔር ባለሥልጣን ነው ። እኛም በጸጋ ባለሥልጣኖች ነን ። እግዚአብሔር ገዥ ነው ። እኛም በጸጋ የፍጥረት ገዢዎች ነን ። እግዚአብሔር ንጹሕ ነው ። እኛንም በንጽሕና ፈጥሮናል ። ስለዚህ ሰው በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል በመፈጠሩ ነው ቅዱስ ፥ ንጹሕ ፥ ሕያው ፥ ልዩ ፥ ባለሥልጣንና ገዥ ነው የሚባለው ። እግዚአብሔር የሚወደውን ሥራ መሥራት እግዚአብሔርን መምሰል ነው ። እግዚአብሔር አባታችን ነውና አባት የሚሠራውን እኛ ልጆቹ እንድንሠራ ይጠበቅናል።

ከላይ እንደተገለጸው አብ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን አልቦ ብቻውን አይኖርም ፤ አይሠራም ። ወልድም ለብንና መንፈስ ቅዱስን አልቦ ብቻውን አይኖርም ፤ አይሠራም ። መንፈስ ቅዱስም አብንና ወልድን አልቦ ብቻውን አይኖርም ፤ አይሠራም ። ሦስቱም አንዱ ለአንዱ ምስክር ነው ። ለምሳሌ ወልድ በዮርዳኖስ ሲጠመቅ አብ «በእርሱ ደስ የሚለኝ ፤ የምወደው ልጄ ይህ ነው» ብሎ መስክሯል ። (ማቴ. ፫፥16 ። ማር. ፩፥10 ። ሉቃ. 3፥22) ። ይህ ምስክርነት በደብረ ታቦርም ተደግሟል (ማቴ ፲፯ ፥ 5) ። ወልድም ስለ አብ መስክሯል ። መንፈስ ቅዱስም ስለ አብና ስለ ወልድ ይመሰክራል ። እንኳን ስለ አብና ስለ ወልድ ስለ እኛም ይመሰክራል ። የእግዚአብሔር ልጅ ጌታችን ኢየሱስ ከርስቶስ በሥጋ ማርያም ካረገ ጀምሮ ስለ ወልድ አዳኝነት ፤ ስለ አብም አባትነት የሚመሰክረው መንፈስ ቅዱስ ነው ።

በመሆኑም አብ ወልድን ፤ መንፈስ ቅዱስን ይወድዳል ፤ ወልድም አብን መንፈስ ቅዱስን ይወድዳል ፤ መንፈስ ቅዱስም አብንና ወልድን ይወድዳል ። ከዚህም የተነሣ በመጽሐፍ ቅዱስ «እግዚአብሔር ፍቅር ነው» ተብሏል ። (፩ዮሐ 4፥16) ።

እንግዲህ በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል መፈጠር ማለት አንዱ አንዱን አልቦ ወይም አንዱ ያለ ሌላው ለመኖር አለመፈለግ ማለት ነው ። በተለይ ከርስትና ማለት አንዱ አንዱን አልቦ ለመኖር አለመፈለግ ማለት ነው ። እንኳን የፍቅር ባለቤት በሆነው በከርስቶስ የሚያምነው ቀርቶ ፤ እግዚአብሔር የፈጠረው የዓለም ሕዝብ ሁሉ ወገናችን ነው ። የከርስቶስ ወንጌል "የሚጠሏችሁን ውደዱ የሚረግሟችሁን መርቁ" የሚለን ፥ በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል የተፈጠረውን ሰው ሁሉ እንድንወድና እንድናከብር ነው። (ማቴ 5 ፥ 40-45)

የእግዚአብሔር ልጆች የሚታወቁት በፍቅራቸው ፥ በርኅራኄያቸውና እርስ በእርስ በመደጋገፋቸው ፤ በመዋደዳቸው ነው ።። (ዮሐ 15 ፥ 12) ።

ስለዚህ እውነተኞች ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥረናል ብለው የሚያምኑ ከሆነ ፤ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንዱ አንዱን አልቦ እንደማይሠራ ፤ እንደማይኖር ሁሉ ፤ እነርሱም አንዱ ሌላውን አልቦ መኖሩ ትርጉም ስለሌለው በመፈቃቀርና በመደጋገፍ ሊኖሩ ይገባል ። በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠር ማለት እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ እርስ በእርስ ተፋቅሮ ፤ ተረዳድቶና ተደጋግፎ መኖር ማለት ነው ።

ትምህርተ ድኅነት (ነገረ ሥጋዌ)

እንደሚታውቀው በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥረን በገነት ተከብረን ስንኖር አጠፋን ኃጢአት ሠራን ፥ ወደቅን ፥ ሞት ተፈረደብን ። ከዚህም ሞት የሚያድነን ማንም አልነበረም ። የሰማይ መላእክት ሊያድኑን አልቻሉም ። ነቢያት ሊያድኑን አልቻሉም ። ቅዱሳንም ሊያድኑን አልቻሉም ፤ ራሳቸውን ሊያድኑ አይችሉምና ።

ነገር ግን እግዚአብሔር ዓለምን ለማዳን በነበረው እቅድ አንድያ ልጁን ላከልን ። መቼም መታዘዝ ያለበት ልጅ ነው ። የወልድ ግብሩ ተወላዲ ነው ። ምንም እንኳ በዘመን ባይቀዳደሙ ፤ በሥልጣን ባይበላለጡም ፤ አብ አባት ነው ወልድ ልጅ ነው ፤ መንፈስ ቅዱስ ሠራጺ ወይም ሕይወት ነው ። ስለዚህ አብና መንፈስ ቅዱስ ባያስገድዱትም ወልድ እኛን ስለወደደን በአብ ፤ በመንፈስ ቅዱስና በራሱም ፈቃድ ፍጹም ሰው ሆነ ። ሰው የሆነው አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፤ ሰማይና ምድር የማይችሉት አርሱ በቅዱስ ገብርኤል አብሣሪነት ተፀንሶ ከእመቤታችን ተወለደ ። እንደሚታወቀው ሁሉ ቅዱስ ገብርኤል እመቤታችንን «ተፈሥሒ ፍሥሕት አ ምልዕተ ጸጋ - ጸጋን የተሞላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ" ባላት ጊዜ ፤ «ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ - እንደ ቃልህ ይሁንልኝ" ባለች ጊዜ አካላዊ ቃል ፤ የማይታየው ፥ የማይጨበጠው ፥ የማይወሰነው እግዚአብሔር ወልድ በተለየ አካሉ በግብረ መንፈስ ቅዱስ ከቅድስት ማርያም ፍጹም ሰው ሆነ። በቤተ ልሔም ተወለደ ። ቀስ በቀስም አደገ ። ስለ እኛ ተጠመቀ ፤ ጾመ ፥ ሁለተኛ አዳም ሆኖአልና ፈተናን ሁሉ ተፈተነ ፥ አሸነፈ ። ተዘዋውሮ አስተማረ ። ምልክቶችንና ድንቅ ተአምራትንና መንክራትን አደረገ ። ቤተ ክርስቲያን በሐዲስ ኪዳን ማድረግ የሚገባትን አርአያ ሆኖ ሠርቶ አሳየ ። በመጨረሻም ስለ እኛ ኃጢአት በቀራንዮ ተሠዋ ። በዚህ ጊዜ የጥሉ ግድግዳ ፈረሰ ። «በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳን በሥጋው ያፈረሰ» ተብሎ እንደ

ተጻፈ (ኤፌ 2 ፥ 15)። የአዳ ደብዳቤአችንንም ደመሰሰው ። «በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትእዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰው» እንዲል (ቈላ 2 ፥ 14)።

የጥንተ ጠላታችንን የዲያብሎስንም ሥራ ኃጢአትን አፈረሰው ። «ስለዚህ የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ» እንዲል (1ዮሐ 3 ፥ 8) ። ተዘግታ የነበረች ገነት ተከፈተች ። ሕይወትን አገኘን ። ከእግዚአብሔር ጋር ታረቅን ። ጠላቶቹ ስንሆን በልጁ ሞት ይቅር አለን ፤ እንደገናም ልጆቹ ለመሆን አበቃን።

እርሱ እኛ የምንሞተውን ሞት ሞተልን ። አሁን እርሱ እንደ ሞተ እንሞታለን ፤ እርሱ እንደተነሣ እንነሣለን። በክብር ዐረገ ፥ በአባቱ ቀኝ ተቀምጦአል ፤ ምልዐተ መለኮቱ በሁሉ ቦታ ሆኗል ፤ አሁንም ከእኛ ጋር ነው ።

ያ ድንቅ ጌታ እንደገና በክብር ፥ በግርማ መለኮት ይመጣል ። ዓለማት ያልፋሉ ፤ ዛሬ የምናያቸው ኃያላን አይኖሩም ። ሙታን ይነሣሉ ። የሚሳነው ነገር ስለሌለ ሁላችን በፊቱ እንቆማለን ። ሁላችን አንድ ቀን እንነሣለን ። እርሱ ለትንሣኤያችን በኩር ሆኗልና ። እኛ ደግሞ ሰዓታችን ሲደርስ እርሱ ሲመጣ እንነሣለን ። ዛሬ የምንኖረው በትንሣኤ ተስፋ ነው ። በምድር ተስፋ ብቻ አይደለም የምንኖረው። ምድርማ ጊዜያዊ መኖሪያችን ናት ። ሌላ ተስፋ አለን ፤ ሌላ ሕይወት አለን ፤ ሌላ ሀገር አለን። ያንን ግን የምናገኘው በእምነት ነው ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኛ ሰው እንደሆነ እናምናለን ። ስለ እኛ መከራን እንደተቀበለ እንደሞተ ፤ የእኛን እዳ በደሙ ፥ በሞቱ እንደከፈለ ፤ በእርሱ ሞት ልጆቹ እንዳደረገን ፤ በእርሱ ሞት ሕይወትን እንዳገኘን ፤ እርሱ እንደተነሣ እንደምንነሣ ፤ እርሱ ሕያው እንደሆነ ለዘላለም ሕያዋን ሆነን እንደምንኖር ስናምን እንደዚሁም በእግዚአብሔር ቃል እየተጽናናን ስንኖር ፤ ይህንን እምነት ጠብቀን ሕይወታችንን በሞተ ሥጋ ሲደመደም ፤ የዘላለም ሕይወት አለን ። ስለዚህ መዳን በእምነት ነው ። "መዳንም በሌላ በማንም የለም ፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና" ተብሎ ተጽፏል (የሐዋ 4 ፥ 12) ።

ከዲያብሎስ ባርነት ነጻ መውጣት በሌላ በማንም የለም። ትንሣኤ ሙታን በሌላ በማንም የለም። በላይ በሰማይ በታች በምድር መዳን በአንድ ብቻ ነው ፤ እሱም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ነው ። አባቶቻችን ያስረከቡን ያወረሱን ሀብት ይሄ ነው ። የዘላለም ሕይወት ተስፋችን ይሄ ነው ።

እንደዚሁም እኛ አርቶዶክሳዊያን እመቤታችንን ድንግል ማርያምን «አማዝትነ ወመድኃኒትነ - እመቤታችን እና መድኃኒታችን" በትክክል እንላለን ፤

ቅዱሳን መላእክቱንም አዳኞቻችን እንላቸዋለን ። እንኳን ቅዱሳን መላእክቱን ፣ መሳፍንትን አዳኞች ፣ ታዳጊዎች እንዳሏቸው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል (መሳ 3 ፥ 7-16 ፡ 31) ።

በተጨማሪም ጻድቃኑን ፣ ነቢያቱን ፥ ቅዱሳኑን ፥ አዳኞች እንላቸዋለን ። እንኳንና ቅዱሳኑ ስለ ስሙ ሲመሰክሩ ሕይወታቸውን የሰጡት የመንፈስ አርበኞች ይቅሩና እኔም በወንጌል አዳኝ ተብያለው ። እኔ ምእመናንን እንዳድን ፣ ምዕመናንም እኔን እንድታድኑ ታዝዟል። (የይሁዳ መልእክት ቁጥር 22) ።

ከዚህ አንጻር አመቤታችንን አማዝአትነ መድኃኒትነ እንላታለን ። መላእክትንም አዳኞች እንላቸዋለን ። የአምላካችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት ከአመቤታችን መድኃኒትነት እንደዚሁም ከመላእክትና ከቅዱሳን አዳኝነት ጋር ልዩነቱ ምንድነው ? ልዩነቱን ያወቅን እንደሆነ መልስ ለመስጠት ችግር የለውም ። ለአለምሮአችንም መልካም ነው ። ነገር ግን ልዩነቱን ካላወቅን ግን ለሚጠይቁን እንደተደናገጥንና ፣ ሁልጊዜ ግራ እንደተጋባን ነው የምንኖረው ።

እስኪ ጥያቄውን ከወንጌሉ አንጻር በማስተዋል እንየው ። በእግዚአብሔርና በእኛ መካከል የነበረውን የጥል ግድግዳ የሚያፈርስ አልነበረም። ከዲያብሎስ ባርነት ነጻ የሚያወጣን ፣ የዲያብሎስን ራስ የሚቀጠቅጥ ማንም አልነበረም። ከሞት የሚያድን ፣ ትንሣኤ ሙታን የሚሆን ሌላ ማንም አልነበረም ። ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው የሚለን ። ታዲያ እንደዚያ ከሆነ በላይ በሰማይ ፣ በታች በምድር መዳን በሌላ በማንም የለም ፣ መዳን በእሱ ብቻ ነው የሚለውን የወንጌሉን ቃል ፣ ዶግማውን አባቶቻችን በብራና ጽፈው ካስረከቡን ለምንድነው እመቤታችንን አዳኛችን ያልነው? ሌላ አዳኝ የለም ከተባለ ለምንድነው መላእክትን አዳኞች ያልናቸው ። ለምንድነው ነቢያትን ፥ ሐዋርያትን ፥ ጻድቃንን ፥ ሰማዕታትን ፥ ቅዱሳንን ሁሉ አዳኞች ያልናቸው ?

ለአእምሮዬ ጥሩ መስሎ የታየኝን አንድ ቀላል ምሳሌ ልጠቀም። ዶክተር አበበ በሽታዬን መርምሮ አገኘ ፣ መድኃኒት ሰጠኝ ፣ እኔ መድኃኒቱን ወሰድኩ ዳንኩ ። "ዶክተር አበበ አድኖኛል ፤ ዶክተር አበበ ባይደርስልኝ ኖሮ ሞቼ ነበር" እላለሁ ። ይሄ የአነጋገር ፈሊጥ ነው ። "ዶክተር አበበ ባይደርስልኝ ኖሮ ሞቼ ነበር ፣ አዳነኝ" ስል ግን "ጀርሙን የገደለው መድኃኒቱ ነው ? ወይስ ዶክተር አበበ ነው ?" የሚል ጥያቄ ቢነሣ መልሱ እንደሚከተለው ነው ።

ጀርሙን የገደለው መድኃኒቱ ነው ። ግን በተለምዶ አነጋገር ዶክተር አበበ አዳነኝ አላለሁ ፤ ትክክልም ነው ። ምክንያቱ ዶክተር አበበ በተሰጠው ጸጋና ስጦታ ከመድኃኒቱ ጋር ባያገናኘኝ ኖሮ መሞቴ አይቀርም ነበርና ። ማንም ተነሥቶ ያለሞያው ሐኪም ነኝ ብሎ መድኃኒት ቢያዝልኝ ፥ እንኳንስ ሊያድነኝ

እንዲያውም ሞቴን ያፋጥነው ይሆናል ። ስለዚህ ወላዲተ አምላክን «አግዝእትነ ወመድኃኒትነ» ፣ የምንላት መድኃኒቱን ወልዳ ስለሰጠችን ነው ። እሷ መድኃኒት ባትሰጠን ፣ ክርስቶስ ከእርሷ ባይወለድ ኖሮ መዳን እንችላለን ? በፍጹም አንችልም ። እንግዲህ ለመዳናችን ዋና ምክንያት እሷ ናት የምንለው ይህን መሠረት አድርገን ነው ።

መላእክቱንም አዳኞች የምንላቸው ወንጌሉ እንደሚናገረው እኛን ከከፋት ወደ ደግነት እንድንመለስ ፣ እንድናስተውል ፣ ነቢያትን ሐዋርያትን በማገዝ ወንጌሉን እንድንማር ስለረዱን ሲሆን ፣ በአጠቃላይ ክርስቶስን አምነን መድኃኒቱን አግኝተን እንድንድን መላእክት ያደረጉትን አስተዋጽኦ ፣ ዛሬም የሚያደርጉትን መሠረት በማድረግ ነው ።

በቤተ ክርስቲያን ሐዋርያትን የረዱአቸው ፣ ትልቁን ወንጌል የሰበኩት መላእክት ናቸው ። መጀመሪያውንም ብሥራቱን የነገሩን መላእክት ናቸው ። ሲወለድም ደስታውን የነገሩን ፣ ትንሣኤውንም ያበሠሩን መላእክት ናቸው ። በዕርገቱም ጊዜ ያጽናኑን መላእክት ናቸው ። ዳግም ሲመጣም ቀድመው የሚመጡት እነርሱ ናቸው ። ስለዚህ በመዳን ውስጥ ትልቅ ተሳትፎ አላቸው ። ምክንያቱም ቅዱሳን መላእክት በተሰጣቸው ጸጋ ወደ መድኃኒቱ አድርሰውናልና ።

ነቢያት በትንቢት ፣ ሐዋርያት በትምህርት ፣ ሰማዕታት በምስክርነት ፣ ጻድቃን በጸሎትና በቃል ኪዳናቸው ፣ ሁሉም የእግዚአብሔር ቅዱሳን የመንፈስ ቅዱስ ሐኪሞች ናቸው ። ተሹመዋልና በተሰጣቸው ጸጋ ያድናሉ ። አንድ ሐኪም ዝም ብሎ አይደለም ዶክተር የሚባለው ፤ ብዙ ጥሮ ፥ ብዙ ደክሞ ፥ ብዙ ወጥቶ ወርዶ ባገኘው እውቀት ነው ። ማንም ተነሥቶ ዶክተር ሊሆን አይችልም ። ማንም ተነሥቶ ነቢይ ሊሆን አይችልም ። ማንም ተነሥቶ ሰማዕት ሊሆን አይችልም ። ስለዚህ እነዚህ መንፈስ ቅዱስ ያከበራቸው ፣ እውቀቱን ጸጋውን ያበዛላቸው የመንፈስ ቅዱስ የቤተ ክርስቲያን ዶክተሮች በማስተማራቸው የኃጢአት በሽታን እየመረመሩ ፣ በጸሎታቸው ፥ በቃል ኪዳናቸው ፥ እግዚአብሔር በሚያሳያቸው ነገር ሁሉ የኃጢአት በሽታን እየመረመሩ ከመድኃኒቱ ያደርሱናል ። መድኃኒቱ ግን በሰማይም በምድርም አንድ ብቻ ነው ፣ እሱም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ።

ስለዚህ እነሱን አዳኞች የምንላቸው ከመድኃኒቱ ጋር ስላገናኙን ነው ። እስኪ ማነው በቤተ ክርስቲያን ከክርስቶስ በቀር አዳኝ ነኝ ያለው? ከመላእክትስ የትኛው መልአከ ነው ? ከነቢያት የትኛው ነቢይ ነው ? ከሐዋርያት የትኛው ሐዋርያ ነው ? ከሰማዕታትስ ከጻድቃንስ የትኛው ሰማዕት የትኛው ጻድቅ ነው በኔ ብታምኑ ትድናላችሁ ያለው። እነዚህ ሁሉ የደከሙት ፣ እነዚሁ ሁሉ ማሳየት የሚፈልጉት ፣ እነዚሁ ሁሉ እንድንገናኝ የሚጥሩት ፣ አንዱን በሰማይና

በምድር የመላውን ፣ ነገር ግን ሰው የሆነውን ፤ ስለኛ ራሱን አዋርዶ ፣ ስለ እኛ ራሱን ዝቅ አድርጎ የሞተውን ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ነው ። ከእርሱ በቀር መዳን ስለማንችል ከእሱ ጋር ተገናኝተን እንድንድን ፣ ሁሉም የሚያደርሱን ወደ ክርስቶስ ነው ።

ሁላችንም በወላዲተ አምላክ በድንግል ማርያም ምልጃ በእሷ ጸሎት ወደ ቤተ ክርስቲያን መጥተናል ። በተጨማሪም ንስሐ እንድንገባ ደግሞ በቅዱሳኑ ጸሎት ፣ ምልጃ ፣ ቃል ኪዳን ፤ በወቅቱ ባሉት የሃይማኖት አባቶች የወንጌል ትምህርት እና በመዝሙሩ ሁሉ ታግዘናል። ታዲያ ለመዳን ግን ምን ማድረግ አለብን ? የረከሰ ሕይወታችን እንዲቀደስ ምን ማድረግ አለብን ? በእርግጥ ንስሐ መግባት አለብን ። ኃጢአታችንንም መናዘዝ ይኖርብናል ። የረከሰ ሕይወታችን እንዲቀደስ ፣ ያደፈ ሕይወታችን እንዲነጻ ፣ ከኃጢአት ሰብራት እንድንጠገን በአጠቃላይ ከእግዚአብሔር ጋር እንድንታረቅ አንድ ነገር ብቻ ያስፈልገናል ። እርሱም ሥጋውንና ደሙን መቀበል ነው ። የምንቀበለው ሥጋና ደም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ነው ።

እዚህ ላይ እንድናስተውለው የሚያስፈልገው የምንቀበለው ሥጋና ደም የአብ አይደለም ፤ አብ ሥጋ የለውም ሥጋ አልለበሰምና ። የመንፈስ ቅዱስም አይደለም ፤ መንፈስ ቅዱስ ሥጋ የለውም ፥ መንፈስ ቅዱስ ሥጋ አልለበሰምና ። ነገር ግን ወልድ በተለየ አካሉ ከእመቤታችን ከቅድስት ማርያም ከነፍሷ ነፍስን ከሥጋዋ ሥጋን ነሥቶ በተዋሕዶ ፍጹም ሰው ሆኖ ስለ ሞተልን ፣ በአምላክነቱ ወልድ ፥ በሰውነቱ ኢየሱስ የተባለ ኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋውንና ደሙን በመቀበል የዘላለም ሕይወት ፥ የነፍስ መድኃኒት እናገኛለን ።

ስለ እምነታችን ለሚጠይቁን ሁሉ የምንመልሰውን እንወቅ ።

የቤተ ክርስቲያን አባቶች ዓለም አቀፍ ተቀባይነትን ባገኙት የቤተ ክርስቲያን ዓለም ዓቀፍ ጉባኤዎች ዶግማንና ቀኖናን በቅዱሳት መጻሕፍት ላይ ተመሥርተው ወስነዋል ። ቤተ ክርስቲያናችን ከምትቀበላቸው ጉባኤዎች መካከል ሁለቱን ለምሳሌ እንዲሆኑን ከዚህ በታች እናያለን።

የኒቅያ ጉባኤ

የሥላሴን አንድነትና ሦስትነት አይተናል ። ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል ወልድ በተለየ አካሉ ፍጹም ሰው ሆኗል ። እኛን ለማዳን በተዋሕዶ ፍጹም ሰው ሲሆን ፍጹም አምላክ ነው ። ስለዚህ ፍጹም ሰው በመሆኑ ፥ ሁለተኛ አዳም በመሆኑ ፣ የኛ ጠበቃ በመሆን የተገለጠው ኢየሱስ ክርስቶስ ፣ በዚህ ምድር ላይ ሰው የተናገረውን ተናግሯል ፤ ሰው እንደሚደክመው ደክሟል ፣ ሰው እንደሚርበው ተርቧል ፤ እንደምናዝን አዝኗል ፣ እንደምናለቅስ አልቅሷል ፣ ከኃጢአት በቀር ሁሉን ነገር እንደ እኛ አድርጓል ። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደሚታወቀው ፣ ወድዶ ያደርገውን መዋረድ ፣ ወድዶ ያደረገውን ራስን ዝቅ ማድርግ ፣ ወድዶ ያደረገውን እንደ አንድ ሰው መንቀሳቀስ ፣ ወድዶ ያደረገውን ነገር ሁሉ በማየት "ይህን ያደረገው እኮ ፍጡር ቢሆን ነው" በማለት "ፍጡር ነው" ብለው በድፍረት የሚያስተምሩ ሰዎች ተነስተው ነበር ።

ለምሳሌ የመጀመርያው ተጠራጣሪ ሰው አርዮስ ነው ። አርዮስ "ወልድ ፍጡር ነው" አለ ። ወልድ ፍጡር አለመሆኑን 318 ሊቃውንት በኒቅያ ተሰብስበው በቅዱሳት መጻሕፍት ምስክርነት አረጋገጡ ። ይህ የሆነው በ325 ዓ. ም. ኒቅያ በተባለ ጉባኤ ነው ። እነዚህ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ፍጡር ነው ያለ አርዮስንና ተከታዮቹን ፥ በእግዚአብሔር ቃል ምስክርነት ካስረዱና የክርስቶስን ፍጹም ሰውነቱንና ፥ ፍጹም አምላክነቱን አረጋግጠው አርዮስን አውግዘው ከለዩ በኋላ ፣ ከዛሬ ጀምሮ የዓለም ክርስቲያኖች ስማቸው «አርቶዶክስ» እንዲሆን ብለው ወሰኑ ። ከዚያ በፊት የነበሩት አማኞች በመጀመሪያ «ደቀ መዛሙርት» እየተባሉ ይጠሩ ነበረ ። በኋላ አንጾኪያ በተባለው ቦታ «ክርስቲያን» ተባሉ ። እስከ 325 ዓ. ም. እስከ ኒቅያ ጉባኤ ድረስ የአማኞች ስም ክርስቲያን ነበር (ሐዋ ዘ ፥ 26) ።

ስለዚህ ከ325 ዓ. ም. ጀምሮ አርቶዶክስ የሚለው ስም እስካሁን አለ ። አርቶዶክስ ማለት የቀና ሃይማኖት ማለት ሲሆን ፣ ደስ የሚለው የክርስቶስን ፍጹም አምላክነት ፣ ፍጹም ጌትነት የሚገልጽ ስም ነው እንጂ የኋላ ቀር ወይም የአከራሪነት ስያሜ አይደለም ። ክርስቶስ ሁልጊዜ አዲስ እንደሆነ ሁሉ ፥ አርቶዶክስ የሚለውም ስም ለኛ ሁልጊዜ አዲስ ነው ።

የቍስጥንጥንያ ጉባኤ

ሊቃውንት ከላይ የተጠቀሰውን ካሰረዱ በኋላ እንደገና ደግሞ ሌላ መቅዶንዮስ የተባለ ሰው በ381 ዓ.ም. መንፈስ ቅዱስን "ሕጹጽ ነው ፥ አካል የለውም ፥ ዝርው ነው ፥ እንደ አብ እንደ ወልድ አይደለም" ብሎ ተነሣ ።

እሱንም 150 ሊቃውንት በቍስጥንጥንያ ተሰብስበው በእግዚአብሔር ቃል ምስክርነት ካስረዱ በኋላ በኒቅያ ጉባኤ የተጀመረውን ፤ በቍስጥንጥንያ ጉባኤ ጨርሰው የሃይማኖታችን መግለጫ ምን መሆን እንዳለበት ወስነዋል ። ይህ የሃይማኖት መግለጫ ባጭሩ የእግዚአብሔር ልጆች ነን ለማለት ፤ የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆናችን ማረጋገጫ ነው ። ስለዚህ ለኦርቶዶክሳውያን የሃይማኖት መግለጫችን ፤ ዶግማችን ከ325 ዓ.ም ጀምሮ ተወስኖ ተሰጥቶናል ። ይህም ማለት እነሱ አዲስ ሃይማኖት ፈጠሩ ማለት አይደለም ። ሃይማኖቱ ድሮም ቢሆን የነበረ ነው ። ነገር ግን ያን የነበረውን ሃይማኖት ከመናፍቃን ተከላከለው እንድንጠብቀው ኤድርገው የሃይማኖታችንን መግለጫ አስረከበውን አልፈዋል ። አባቶች በውሳኔያቸው ስለ ምስጢረ ሥላሴ ፥ ስለ ምስጢረ ሥጋዌ ፥ ስለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ፥ ስለ ምሥጢረ ጥምቀት ፥ ስለ ትንሣኤ ሙታንና ስለሚመጣው ሕይወት ተናግረዋል ። እያንዳንዳችን ክርስቲያኖች ይህንን በቃላችን ልናውቅ ይገባል ። የሃይማኖታችን መግለጫ «ጸሎተ ሃይማኖት» ለኛ ለክርስቲያኖች መታወቂያ ካርዳችን ማለት ነው ። ስለዚህ እያንዳንዳችን ልናውቀው ልንረዳው ስለሚገባ እንደሚከተለው ቀርቧል ።

አንቀጸ ሃይማኖት (የሃይማኖት መግለጫ / ጸሎተ ሃይማኖት)

ስለ አብ

1) ***ሁሉን በያዘ ፥ ሰማይና ምድርን የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ በአንድ አምላክ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን ።***

የዚህ አንቀጽ ፍጹም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መነሻዎች ከዚህ የሚከተሉትና ሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ኃይለ ቃሎች ናቸው ።

ሀ/ «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ» ዘጸ 20 ፥ 3 ።

ለ/ «እግዚአብሔር በስድስት ቀን ሰማይንና ምድርን ፤ ባሕርንም ያለባቸውንም ፈጥሮ ፤ በሰባተኛው ቀን ዐርፎአልና» ። ዘጸ 20 ፥11 ።

ሐ/ «እንግዲህ እግዚአብሔር በላይ በሰማይ ፤ በታችም በምድር አምላክ እንደ ሆነ ፥ ሌላም እንደሌለ ዛሬ አወቅ» ። ዘዳ 4 ፥ 39 ።

መ/ «እስራኤል ሆይ ስማ ፤ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው»። ዘዳ 6 ፥ 4 ።

ሠ/ «ለእኛስ ነገር ሁሉ ፤ ከርሱ የሆነ ፤ እኛም ለእርሱ የሆንን አንድ አምላክ አብ አለን» ። ቆሮ 8 ፥ 6 ።

ረ/ «ከሁሉ በላይ የሚሆን ፤ በሁሉም የሚሠራ ፤ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ፤ የሁሉ አባት አለ» ። ኤፌ 4 ፥ 6 ።

ስለ ወልድ

2) ***ዓለም ሳይፈጠር ከርሱ ጋር በነበረ ፤ የአብ አንድ ልጁ በሚሆን ፤ በአንድ ጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን ።***

ለዚህም አንቀጽ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መነሻዎች ከዚህ የሚከተሉትና ሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ኃይለ ቃሎች ናቸው ።

ሀ/ «እግዚአብሔር አለኝ ፦ አንተ ልጄ ነህ ፤ እኔ ዛሬ ወለድኩህ» መዝ 2 ፥ 7 ። ዕብ 1 ፥ 5 ።

ለ/ «ከአጥቢያ ኮከብ አስቀድሞ ከሆድ ወለድኩህ» ። መዝ 109 ፥ 3 ።

ሐ/ «ቢአርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ፤ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወዶአልና ። ዮሐ 3 ፥ 16

መ/ «በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አመን አንተና ቤተሰቦችህ ትድናላችሁ» ። የሐዋ 16 ፥ 31

ሠ/ «ነገር ሁሉም በእርሱ በኩል የሆነ ፤ እኛም በእርሱ በኩል የሆንን ። አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን» ። ቆሮ 8 ፥ 6 ።

ረ/ «ይህም በሰማይና በምድር ፤ ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ ፤ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ ፤ ምላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው» ። ፊል 2 ፥ 10 ።

3) ***ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ፤ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ ፤ የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ ፤ በመለኮቱ ከአብ ጋር የሚተካከል ።***

ለዚህም አንቀጽ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መነሻዎች ከዚህ የሚከተሉትና ሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ኃይለ ቃሎች ናቸው።

ሀ/ «በመጀመሪያ ቃል ነበረ ፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ፣ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ» ። ዮሐ 1 ፥ 1 ።

ለ/ «እኔና አብ አንድ ነን»። ዮሐ 10 ፥ 30 ።

ሐ/ «እኔን ያየ አብን አይቶአል» ። ዮሐ 14 ፥ 9 ።

መ/ «ለአብ ያለው ሁሉ የእኔ ነው» ። ዮሐ 16 ፥ 15 ።

ሠ/ ከአብ ወጥቼ ወደ ዓለም መጥቻለሁ ፣ ደግሞ ዓለምን አተወዋለሁ ወደ አብም እሄዳለሁ» ። ዮሐ 16 ፥ 28 ።

ረ/ «ብርሃንም ወደ ዓለም ሰለ መጣ ፣ ሰዎችም ሥራቸው ክፉ ነበርና ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ሰለ ወደዱ ፍርዱ ይህ ነው» ። *ዮሐ 3 ፥ 19 ።*

4) ***ሁሉ በእርሱ ሆነ ፣ ያለ እርሱ ግን ምንም ምን የሆነ የለም ፣ በሰማይም ያለ፣ በምድርም ያለ ።***

ለዚህም አንቀጽ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መነሻዎች ከዚህ የሚከተሉትና ሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ኃይለ ቃሎች ናቸው ።

ሀ/ ሁሉ በእርሱ ሆነ ፥ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነምም» ። ዮሐ 1፥ 13 ።

ለ/ «የሚታዩትና የማይታዩትም ፥ ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት ፥ በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ ፣ በእርሱ ተፈጥረዋልና» ። ቆላ 1 ፥ 16 ።

<u>ስለ ምሥጢረ ሥጋዌ</u>

5) **ስለ እኛ ስለ ሰዎች ስለ መዳናችን ከሰማይ ወረደ ፣ ከመንፈስ ቅዱስ የተነሣ፣ ከቅድስት ድንግል ማርያም ፈጽሞ ሰው ሆነ ።**

ለዚህም አንቀጽ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መነሻዎች ከዚህ የሚከተሉትና ሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ኃይለ ቃሎች ናቸው።

ሀ/ «እነሆ ፥ ድንግል ትፀንሳለች ፥ ወንድ ልጅም ትወልዳለች ፥ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች» ። ኢሳ 7 ፥ 14 ።

ለ/ «መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት ፦ መንፈስ ቅዱስ ባንቺ ላይ ይመጣል ፥ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል ፤ ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል ። ሉቃ 1 ፥ 35 ።

ሐ/ «የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስም ልደት እንዲህ ነበረ ። እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ በመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች» ። ማቴ 1.፥ 18 ።

መ/ «ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች የተወለደውን ልጁን ላከ» ። ገላ 4 ፥ 4 ።

<u>ስለ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ</u>

6) ***ሰውም ሆኖ በጸንጠናዊው በጲላጦስ ዘመን ስለ እኛ ተሰቀለ ፥ ታመመ ፥ ሞተ ፥ ተቀበረ ፥ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ ። በቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ተጻፈ ።***

ለዚህም አንቀጽ ፍጹም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መነሻዎች ከዚህ የሚከተሉትና ሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ኃይለ ቃሎች ናቸው ።

ሀ/ «ጲላጦስም ሁከት እንዲጀመር እንጂ አንዳች እንዳይረባ ባየ ጊዜ ፥ ውኃ አንሥቶ ፦ እኔ ከዚህ ጻድቅ ሰው ደም ንጹሕ ነኝ ፤ እናንተ ተጠንቀቁ ሲል በሕዝቡ ፊት እጁን ታጠበ»። ማቴ 27 ፥ 24 ።

ለ/ «በዚያ ጊዜ በርባንን ፈታላቸው ፥ ኢየሱስን ግን ገርፎ ሊሰቀል አሳልፎ ሰጠ» ማቴ 27 ፥ 26 ።

ሐ/ «ኢየሱስም ሁለተኛ በታላቅ ድምፅ ጩኾ ነፍሱን ተወ» ። ማቴ 27 ፥ 50 ።

መ/ «ዮሴፍም ሥጋውን ይዞ በንጹሕ በፍታ ከፈነው ፤ ከዓለት በወቀረው በአዲሱ መቃብረም አኖረው ፥ በመቃብሩም ደጃፍ ታላቅ ድንጋይ አንከባሎ ሄደ» ። ማቴ 27፥ 59-60 ።

ሠ/ «እንደ ተናገረ ተነሥቶአልና በዚህ የለም» ። ማቴ 28 ፥ 6 ።

ረ/ «ሕያውን ከሙታን መካከል ስለ ምን ትፈልጋላችሁ ? ተነሥቶአል እንጂ በዚህ የለም» ሉቃ 24 ፥ 5 ።

ሰ/ «መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ ፥ ተቀበረም ፥ መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሥቶአል» ። ነቆሮ15 ፥ 4

ሸ «ክርስቶስም ካልተነሣ እንግዲያስ ስብከታችን ከንቱ ነው ። እምነታችሁም ደግሞ ከንቱ ናት» ። ነቆሮ 15 ፥ 14 ።

7) ***በክብር ወደ ሰማይ ዐረገ ፣ በአባቱም ቀኝ ተቀመጠ ፣ ዳግመኛም በጊትነት ይመጣል ። ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም ።***

ለዚህም አንቀጽ ፍጹም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መነሻዎች ከዚህ የሚከተሉትና ሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ኃይለ ቃሎች ናቸው ።

ሀ/ «ሲባርካቸውም ከእነርሱ ተለየ ወደ ሰማይም ዐረገ» ። ሉቃ 24 ፥ 51 ።

ለ/ «ከሰማይም ከወረደው በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም ፥ እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው» ። ዮሐ 3 ፥13 ።

ሐ/ «ይህንም ከተናገረ በኋላ እነርሱ እያዩት ከፍ ከፍ አለ ፤ ደመናም ከዓይናቸው ሰውራ ተቀበለችው» ። የሐዋ 1 ፥ 9 ።

መ/ «እርሱም ሲሄድ ወደ ሰማይ ትኩር ብለው ሲመለከቱ ሳሉ ፥ እነሆ ፥ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች በአጠገባቸው ቆሙ ፤ ደግሞም :- የገሊላ ሰዎች ሆይ ፥ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለ ምን ቁማችኋል ? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት ፥ እንዲሁ ይመጣል» ። ሐዋ 1 ፥ 10 ።

ሠ/ እነሆ ፥ ሰማያት ተከፍተው የሰው ልጅም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ አለ» ። የሐዋ 7 ፥ 55 ።

ረ/ «በሌሊት ራእይ አየሁ ፤ እነሆም ፥ የሰው ልጅ የሚመስል ከሰማይ ደመናት ጋር መጣ በዘመናት ወደ ሸመገለውም ደረሰ ፤ ወደ ፊቱም አቀረቡት ። ወገኖችና ሕዝብ በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ሁሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብር መንግሥትም ተሰጠው ፤ ግዛቱም የማያልፍ የዘላለም ግዛት ነው ፥ መንግሥቱም የማይጠፋ ነው» ። ዳን 7 ፥ 13።

ሰ/ «በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘላለም ይነግሣል ፤ ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም ። ሉቃ 1 ፥ 33 ።

ሸ/ «የሰው ልጅ ከመላእክቱ ጋር በአባቱ ክብር ይመጣ ዘንድ አለውና ያን ጊዜም ለሁሉም እንደ ሥራው ያስረክበዋል» ። ማቴ 16 ፥ 27 ።

ቀ/ «ጌታ እራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና» ። 1 ተሰ 4 ፥ 164.።

<u>ስለ መንፈስ ቅዱስ</u>

8) ***በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን ፥ ጌታ ፥ ለዳኝ በሆነ ፥ ከአብ በሠረጸ ፤ ለእነርሱም እናመሰግነው ፥ ከአብና ከወልድ ጋር በክቢያት የተናገረ ።***

ለዚህም አንቀጽ ፍጹም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መነሻዎች ከዚህ የሚከተሉትና ሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ኃይለ ቃሎች ናቸው ።

ሀ/ «እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ፥ ያዘዝኳችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው» ። ማቴ 28 ፥ 19 ።

ለ/ «ዳዊት ራሱ በመንፈስ ቅዱስ :- ጌታ ጌታዬን :- ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው» ። ማር 12 ፥ 36 ።

ሐ/ «ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ፥ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል» ። ዮሐ 15 ፥ 26 ።

መ/ «ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና ፥ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ» 2 ጴጥ 1 ፥ 21 ።

<u>ስለ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን</u>

9) ***ከሁሉ በላይ በምትሆን ፤ ሐዋርያት በሰበሰቡአት ፤ በእንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን ።***

ለዚህም አንቀጽ ፍጹም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መነሻዎች ከዚህ የሚከተሉትና ሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ኃይለ ቃሎች ናቸው ።

ሀ/ «አንተ ጴጥሮስ ነህ ፥ በዚህችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም» ። ማቴ 16 ፥ 18 ።

ለ/ «እነርሱንም ባይሰማ ለቤተ ክርስቲያን ንገራት ፤ ደግሞም ቤተ ክርስቲያንን ባይሰማት ፥ እንደ አረመኔና እንደ ቀራጭ ይሁንልህ» ማቴ 18፡-17

ሐ/ «ባሎች ሆይ ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ» ። ኤፌ 5 ፥ 25 ።

<u>ስለ ምሥጢረ ጥምቀት</u>

10) ***ኃጢአትን ለማስተሥረይ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን ።***

ለዚህም አንቀጽ ፍጹም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መነሻዎች ከዚህ የሚከተሉትና ሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ኃይለ ቃሎች ናቸው።

ሀ/ «ያመነ የተጠመቀም ይድናል ፥ ያላመነ ግን ይፈረድበታል» ። ማር 16 ፥ 16 ።

ለ/ «እውነት እውነት እልሃለው ፥ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም ። ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው ፥ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው ። ዮሐ 3 ፥ 5 ።

ሐ/ «ጴጥሮስም ፦ ንስሐ ግቡ ፥ ኃጢአታችሁም ይሠረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ» የሐዋ 2 ፥ 38 ።

መ/ «ይህም ውኃ ደግሞ ማለት ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል ፥ የሰውነትን አድፍ ማስወገድ አይደለም ፥ ለእግዚአብሔር የበጎ ሕሊና ልመና ነው እንጂ ፥ ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ነው ። 1 ጴጥ 3 ፥ 21።

ሠ/ «አንድ ጌታ ፥ አንድ ሃይማኖት ፥ አንዲት ጥምቀት» ። ኤፌ 4 ፥ 15 ።

<u>ስለ ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን</u>

11) ***የሙታንንም መነሣት ተስፋ እናደርጋለን ።***

12) ***የሚመጣውንም ሕይወት ፣ ለዘላለሙ እሜን።***

ለዚህም አንቀጽ ፍጹም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መነሻዎች ከዚህ የሚከተሉትና ሌሎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ኃይለ ቃሎች ናቸው።

ሀ/ «በምድርም ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉቱ ብዙዎች ይነቃሉ ፤ እኩሌቶቹ ወደ ዘላለም ሕይወት ፥ እኩሌቶቹም ወደ እፍረትና ወደ ዘላለም ጉስቁልና» ። ዳን 12 ፥ 2 ።

ለ/ «መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ፥ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና» ። ዮሐ 5 ፥ 29 ።

<u>ማጠቃለያ</u>

የቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት <u>ዶግማ እና ቀኖና</u> በሚል በሁለት የተከፈለ መሆኑን ከዚህ በላይ ተመልክተናል ። ዶግማ የእግዚአብሔርን መኖር ፥ የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት ፥ የክርስቶስን አዳኝነት የምንረዳበት ከእግዚአብሔር የተሰጠን ሰማያዊ ጸጋ ነው ። ዶግማ የሚሻሻል አይደለምና <u>ጽድቅና ኩነኔ</u> ፥ <u>ሞትና ሕይወት</u> በዶግማ መሆኑን ተረድተን እስከ ሞት ድረስ መጠበቅ አለብን ። ይህንንም አስመልክቶ የእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል እንዲህ ይላል «እስከ ሞት ድረስ የታመንህ ሁን ፥ የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለው» (ራእ 2 ፥ 10) ።

በተጨማሪም የዶግማና ቀኖና ምንጭ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስም የሚገኘው ከዶግማ ውስጥ መሆኑን ልናስተውል ይገባል ።

ምዕራፍ ሁለት

<u>ቀኖና</u>

ከዶግማ ቀጥለን የምናየው ትምህርት ስለ ቀኖና ነው ። ይህ ትምህርት ትንሽ ከበድ ሊል ይችላል ። አንዳንዶች እንዲያውም "ይህ ትምህርት ለምን አስፈለገ?" ብለው የሚጠይቁ አሉ ። ይሁን እንጂ ትምህርቱ በጣም አስፈላጊ ስለሆነ እንደሚከተለው ቀርቧል ።

ቀኖና የሚመሠረተው ፥ የሚሠራው ከሐዋርያት ጀምሮ በቅዱስ ሲኖዶስ ነው ። ስለዚህ በቀኖና ላይ ቅዱስ ሲኖዶስ ሙሉ ሥልጣን አለው ። ለቤተ ክርስቲያን ደኅንነት ፥ ቅዱሳት መጻሕፍትን ለመጠበቅ ፥ ቤተ ክርስቲያንን ከመናፍቃን ለመከላከል ፥ እንደዚሁም ክርስቲያኖች በክርስቲያናዊ ሕይወትና በሥርዓት እንዲኖሩ በአጠቃላይ ለመልካም ነገር ከሐዋርያት ጀምሮ የሃይማኖት አባቶች ቀኖናን ለቤተ ክርስቲያን እድገት ይደነግጋሉ ፥ ያሻሽላሉ ፥ ካስፈለገ ይጨምራሉ ፥ ወይንም ይቀንሳሉ ።

ቅዱስ ሲኖዶስ ሲባል ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊት የሆነችው የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የጳጳሳት ጉባዔ ማለት ነው ። ይህ ጉባዔ ከሐዋርያት ጀምሮ ያለ ነው ። የሲኖዶስ ዋና ትልቁ ሥራው መንጋውን መምራት ነው ። መንጋውን ለመምራት ደግሞ ሕግ ያስፈልገዋል ፤ ምክንያቱም የክርስቲያኖች ጎበረት የእግዚአብሔር መንግሥት ነውና ። በዚህ ዓለም ያሉ መንግሥታት ሕዝባቸውን ለመምራት የግድ ሕግ ያስፈልጋቸዋል ። ልክ እንደዚህ ሁሉ የእግዚአብሔር መንግሥት የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን እንዲመሩ ከመንፈስ ቅዱስ ሥልጣን የተሰጣቸው የሃይማኖት አባቶች ጳጳሳት ጉባኤያቸው ሲኖዶስ ስለሚባል ፥ ሲኖዶስ በተባለው ጉባኤያቸው ሕግን ይሠራሉ ። በዚያ በሚሠሩት ሕግ ላይ የመጨመር ወይም የመቀነስ ሙሉ ሥልጣን መንፈስ ቅዱስ ሰጥቷቸዋል ።

ወገኖቼ ፤ ዛሬ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከመቼውም ዘመን የበለጠ ችግር ላይ ትገኛለች ። ቤተ ክርስቲያኗ የወላድ መካን እየሆነች ነው ። በየጊዜው ታጠምቃለች ፥ ታሳድጋለች ፥ አንገታቸው ወጣ ሲል ለሌሎች ታስረክባለች ። እነዚህ ሰዎች የሚሄዱት በመታለል ብቻ አይደለም ። ሌሎች የሚነግሯቸው ሁሉ እውነት እየመሰላቸውም ነው እንጂ ። አባቶቻችን ቀኖና ውስጥ የሰጡንን ፤ ያስረከቡንን ነገር «ሃይማኖት ነው ብላችሁ በሥርዓቱ ድነናል ትላላችሁ» ፤ ብለው ሲጠይቁንእኛ የምንመልሰው ስለሌለን ፤ ልጆቻችንም አብዛኛውን ጊዜ የሚመልሱት ስለሌላቸው ፤ እኛንም ሲጠይቁ አንዳንድ ጊዜ

ተገቢውን መልስ ስለማንሰጥ ፣ ልጆቻችን ሃይማኖታችን ውሸት እየመሰላቸው እየተዉት ለሌላው ሲሳይ ሆነዋል ። በተለይም ለአዲሱ ትውልድ እንደዚሁም በምዕራቡ ከፍለ ዓለም የሚወለዱትን ለመተካትና ለመጠበቅ ይህንን ትምህርት ለይተን መማርና ማወቅ ይኖርብናል ። በመሆኑም ከዚሁ የበለጠ ችግር ያለመኖሩን በመንገዘብ ስለቀኖና እናማራለን።

ቀኖና ማለት መንፈስ ቅዱስ የሚመራው ቅዱስ ሲኖዶስ ለቤተ ክርስቲያን ጥቅም የሚሠራው ፣ የሚደነግገው ሥርዓት ነው ።

ቀኖና ለምን አስፈለገ ?

ቀኖና ያስፈለገበት ዓይነተኛ ምክንያቶች ከዚህ የሚከተሉት ናቸው።

1/ ቤተ ክርስቲያንን ከቢጽ ሐሳውያንና ከመናፍቃን ትምህርት ለመጠበቅ፣

2/ ቤተ ክርስቲያንን በሥርዓት ለመምራት፣

3/ ቅዱሳት መጻሕፍትን ከመናፍቃን መጻሕፍት ለመለየት ነው።

1) ቤተ ክርስቲያንን ከቢጽ ሐሳውያንና ከመናፍቃን ትምህርት ለመጠበቅ ።

«ቢጽ ሐሳውያን» ማለት ሐሰተኞች ወንድሞች ማለት ነው ። ቢጽ ማለት ወንድሞች ማለት ነውና ። ከአሪት እምነት ወደ ክርስትና የገቡ አንዳንድ ወንድሞች ከክርስቶስ በላይ ፣ ከሐዋርያው ከቅዱስ ጳውሎስና ከሐዋርያት በላይ እናስባለን በሚል ፣ ወንጌል ያለ አሪት ፥ ጥምቀት ያለ ግዝረት አይረባም ፥ አይጠቅምም ብለው የመጀመሪያዎቹን ክርስቲያኖች ማደናገር ስለ ጀመሩ ፣ ቅዱስ ጳውሎስ «ቢጽ ሐሳውያን» አላቸው ። ውሸታሞች ወንድሞች ለማለት ነው ። ቢጽ ሐሳውያን የሚባሉት ከአይሁድ እምነት ወደ ክርስትና የተመለሱት ናቸው ። ግን ሥርዓትን በተመለከተ "የሙሴ ሥርዓት ከወንጌል ጋር አብሮ መራመድ አለበት ፤ እንደ ሙሴ ሥርዓት ካልተገረዛችሁ ትድኑ ዘንድ አትችሉም" ብለው ማስተማር ጀምረው የነበሩ ናቸው ።

«መናፍቃን» የሚባሉት ደግሞ ፣ በተለይም ከሥላሴ ትምህርት ውስጥ የሚቀንሱ ፣ የሚያጎድሉ ፣ ከአባቶቻችን ትምህርት ከኒቅያ ጉባዔ ፣ ከቀስጥንጥንያ ጉባኤ ፣ ከኤፌሶን ጉባኤ ፣ በተለይም ሐዋርያት ካስተማሩን ከወንጌል ወጥተው ከሥላሴ አንድነት ሦስትነት፣ ከክርስቶስ የባሕርይ አምላክነት ፣ ከምሥጢረ ሥጋዌ ላይ የሚያጎድሉ ፣ የሚቀንሱ ፥ መልካሙን ትምህርት የሚያበላሹ ናቸው ።

ቀኖና ያስፈለገበትን የመጀመሪያውን ምክንያት በመጠኑ ለማብራራት በቀጥታ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰደውን እናያለን ።

«አንዳንዶችም ከይሁዳ ወረዱና ፦ እንደ ሙሴ ሥርዓት ካልተገረዛችሁ ትድኑ ዘንድ አትችሉም ብለው ወንድሞችን ያስተምሩ ነበር ። በእነሱና በጳውሎስ በበርናባስም መካከል ብዙ ጥልና ክርክር በሆነ ጊዜ ስለዚህ ክርክር ጳውሎስና በርናባስ ከእነርሱም አንዳንዶች ሌሎች ሰዎች ወደ ሐዋርያት ወደ ቀሳውስትም ወደ ኢየሩሳሌም ይወጡ ዘንድ ተቆረጠ » ይላል ። (የሐዋ 15 ፥ 1-2) ።

ሁለተኛ ጥቅስ ደግሞ በዚያው በሐዋርያት ሥራ «ከፈሪሳውያን ወገን ግን ያመኑት አንዳንዶቹ ተነሥተው ትገርዙአቸው ዘንድ እና የሙሴን ሕግ እንዲጠብቁ ታዙአቸው ዘንድ ይገባል አሉ» ይላል ። (የሐዋ 15 ፥ 5)

አሁንም የሐዋርያት ሥራ «ሐዋርያትና ቀሳውሳትም ስለዚህ ነገር ለመመካከር ተሰበሰቡ» ይላል ። (የሐዋ 15 ፥ 6) ።

ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ የምንረዳው የመጀመርያው ሲኖዶስ ይህ የሐዋርያት ጉባኤ ነው ። ሐዋርያት ተሰብስበው ሲመካከሩ «ከብዙ ክርክርም በኋላ ቅዱስ ጴጥሮስ ተነሥቶ እንዲህ አላቸው ... «እንግዲህ አባቶቻችንና እኛ ልንሸከመው ያልቻልነውን ቀንበር በደቀ መዛሙርት ጫንቃ ላይ በመጫን እግዚአብሔርን አሁን ስለ ምን ትፈታተናላችሁ ? ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ እንደ እነርሱ ደግሞ እንድን ዘንድ እናምናለን» በማለት ንግግሩን ደመደመ ። (ሐዋ 15 ፥ 7-11) ።

በዚሁ ጉባኤ ሐዋርያት በሚከተለው አንቀጽ ውስጥ የተጠቀሰውን ውሳኔ ወሰኑ ።

የሐዋርያት የመጀመሪያው ሲኖዶስ ይህን ችግር ለመፍታት ተሰብስቦ «ሐዋርያትና ሽማግሌዎች ወንድሞችም በአንጾኪያና በሶርያ በኪልቅያም ለሚኖሩ ከአሕዛብ ወገን ለሆኑ ወንድሞች ሰላምታ ያቀርባሉ ። ያላዘዝናቸው ሰዎች ከኛ ወጥተው ፦ ትገረዙ ዘንድና ሕግን ትጠብቁ ዘንድ ይገባችኋል ብለው ልባችሁን እያወኩ በቃል እንዳናወጡአችሁ ስለ ሰማን ፥ ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነፍሳቸውን ከሰጡት ከምንወዳቸው ከበርናባስና ከጳውሎስ ጋር የተመረጡትን ሰዎች ወደ እናንተ እንልክ ዘንድ በአንድ ልብ ሆነን ፈቀድን ። ራሳቸውም ደግሞ በቃላቸው ያንኑ ይነግሩአችሁ ዘንድ ይሁዳንና ሲላስን ልከናል ። ለጣዖት ከተሠዋ ፥ ከደምም ፥ ከታነቀም፥ ከዝሙትም ትርቁ ዘንድ ከዚህ ከሚያስፈልገው በቀር ሌላ ሸክም እንዳንጭንባችሁ እኛና መንፈስ ቅዱስ

ፈቅደናልና ፤ ከዚህም ሁሉ ራሳችሁን ብትጠብቁ በመልካም ትኖራላችሁ ። ጤና ይስጣችሁ» ብለው ላኩ ። (የሐዋ 15 ፥ 23-29) ።

አባቶቻችን ሐዋርያት በመጀመሪያው ሲኖዶስ የወሰኗቸው ፡- ዋና ዋና ነጥቦች ።

1/ ለጣዖት የተሠዋ እንዳይበሉ ፤

2/ የእንስሳትን ደም እንዳይበሉ ፤

3/ ታንቆ የሞተ የእንስሳ ሥጋ እንዳይበሉ ፤

4/ ከዝሙትም እንዲርቁ ነው ።

ደምን መብላት በተመለከተ በአገራችን በገበሬው ዘንድ የበሬውንም የበጉንም ደም በብረት ምጣድ ቆልተው ወይም ጠብሰው የሚበሉ አሉ ። ይኸውና ከላይ በተጠቀሰው ከፍለ ንባብ እንደተጠቀሰው «ከደምም ፥ ከታነቀም» በማለት ቅዱሳን ሐዋርያት ከልከለዋል ።

ዝሙትንም በተመለከተ በአማኞች ዘንድ እንደ ቀላል ስሕተት ይታይ ስለ ነበር አባቶቻችን ሐዋርያት ከአራቱ ነጥቦች አንዱ ሊድርገው አስቀምጠውልናል ። ከዚህም በማያያዝ ከሚያስፈልገው በቀር ሌላ ሸክም እንዳንጭንባችሁ እኛና መንፈስ ቅዱስ ፈቅደናልና ። ከዚህም ሁሉ ራሳችሁን ብትጠብቁ በመልካም ትኖራላችሁ ፤ ጤና ይስጣችሁ» በማለት ወሰኑ ። በመጀመሪያ ታውካ የነበረችው ቤተ ክርስቲያንም በዚህ ውሳኔ መሠረት ሰላም አገኘች ። ወንጌልም ለማደግ ዕድል አገኘች ፤ አንዱ አንዱን መወንጀሉ አከተመ ።

የተወደዳችሁ ምእመናን! በወንጌል እውቀት ካልበሰልን ፤ ወንጌልን ካልጠየቅን ምንጊዜም ቢሆን መሰላታችን አይቀርም ። ውሸታም እውነተኛ ሊመስል ይችላል ። ስለዚህ ይህ ዓይነት ችግር በመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ነበር ። ቤተ ክርስቲያን ሰላም ያገኘችው ከላይ በተጠቀሰው መሠረት ሐዋርያት የመጀመሪያውን ቀኖና ከሠሩና የእነሱም ተከታዮች የቤተ ክርስቲያን አባቶች በየጊዜው እንደ አስፈላጊነቱ በሲኖዶሳቸው ሥርዐተ ቀኖና በማውጣታቸው ነው ።

2) <u>ቤተ ክርስቲያንን በሥርዓት ለመምራት ነው</u> ።

ቀኖና ያስፈለገበት ሁለተኛው ምክንያት ቤተ ክርስቲያንን በሥርዓት ለመምራት ነው። በወቅቱ ከአይሁድም ፥ ከአሕዛብም ወደ ክርስትና ይገቡ ስለነበር ፤ እነዚህን ሁሉ አንድ ወጥ በሆነ ሕግና ሥርዓት ለመምራት ቀኖና እጅግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው ።

«በከተማዎችም ሲዞሩ በኢየሩሳሌም የነበሩት ሐዋርያትና ቀሳውስት የቆረጡትን ሥርዓት ይጠብቁ ዘንድ ሰጡአቸው ። አብያተ ክርስቲያናትም በሃይማኖት ይበረቱ ነበር ፥ በቍጥርም ዕለት ዕለት ይበዙ ነበር» ይላል ። (ሐዋ 16 ፥ 4-5) ።

ከዚህ የምንረዳው ሥርዓት ለሃይማኖት ብርታትን ይሰጣል ። ሥርዓት ሲኖር በቍጥርም መብዛት ይኖራል ፤ ሥርዓት ካለ ፍቅር አለና ።

ሌላው «ወንድሞች ሆይ ! በሁሉ ስለምታስቡኝና አሳልፌ እንደሰጠኋችሁ ወግን ፈጽማችሁ ስለ ያዛችሁ አመሰግናችኋለሁ» ይላል ። (1ቆሮ 11 ፥ 2) ።

እዚህ ላይ ቅዱስ ጳውሎስ «መልካም ወግ» ያላት ወንጌልን ነው ፤ ጠቃሚ ነው ። «ማንም በሚያባብል ቃል እንዳያስታችሁ ይህን እላለሁ ። በሥጋ ምንም እንኳ ብርቅ በመንፈስ ከእናንተ ጋር ነኝና ሥርዓታችሁንም በክርስቶስም ያለውን የእምነታችሁን ጽንአት እያየሁ ደስ ይለኛል» ይላል ። (ቈላ 2 ፥ 5) ።

"እንግዲያስ ወንድሞች ሆይ ጸንታችሁ ቁሙ ፤ በቃላችንም ቢሆን ወይም በመልእክታችን የተማራችሁትን ወግ ያዙ" ይላል ። (2ተሰ 2 ፥ 15) ።

"ወንድሞች ሆይ ከእኛ እንደ ተቀበለው ወግ ሳይሆን ያለ ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዝዛችኋለን ። እኛን ልትመስሉ እንዴት እንደሚገባችሁ ራሳችሁ ታውቃላችሁና ፥ በእናንተ ዘንድ ያለ ሥርዓት አልሄድንምና ።" (2ተሰ 3 ፥ 6) ።

"ስለዚህ ወንድሞች ሆይ ፥ ትንቢት ለመናገር በብርቱ ፈልጉ ፥ በልሳኖች ከመናገርም አትከልክሉ ፤ ነገር ግን ሁሉ በአግባብና በሥርዓት ይሁን" (1ቆሮ 14 ፥ 39)

"ንቁ በሃይማኖት ቁሙ ፥ ጎልምሱ ፥ ጠንክሩ ። በእናንተ ዘንድ ሁሉ በፍቅር ይሁን"» (1ቆሮ 16 ፥ 13) እያለ ይሄዳል ። ሥርዓት ማለት ይሄ ነው ። የተጀመረው በሐዋርያት ጊዜ ነው ። ከሐዋርያት ጀምሮ የቀጠለው ሲኖዶስ እስከ አሁን ድረስ ሥርዓትን የመሥራት ኃላፊነት አለበት ።

3) <u>ቅዱሳን መጻሕፍትን ከመናፍቃን መጻሕፍት ለመለየት ነው</u> ።

ሦስተኛው ምክንያት ቅዱሳት መጻሕፍትን ከመናፍቃን መጻሕፍት ለይቶ ለማወቅ ነው ። ለምሳሌ እኛ ሰማንያ አንድ የምንለው መጽሐፍ ቅዱስ በቀኖና የተገኘ ነው ። ስለዚህ እውነተኞችን ቅዱሳት መጻሕፍት ከውሸተኞች የሚለዩት በቀኖና ነው ። አባቶቻችን ቅዱሳት መጻሕፍትን ከመናፍቃን መጻሕፍት የለዩት በዚሁ ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን በቀኖና ላይ ተመሥርተው ነው ። ቀኖና ሲኖር ነው መለየት የሚቻለው ።

«የከበርክ ቴዎፍሎስ ሆይ ! ከመጀመሪያው በዓይን ያዩትና የቃሉ አገልጋዮች የሆኑት እንዳስተላለፉልን ፥ በኛ ዘንድ ስለ ተፈጸመው ነገር ብዙዎች ታሪክን በየተራው ለማዘጋጀት ስለሞከሩ ፥ እኔ ደግሞ ስለተማርኸው ቃል እርግጡን እንድታውቅ በጥንቃቄ ሁሉን ከመጀመሪያው ተከትዬ በየተራው ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ» ይላል ። (ሉቃ 1 ፥ 1-4)

ይህ ማለት በዚያ ወቅት ልዩ ልዩ ጽሑፎችን የሚያዘጋጁ ግኖስቲኮችና ሌሎችም ሰዎች ነበሩ ። እነዚህ ሰዎች «የማቴዎስ ወንጌል» ፤ «የበርናባስ ወንጌል» እያሉ ያምታቱ ነበር ። ከዚያ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን እውነተኞችን ቅዱሳት መጻሕፍት ፥ እውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል ያለባቸው መጻሕፍትን ለይተው ከእነዚህ በቀር ሌላ እንዳትቀበሉ ብለው አባቶቻችን ወስነውልን አለፉ ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ተከታዩ ቅዱስ ሲኖዶስ እያጸናና እየጠበቀ እስካለንበት ደርሷል ። እናም የዛሬው ቅዱስ ሲኖዶስ አንድ ችግር ቢነሣ ሥርዓቱን የመጠበቅ ፥ የማጽናት ፥ "ይሄ ትክክል ነው ፥ ያ ትክክል አይደለም" የማለት ኃላፊነት ስላለበት ታሪኩ ከዚያ ተያይዞ የመጣ ነው ለማለት ነው ።

ቀደም ተብሎ እንደተጠቀሰው ቀኖና በየጊዜው ሊሻሻል ይችላል ። ቀኖና የእምነትና ያዳነን የክርስቶስ ፍቅር መግለጫ መሆኑን ማወቅ አለብን ። በዚህ ላይ ሲኖዶስ ሙሉ ሥልጣን ያለው መሆኑን ካላመንንና ለውሳኔአቸውን ለመተግበር ካልተዘጋጀን በምንም ዓይነት ቤተ ክርስቲያን በሰላም ልትኖር አትችልም ። አለመታዘዝ እራሱ ኃጢአት መሆኑንም ማወቅ አለብን ።

የኛ ትልቁ ችግራችን "አታድርጉ" ስንባል ማድረጋችን ፥ "አድርጉ" ስንባል አለማድረጋችን ነው ። ታዲያ ከብዶ ከሆነ ሊያቀል ቀልሎም ከሆነ ሊጨምር ቅዱስ ሲኖዶስ ጉባኤ ሲዘረጋ «አይሞከርም» ማለትን ምን አመጣው ? ያ የሆነበት ምክንያት የቀኖና ትምህርት በስፋት ስላልተሰጠ ነው ። የቀኖና ትምህርት ካልተሰጠ መጨመርም ሆነ መቀነስ ፥ መሻሻልም ወይንም ማሻሻልም ስለሚያስቸግር ይህችን ቤተ ክርስቲያን በምንም ዓይነት መልኩ ማሳደግ አይቻልም ።

ስለዚህ ስለሚጨመሩ ፥ ስለሚሻሻሉ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች እኛ አርቶዶክሳውያን የግድ ማወቅ ይኖርብናል ። ይህን ካላወቅን ፥ ሲኖዶስ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ፥ ለምእመናን የሚከብዳቸውን የማቅለል ፥ የሚቀልላቸውን የማከበድ ኃላፊነት እንዳለበት ካልተረዳን ለቅዱስ ሲኖዶስ መንፈሳዊ አመራር እንቅፋት ይሆናል ።

ቀኖና የሚሻሻለው በዘፈቀደ አይደለም ። የሚሻሻለው በሲኖዶስና በሲኖዶስ ብቻ ነው ። ቅዱስ ሲኖዶስ እስካላሻሻለ ድረስ እኛ በሥልጣናችን

ማሻሻል አንችልም ። ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ቀኖናን ማሻሻል እንደሚችሉ የሚገልጹትን ማስረጃዎች እንመልከት ።

«በሥራ ፍጹም የሆነ ሁሉ ጎደሎውን ሊሸረው ይገባልና ። ስለዚህ የጌታችን ሕግ [ወንጌል] ከእርስዋ የሚቀድመውን አሪትን ሻረችው ። እርሷ ወይም ወንጌል ግን ልትሻር አይገባትም ። ከእርስዋ የሚበልጥ የለምና ። እርሷ የፍጹምነትና የመጨረሻ ፍጽምት ሕግ ናትና» ይላል ። (ፍትሐ ነገሥት ፥ መቅደም ገጽ 7) ።

ይህ ፍትሐ ነገሥት በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ያገኘነው መጽሐፋችን ነው ። ሌላው «ምናልባት እኛ ያጎደልነው ነገር ቢኖር በሁላችንም መንፈስ ቅዱስ አድሮብናል እናንተ እንደሚገባ አድርጋችሁ ፍረዱ» ይላል (ትእዛዘ 71) ። በዚህ ላይ ማስተዋል ያለብን ይህንን መመሪያ የሰጠን ቅዱስ ሲኖዶስ መሆኑን ነው ። በመቀጠልም አባቶቻችን «ከኛ የቀረ ምንም ቢኖር ኤጲስ ቆጶስ ይፈጽም» ይላሉ (ትእዛዝ 35) ።

«የተወደዳችሁ ወንድሞቻችን ሆይ ! ቤተ ክርስቲያን በሚገባ ወደ ጸጥታ ወደብ ትመራ ዘንድ ከእኛ የቀረ ምንም ሥርዓት ቢኖር እግዚአብሔር ለሚገባው ሰው ይግለጥለት» ይላል (ትእዛዝ 47) ።

ሌላው «እነሆ በዚህ መጽሐፍ መጨረሻ ላይ ለሊቃውንት የሚገባው ነገር ተጽፏል፣ በእርሱ ላይ እንዲጨምሩ ከእርሱም እንዲቀንሱ በዚህ ውስጥ ያልተፈቀደላቸው ነገር የለም» ይላል ። (ፍትሐ ነገሥት መቅድም ፥ ገጽ 11)

«ያልተፈቀደላቸው የለም» የተባለው ሲኖዶስ በተባለ ጉባኤ ለሚሰበሰቡ ቤተ ክርስቲያንን ለሚመሩ ጳጳሳት ነው ። ቤተ ክርስቲያንን በሰላም ለመምራት የመጨመርም ፥ የመቀነስም መብት እንዳላቸው መንፈስ ቅዱስ ፈቅዶአል ። አባቶቻችንም «እኛም ፈቅደናል» ይላሉ ። ስለዚህ የዶግማንና የቀኖናን ልዩነት ካላወቅን የምንኖረው እየተምታታብን መሆኑን መረዳት ይገባል ።

<u>የቀኖና ዓላማ</u>

የቀኖና ዓላማ ስለ ጾም ቀናት ማነስና መብዛት ፥ ስለ ጾም የምግብ ሰዓት ፥ ስለ በዓላት ማነስና መብዛት ፥ ስለ በዓላት መቼ መሆን እንደሚገባ ፥ ስለ ቅዳሴ ሥርዓት ፥ በስንት ? መቼ ? እንዴት መቀደስ እንደሚገባ ፥ ስለ ሴቶች እና ስለ ወንዶች መግቢያ በርና መቆሚያ ቦታ ? ስለ ሕፃናት በአርባ ፥ በሰማንያ ቀን መጠመቅ ፥ ስለ መስቀል መሳለም ፥ ስለ ቅዱስ ሥዕል ፥ ስለ አዲስ ኪዳን የታቦት አገልግሎት ፥ ስለ ቤተ መቅደስ ሥርዓት በሙሉ ፥ ስለ ዝክርና ተዝካር ፥ ስለ ጸሎተ ፍትሐትና ስለመሳሰሉት የሚደነግግ ነው ። ቀኖና መሠረቱን ሳይለቅ

እንደ ጊዜው ሁኔታ ሊሻሻል የሚችል ሥርዓት ነው ። ለምሳሌም ጌታችን ጹሙ ብሎአል ፤ ኃይላችሁ ነው ብሎአል (ማቴ 17 ፥ 21) ። ስለዚህ ጾም የግድ አስፈላጊ ነው ። ግን መቼ ? ስንት ቀን ? ስንት ወር ? እንዴት ? የሚለውን መወሰን የሲኖዶስ ኃላፊነት ነው ።

ጌታ የጾመው አርባ ቀናት ነው ፤ እኛ ደግሞ አምሳ አምስት ቀናትን እንጾማለን ። ምዕራባዊውያን የኦርቶዶክስ ተቃዋሚዎች «አናንተ አሥራ አምስት ቀን ጨምራችኋል ፤ ከየት አመጣችሁት ? ከመጽሐፍ ቅዱስ የሌለውን እንዲያው ዝም ብላችሁ በልማድ የምትኖሩ» ቢሏችሁ ምን ትላላችሁ ?

መልሱ ለቤተ ክርስቲያን ጥቅም ፤ ለክርስቲያኖች መንፈሳዊ ኃይል ፤ ለልዩ ታሪክና የወንጌል ትምህርት ሲባል በሲኖዶስ አሥራ አምስት ቀን ተጨምሮአል የሚል ነው ። አሥራ አምስት ቀን የተጨመረበት ሌላ ታሪክ አለው ፤ ሆኖም በዚህ ርእስ ውስጥ አሁን አንገባበትም ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሐዲስ ኪዳን ፍልሰታን አሥራ አምስት ቀን ጹሙ የሚል ቃል የለም ። ለሚጠይቁን አሁንም መልሱ ለቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ኃይል ፤ ለልዩ ጥቅም ፤ ለልዩ ታሪክ ፤ ለልዩ የእመቤታችን ምሥጢራዊ ፍቅር ራሱን የቻለ ሕይወት ስለ ሆነ በቅዱስ ሲኖዶስ ፤ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን የተደነገገ ነው የሚል ነው ።

በተጨማሪ «ዓርብ ረቡዕን ጹሙ» የሚል ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አላገኘንም ። ዓርብ ረቡዕ የተጨመሩት በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ነው ። ረቡዕ ጌታን ለመግደል የአይሁድ ካህናት የተፈራረሙበትን ፤ ዓርብ ደግሞ ስለኛ የተሰቀለበትን ፥ የተሠዋበትን ቀን ለማስታወስ ነው ። ዛሬም «ቤተ ክርስቲያንን አናጥፋ ፤ ክርስቲያኖችን እንግደል ፤ እንስቀል» ከሚሉት እንዲያድናት ይህን ለመጠቀም አባቶቻችን የደነገጉልን በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ነው ። ስለ ገና ጾምም ፤ ስለ ጾመ ሐዋርያትም ፤ ስለ ጾመ ገሀድም ከመጽሐፍ ቅዱስ መልስ እናገኛለን ብላችሁ ቁፋሮ አትግቡ ። መልሱ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ብቻ የሚገኝ ነው ።

ስለ በዓላት መብዛትና ማነስ በሚመለከትም ፤ ለምሳሌ ያህል ቃና ዘገሊላ ጥር 12 ቀን ይከበራል ፤ ነገር ግን የቃና ዘገሊላ ታሪክ የተፈጸመው በየካቲት ወር ውስጥ ነው ። ወደዚህ መጥቶ እንዲከበር ያደረገው ቅዱስ ሲኖዶስ ነው ። አብዛኞች እኛ የምናከብራቸው በዓላት ፤ ለምሳሌ ያህል በክረምት ከሆነ የሚውሉት ፤ አባቶቻችን ወደ በጋ ወራት አምጥተዋቸዋል ። ለምን ቢባል ? ክርስቲያኖች እንዲመቻቸውና እንዳይከብዳቸው ነው። ዋናው ነገር ያ ቀን መታሰቡ ነው ። ምእመናንን የሚጠቅም ይሁን እንጂ የቀኑ መዘዋወር ችግር የለውም።

በተጨማሪ እንደ ምሳሌ በኩረ በዓላት ፤ ማለትም የበዓላት መጀመሪያ የሆነችውን እሑድን እንውሰዳት ። እሑድ ራስዋ በቤተ ክርስቲያን በሰንበትነት የተወሰነችው በ325 ዓ.ም በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ነው ።

የቅዳሴ ሥርዓትን አንሥተን በስንት ? መቼ ? የሚሉትን ጥያቄዎች እንመልከት ። ለምሳሌ በሀገራችን ቅዳሴ አምስት ካህናት ካልሞሉ ሲቀደስ አይታችሁ ታውቃላችሁ ? በምንም ዓይነት አይሞከርም ፤ አራት ቢሆኑ እንኳን አይቀደስም ፤ የግድ አምስት መሙላት አለባቸው ። በውጭው ሀገር በአሜሪካና በሌላው ሀገር ግን ፥ እንደ ሀገራችን ካህን ባለመትረፍረፉ ፣ ጳጳሳትም ስላልተጨመሩልን አንድ ካህን ብቻውንም ቢሆን ቀድሶ ያቆርባል ። አንድ ካህን ቀድሶ ክርስትና ያነሣል ፤ ለምን ? ቀኖና በመሆኑ በችግር ጊዜ ሊሻሻል ስለሚችል ነው ። ኢትዮጵያ ግን የካህን ችግር ስለሌለባት በአምስት ፥ በሰባት ከዚያም በላይ በአሥራ ሁለት ሊሆን ይችላል ። ነገር ግን ችግር ካለ አንድም ካህን ቢሆን ቀድሶ ማቁረብ ይችላል ።

ጥምቀትን በሚመለከት «ሴት በሰማንያ ወንድ በአርባ ቀን ይጠመቁ» የሚል በወንጌል አታገኙም ። ምናልባት በዘሌዋውያን ምዕራፍ 12 ድሮ በብሉይ ኪዳን ሊባረኩ ሲሉ ሴት በሰማንያ ቀን ወንድ በአርባ ቀን ወደ ቤተ መቅደስ ይሄዱ ነበር ትሉ ይሆናል ። ይህማ አልፏል! ቀርቷል ! ተብሏል ። በእርግጥ ግን እንደ መነሻ ማምጣት ይቻላል ። ግን ሴትዋ በሰማንያ ፤ ወንዱ በአርባ መጠመቅ እንደሚገባው የተወሰነው በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ነው ። ለማስታወስ ያህል በጥላነት ያገለገሉ አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ሥርዓቶች በተመለከተ ለንጽጽር ካልሆነ በስተቀር ለክርስትና እምነታችን መረጃ ሆነው ሊጠቀሱ አይችሉም ። ሆኖም ይህ የሕፃናት ጥምቀት የተወሰነው በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ነው ። ለምሳሌ ሴት ልጅ ሰማንያ ቀን ወንዱም አርባ ቀን ሳይሞላቸው ሕፃናቱ ቢታመሙ አስቀድመው መጠመቅ ይችላሉ ። ለምን ቢባል መጠመቅ የግድ ስለሆነና የወላጆች ኃላፊነትም ስለሆነ ነው ። ተወልደው በአሥረኛው ወይም በአሥራ አምስተኛው ወይም በሃያኛው ቀን ቢታመሙ ፤ ሕመሙ ለሞት የሚያደርስ ከሆነ ቶሎ መጠመቅ ይችላሉ ።

በሌላው መልኩ በልዩ ልዩ ችግር ምክንያት ቀኑ ቢያልፍ «ሰማንያ አርባ ቀን አልፎአልና መጠመቅ አትችልም » አይባልም ። ለምን ቢባል ጥምቀት በአብ ፥ በወልድ ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም የሚፈጸም ስለሆነ ነው ።

በአጭሩ በቀኖና ያገኘናቸውን ሀብቶች ላይተን ማወቅ አለብን ። በቀኖና ያሉትን ነገሮች ስንጠይቅ መጽሐፍ ቅዱስን በማገላበጥ ቀጥተኛ መልስ ማግኘት

አንችልም ። ለነገሩ አባቶቻችን ስለማናቸውም ጉዳይ ቀኖና ሲቀንኑ መጽሐፍ ቅዱስን መነሻ አድርገው ነው። እነሱ የሚወስኑት ፣ ስንት ነው ? እንዴት ? ወይም መቼ ? የሚለውን ነው ። አሁን ደግሞ የዶግማ አላማ ምን እንደሆነ በመጠኑ እንዳስሳለን ።

የዶግማ ዓላማ

«መዳንም በሌላ በማንም የለም ፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና» (ሐዋ 4 ፥ 12) ።

«በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን ፤ አንተና ቤተሰቦችህም ትድናላችሁ ።» (ሐዋ 16 ፥ 31) ። በዚህ ቅዱስ ቃል መሠረት ፥ የእግዚአብሔር አንድነቱ ሦስትነቱ ፥ የኢየሱስ ክርስቶስ የአዳኝነቱ ትምህርትም ዶግማ ይባላል ።

ዶግማ የማይጨመርበት ፥ የማይቀነስበት ፥ ለዘላለም ጸንቶ የሚኖር ነው ። ማጽደቅና መኮነን የሚችል ፣ የማይለወጥና የማይሻሻልም ነው ። በመሆኑም «እግዚአብሔር የለም ፣ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስን አናምንም ፤ የኢየሱስ ክርስቶስ ስም አያድንም» የሚል ፣ ከዶ ለማስካድ የሚያስገድድ ኃይል ቢነሣ የእውነተኛ ክርስቲያን ውሳኔና ምርጫ ሞት ብቻ ነው ። «እስከ ሞት ድረስ የታመንክ ሁን ፥ የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ» ይላልና ። (ራእ 2 ፥ 10) ።

ስለዚህ ጽድቅና ኩነኔ ፣ ሕይወትና ሞት በዶግማ ነውና በእምነታችን እስከሞት ድረስ የጸናን ፥ የበረታን ፥ በጸሎት የተጋን ፣ በእግዚአብሔር ቃል የታነጽን መሆን ይኖርብናል ። እግዚአብሔር ለዚያ ያብቃን ።

ተደጋግሞ እንደተገለጸው ዶግማን እግዚአብሔር ሠራው ፤ ቀኖና ግን በሲኖዶስ የሚሠራ ነው ። በትጋት የሚንቀሳቀስ ሲኖዶስ ካለና ምእመናን ወንጌልን ከተማሩ ፤ቀኖና ትውልድ ባደገ ቍጥር አብሮ ካደገ ፣ ከተተኪው ትውልድ ጋር በአግባቡ ከተዋሐደ ቢጨመር እንጂ አይቀነስም ። ምክንያቱም ቀኖና ምንም እንኳን በጽድቅና በኩነኔ ውስጥ ባይገባም ፤ በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ያለውን ፍቅር የሚገልጽ መንፈሳዊ በረከት መንፈሳዊ ኃይል ነው ። ቀኖና በሌላ በኩል ለወንጌል ወይም ለዶግማ ማግኔት ነው ። ለምሳሌ ፣ የጥምቀት በዓልን በቀኖና ያገኘነው ነው ። ቁጥሩ የበዛ ሕዝብ የጥምቀት በዓል ለማክበር ብሎ ይሰበሰባል ። ስለ በዓሉ ምንም ግንዛቤ የሌለው ሰውም ያከብራል፤ በዚህ አጋጣሚ በቀኖና ምክንያት የተሰበሰበው ሕዝብ ከዶግማ ጋር ይገናኛል ። የኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት የታወቀው በዶግማ ነው ። ለምሳሌ ፣ የቅዱስ ሚካኤል ወይም የቅዱስ ገብርኤል በዓል ይከበራል ፤ ታቦት ይወጣል ሲባል ሕዝቡ ይመጣል ፣ ሲመጣ ከዶግማ ጋር ይገናኛል ፤ ማለትም ትምህርተ

ሃይማኖትን ይማራል ። በአጠቃላይ በቀኖና ሥርዓት ባገኘናቸው ነገሮች ሕዝቡ ይሰበሰባል ፤ ሕዝቡ ሲሰበሰብ ሁልጊዜ በሚሰጠው ትምህርት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፣ የባሕርይ አባቱ እግዚአብሔር አብ ፣ የባሕርይ ሕይወቱ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አንድነት ሦስትነት ይታወቃል ። ሕዝቡ ሲሰበሰብ ባራኪው እራሱ እግዚአብሔር ነው ፣ የሚመለከው እርሱ ነው ፤ የሚሰገድለትም ለእርሱ ነው ፤ ስለዚህ እኛ አርቶዶክሳውያን የዳንነው በክርስቶስ ኢየሱስ እንጂ በሌላ አይደለም ። ሌሎች አማልክትም የሉንም ። ስለዚህ «በላይ በሰማይ ፥ በታች በምድር ፣ መዳን በሌላ በማንም የለም» ፤ በርሱ በወልደ ማርያም ፣ በወልደ እግዚአብሔር ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ነው የሚለውን ይዘን ነው እስካሁን ድረስ አለን ። ይሄ ቤተ ክርስቲያን እስካሁን ድረስ ያስገኘችልን የበረከታችን ሀብት ነው ። ከዚህ የወጣ ዶግማ የለንም ። ከዚህ የወጣ ሃይማኖት የለንም ። ከዚህ የወጣ እምነት የለንም ። ስለዚህ ሥርዓትን ከዶግማ ጋር እየቀላቀሉ በሚጠይቁ አላዋቂ ሰዎች ምክንያት አእምሮአችሁ እየተወናበደ ወደ ቀኝም ወደ ግራም አትበሉ አንበል ። መዳን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው ።

በቀኖና ውስጥ ያለውን ስናከብር ዶግማውን መርሳት የለብንም ። ለምሳሌ ጫማ ማውለቅ የሚመደበው ከቀኖና ነው ። አዲስ ኪዳን የምትለን ቂም ይዘህ አትግባ ነው ። ወደ ቤተ ክርስቲያን መባ ይዘህ ስትመጣ ፣ «ወደ መቅደስ ስትገባ ቅር ያሰኘህ ወይም ያሰኘኸው ወንድምህ ትዝ ቢልህ ፣ መባውን መድረኩ ላይ አስቀምጠህ ተመልሰህ ሂደህ ከእሱ ጋር ታርቀህ ከዚያ በኋላ መባህን ይዘህ ግባ ፣ ምሕረት ታገኛለህ ፣ ይቅርታ ታገኛለህ» (ማቴ 5 ፥ 23-24) የሚለውን የማይረሳውን አትርሱ ። ይህ ዶግማ ነው ። ከሚስትህ ጋር ተቀያይመህ ፣ በባልሽ ቂም ይዘሽ ፣ ከባልንጀራህ ጋር ቂም ይዘህ ፣ ወይም ልባችን የቂም ከረጢት ፣ የበቀል ከረጢት ሆኖ ወደ ቤተ ክርስቲያን ከገባን ፣ ጫማ በማውለቅ ብቻ እግዚአብሔርን ያከበርን እንዳይመስለን ። ይህንን ሐዋርያት የነገሩን ባንናገር ኃጢአቱ በእኛ በካህናት ላይ ነው ። የእግዚአብሔርን ሕግ ማፍረስ ነው ። ይህንን ኣታድርጉ ካሉን አለማድረግ ነው ። ስለዚህ አባቶቻችን ያሉንን በጫማ ብቻ እንዳንሸፍነው ፣ ትኩረቱ ጫማ ማውለቅ ላይ ብቻ እንዳይመስለን ያስፈልጋል።

ለምሳሌ በቅዳሴያችን መግቢያ ላይ «ሃሌ ሉያ እመ ቦ ብእሲ እምእመናን ዘቦአ ቤተ ክርስቲያን በጊዜ ቅዳሴ ፣ ወኢሰምዐ መጻሕፍተ ቅዱሳተ ወኢተአገሠ እስከ ይፈጽሙ ጸሎተ ቅዳሴ ወኢተመጠወ እም ቍርባን ይሰደድ እም ቤተ ክርስቲያን እስመ አማሰነ ሕገ እግዚአብሔር ፣ ወእስተሐቀረ ቁመተ ቅድመ ንጉሥ ሰማያዊ ንጉሠ ሥጋ ወመንፈስ ከመዝ መሐሩነ ሐዋርያት በአብጥሊሶሙ»

ብለን ስናዜም ዜማው ደስ ይላል። ትርጉሙ «ሃሌ ሉያ ፤ በቅዳሴ ጊዜ ከምእመናን ወገን ወደ ቤተ ክርስቲያን የገባ ሰው ቢኖር ፥ ቅዱሳት መጻሕፍትን ሰምቶ የቅዳሴውን ጸሎት እስኪጨርሱ ባይታገሥ ፤ ከቍርባንም ባይቀበል ፥ ከቤተ ክርስቲያን ይለይ ። የእግዚአብሔርን ሕግ አፍርሷልና ። የነፍስና የሥጋ ንጉሥ በሚሆን በሰማያዊ ንጉሥ ፊት መቆምንም አቃሏልና ። ሐዋርያት በሲኖዶሳቸው እንዲህ አስተማሩን» ነው የሚለው ።

ለምን ቢባል የእግዚአብሔርን የአዲስ ኪዳን ሕግ አቃሏልና ፤ ከወንድሙና ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ፍቅር ዘንግቷልና ። አንድ የተዋሕዶ አማኝ አግዚአብሔርን በፍጹም ልቡ ፥ በፍጹም ሐሳቡ በፍጹም ነፍሱ ቢወድድ ፤ ያ ሰው የሞተለትን አምላኩን ኢየሱስ ክርስቶስን ቢወድድ ፤ ወንድሙን እንደ ራሱ ቢወድድ ፤ ከኃጢአት በተቻለ መጠን ቢርቅ ፥ እንዳይቄርብ የሚከለከለው የለም ። ባል ሚስቱን ቢያምን ፤ ሚስት ባልዋን ብታምን ፤ ሁለቱ ክርስቶስን ቢያምኑ እንዳይቄርቡ የሚከለክላቸው ምንም ነገር የለም ። ትእዛዙ የሚያስገዝበን የማይቄርብ ሰው ቃለ ወንጌሉን ፤ ሕገ እግዚአብሔርን አቃሏልና በቅዳሴ ጊዜ አይግባ የሚል መልዕክት ነው ። በመሆኑም ከላይ የተገለጸውን ትእዛዝ አለመፈጸም ስህተት መሆኑን አውቆና ተረድቶ ራስን ለንስሐ ሕይወት አዘጋጅቶ መኖር ያስፈልጋል።

ጫማ ማውለቅ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ያገኘነው እንደሆነ ተጠቅሷል ። ለምሳሌ የግብፅ አርቶዶክሶች ከነጫማቸው ይገባሉ ፤ ቂም ይዘው እንዳይገቡ ግን ዘወትር ትምህርት ይሰጣል ። አንድ ጊዜ አንዲት እናት የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ገብተው ስላዩት ምን አሉኝ መሰላችሁ ። እኚህ እናት ቅዱስ ቍርባንን እጅግ ይፈሩታል። በዕድሜ የገፉ ናቸው ። « ይገርማል ፤ ከዚያ ከግብፆች ቤተ ክርስቲያን ሄጀ ዓይኔ ጉድ አይቶ መጣሁ ። እንዲያው እኔ ደግሞ እነርሱ ክርስቲያኖች ናቸው ሲባል እውነት መስሎኝ ነበር» አሉ ። እኔም "እንዴት"? አልኳቸው ። «ቄሱ፣ ዲያቆኑ ሁሉም ከነጫማቸው ጥልቅ ጥልቅ ይላሉ ። ከነጫማቸው በመግባታቸው መቅደሱን ተጫወቱበት» አሉኝ ። እኔም «በጣም ጥሩ ፤ ግን በቍርባን ጊዜ አዩአቸው ? እንዴት ናቸው ? ሕፃናት ብቻ ነበር የሚቄርቡት ? ወይስ ትልልቆችም ይቄርባሉ ?» አልኳቸው ፤ እርሳቸውም ሲመልሱ «የሚገርም ነው ፤ ሳይቄርብ የቀረ አንድም የለም ። አሁን ያ ሁሉ እውነት ንጹሕ ሆኖ ነው የሚቆርበው?» በማለት ስለ ቄረቡ ግብፃውያኑን ወነጀሏቸው ። እሳቸው ግን ሳይቄርቡ ተመለሱ ። ወገኖቼ ! ይሄኔ እነዚያ ግብፃውያን እኚህን ሴትዮ ምን የሚሏቸው ይመስላችኋል ? «ምናልባት ይህች

ሴት ኢትዮጵያዊት ፕሮቴስታንት ብትሆን ነው እንጂ ፤ ኢትዮጵያዊት አርቶዶክስ ብትሆን ኖሮ ትቄርብ ነበር ነው» የሚሏቸው ።

ስለዚህ እኚህ ኢትዮጵያዊት እናት ስለ ሃይማኖት ያላቸው ግንዛቤ የተስተካከለ አይደለም ። ለእርሳቸው ሃይማኖት ማለት እግዚአብሔርን ለማክበር ያለጫማ መግባት ብቻ ነው ። ቂም ይዞ መግባት ፥ የማይቆርብ ይውጣ እየተባለ መግባታቸው ፥ ለእርሳቸው ኃጢአት አይደለም ። ለምን ቢባል የዶግማንና የቀኖናን ልዩነት ባለማወቃቸው ነው ።

ዳግመኛ አንድ መሪጌታ ደብተራ ፤ ከመነኮሳት ጋር ግብፅ ለትምህርት ይሄዳል ፤ ሁል ጊዜ ያስቀድሳል ፥ ግን ሳይቆርብ ይመለሳል ፤ መነኮሳቱ ይቄርባሉ ። አንዲት ከእናቷ ጋር የምታስቀድስ ወጣት ያንን ደብተራ ሁልጊዜ ታያለች ። አንድ ቀን እናቷን «እማዬ ይሄ ሰው መቼ ነው የሚጠመቀው?» አለቻት ። ወጣቷ እንዲህ ያለችበት ምክንያት በግብፆች ዘንድ ሳይቄርብ የሚወጣ ያልተጠመቀ ብቻ ነውና ። ይህን ታሪክ የነገሩኝ ሰው እስከ አሁን ድረስ በሕይወት አሉ አልሞቱም ።

አስተውሉ! ይህንን ትምህርት ሳስተምር «የኦርቶዶክስ ካህን ሆኖ ከነጫማችሁ ግቡ አለ» ብለው በሃሰት የሚያወሩ አሉ። ከነጫማ ግቡ ብዬ የማውጀው እኔ ሲኖዶስ ነኝ ? ለምንስ ነው ግቡ የምለው? እኔ ለማስተማር የምፈልገው እምነታችንን አውቀን በፍቅር ከልብ እንከተል ነው::

በወንድሞች ከሳሽነት «ሃይማኖታችንን አቃለለ ፤ ሃይማኖታችንን አፈረሰ» መባሌ ብዙም ለእኔ ግድ አይሰጠኝም። እዚህ ላይም ያነሳሁት የማይጠቅማችሁን የሚናገሩ ፤ አባቶቻችሁን የሚወነጅሉ ከሳሾች ስለሚኖሩ ፤ እውነት መስሏችሁ እንዳትደናገሩ ለማሳወቅ ያህል እንጂ ለሌላ ጉዳይ አይደለም ። እኔ እንደሆንኩ ባለፈው በታመምኩ ጊዜ ልሞት እችል ነበር ። ለምን እንደሰነበትኩ አላውቅም ፤ የተባለው ቢባል ግድ የለኝም ። ደግሞ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ማንም ሰው ጠርቶኝ ሳይሆን ፤ ሳላውቀው እራሱ ባለቤቱ ነውና የጠራኝ እስካለሁ ድረስ ቤተ ክርስቲያንን የሚጠቅማትን ከመናገር አልቆጠብም ። ለቤተ ክርስቲያናችን እድገት እና ለምዕመናን ክርስቲያናዊ ሕይወት መታነጽ እንቅፋት የሆነውን አሉባልታና ውዥንብር መንዛት የተቻለው ምእመናን ከመጀመሪያው ስለ ዶግማ እና ስለ ቀኖና ትምህርት ለይተው ስለማያውቁ ነው።

በተጨማሪም ደግሞ «ሴት በወር አበባዋ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ትግባ ብሏል» ተብሎ የሃሰት ወሬ ተናፍሷል ። እንደ እውነቱ ከሆነ እኔ «ሴት በወር አበባዋ ጊዜ

ቤተ ክርስቲያን ትግባ» ብዬ አላስተማርኩም ። ነገር ግን «የወር አበባ ጊዜን ‹መርገም ነው አትበሉ› ብያለሁ ። መርገም አይባልም ። እንኳን የእሷ ፈሳሽ ፣ የዲያበሎስ ግዛት መርገም ፣ የዘላለም ሞት መርገም ፣ ያ የውርስ ኃጢአት መርገም ፣ በደመ ክርስቶስ ተደምስሷል ። «ወሰጠጠ መጽሐፈ ዕዳሆሙ ለአዳም ወለሔዋን ፥ ወረሰዮሙ አግአዝያነ ዘተወልደ ለነ በሀገረ ዳዊት መድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ» "በዳዊት ሀገር የተወለደልን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የአዳምና የሔዋንን የዕዳ ደብዳቤአቸውን ቀደደ ፣ ነጻም አወጣቸው» ተብሎ ተጽፏል ። (የሰኞ ውዳሴ ማርያም)።

«ሠረቀ በሥጋ እም ድንግል ዘእንበለ ዘርዐ ብእሲ ወኢድኃነነ ፣ ለሔዋን እንተ አስሐታ ከይሲ ፈትሐ ለዕሌሃ እግዚአብሔር እንዘ ይብል ብዙኃ አበዝኖ ለሕማምኪ ፥ ወለፃዕርኪ ፣ ሠምረ ልቡ ኀበ ፍቅረ ሰብእ ወአግአዘ»

«ከድንግል ያለ ወንድ ዘር በሥጋ ተወለደ ፣ ተወልዶም አዳነን ። ከይሲ ያሳታት ሔዋንን እግዚአብሔር ምጥሽን ጻዕርሺን አበዛዋለሁ ብሎ ፈረደባት ፣ ሰውን ወደደና ነጻ አደረጋት ።» ነው የሚለው (የሰኞ ውዳሴ ማርያም) ።

በሐዲስ ኪዳን ሴት ልጅ የእግዚአብሔር ጽላት ፣ ታቦትና ቤተ መቅደስ ሆናለች (1ቆሮ. 6 ፥ 19-20) ፣ (1ቆሮ. 3 ፥ 16) ። ቤተ መቅደስነቷ ደግሞ በየወሩ የሚረከስ አይደለም ይልቁንም በየቀኑ ሊያረክሳት የሚችለው ኃጢአት ከሠራች ነው ። እሷ ብቻ ሳትሆን ሁላችንም የእግዚአብሔር ጽላት ፣ ታቦትና ቤተ መቅደስ ሆነናል። እኛን ሁላችንንም በየደቂቃው የሚያረክሰን የምንሠራው ኃጢአት ነው ።

አባቶቻችን በሲኖዶስና በፍትሐ ነገሥት ፣ ሴቷን በወር አበባዋ ጊዜ ወደ በቤተ ክርስቲያን እንዳትገባ ብለው ከልከለዋል ። በፍትሐ ነገሥት የሴትን የወር አበባ ስሙን እንኳን ሲጠሩት በቋንቋ አሻሽለው «የግዳጇ ወራት ሳይፈጸም» ብለው ነው ያስቀመጡት ። (ዘሌዋውያን 15 ፥ 19-27)።

በብሉይ ኪዳን የሴቶች ጉዳይ እንዲያውም በመጨረሻ ላይ ነው የተገለጸው ። በዘሌዋውያን እንደተጻፈው ከሆነ ማንም ፈሳሽ ያለበት ሰው ፣ ለምጻም ሰው ፣ ሕልመ ሌሊት የመታው ሰው ፣ ቤተ መቅደስ እንዳይገባ ይከለክላል ። (ዘሌ 15 ፥ 2-18) በተጨማሪም የተሰለበ ቄስ እንኳን ወደ መቅደስ እንዳይገባ ታዝዟል ።

አባቶቻችን የአሪትን ሕግ እንደ ታሪክ አድርገው እንዳትገባ ብለው የከለከሉበት ምክንያት እንደምታውቁት ፥ አብዛኛው የእኛ ሕዝብ ድሃ ከመሆኑ የተነሣ በሙሴ ዘመን ከነበረው ሕዝብ በአኗኗር ቢያንስ እንጂ የተሻለ ስላልሆነ የንጽሕና አያያዙ በግድ መጠበቅ አለበት ብለው ነው ። ሥርዓቱ ለእሷም ፣ ለሞራሏም ፣ ለእግዚአብሔር ቤትም ክብር ስለሆነ ልትገባ አይገባም ። ምክንያቱም የተፈጥሮ ግዳጅዋን ልትቋጣጠረው አትችልም ፤ ከአቅሟ በላይ ነውና ።

እኔም ሳስተምር ያልኩት «ሴት በወር አበባዋ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ትግባ» አይደለም ። እኔ ትግባ ብዬ የማስተምረው ቅዱስ ሲኖዶስ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ፍትሐ ነገሥት ላይ ያለውን በሙሉ ሥልጣኑ አንሥቶ «አንሥተናል አስተምር» ሲለኝ ብቻ ነው ። ያን ጊዜ ቀኖር አንድ አስተማሪ እሆናለሁ ። እስከዚያ ጊዜ ድረስ የማስተምረው በወር አበባዋ ጊዜ ቤተ መቅደስ እንድትገባ ሳይሆን በዚያን ጊዜ ረከሳለች እንዳትሉ ፣ መርገም ነው እንዳትሉ ነው ።

በተጨማሪም አንዳንድ ወንጌሉ ያልገባችውና ግራ የተጋቡ ሴቶች በወር አበባቸው ወቅት መጽሐፍ ቅዱስን የማይነኩ አሉ ፤ የሚጸልዩበትን ውዳሴ ማርያም የሚያስቀምጡ አሉ ፤ መስቀል የማይሳለሙ አሉ ፤ ለምን ቢባል ረከሰናል ብለው ስለሚያምኑ ነው ። ነገር ግን በወር አበባቸው ላይ ባልሆኑባቸው ጊዜያት ቂም ይዘው ይሳለማሉ ፣ ይጸልያሉ ። ኃጢአት እየሠሩ መጽሐፍ ቅዱስን እንደ ጋዜጣ ያገላብጣሉ ። እኅቶች ! የሚያረክስ ኃጢአት ነው ፤ በወር አበባ ምክንያት የሚረከስ ሕይወት የላችሁም ። ከርስቶስ ደሙን ያፈሰሰላችሁ በየወሩ እንድትረክሱ አይደለም ። በእሱ የዳናችሁት በየወሩ እንድትረክሱ አይደለም ። ማንም እናንተን «ርኩሳን ናችሁ» ማለት አይችልም ። አንዱ አንዷን «ርኩስት ናት ፥ በዚህ ጊዜ ትረክሳለች» ብሎ እንዳይናገር።

ባለሁበት አካባቢ ሰዎች እንዳወሩኝ ፣ አንድ ጊዜ አንድ ሊቅ ካህን ልጆቻቸውን ሊጠይቁ ከኢትዮጵያ ይመጣሉ ። አንዲት ሴት ካህኑን አግኝታ ሲጨዋወቱ «አንቱ አባቴ እዚህ አሜሪካ ያሉ አንዳንድ መነኮሳት ምነው ዘመናውያን እንሁን እያሉ አስቸገሩን?» ብለው ይጠይቃሉ ። ከዚያም «ከነጫማችሁ ወደ ቤተ ክርስቲያን ግቡ ፣ ሴትም በወር አበባዋ ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን መግባት ትችላለች ፣ ኃጢአት የለባትም» እያሉ ያስተምራሉ ትላቸዋለች ። ካህኑም ነገሩ ገባቸውና «ለመሆኑ እንቺ ስታስቢው መግባት ይቻላል እንዴ ?» ብለው እንደ ገና እርሷን መልሰው ይጠይቃሉ ። እርሷም ቆጣ ብላ «እንዴ እንዴት ይቻላል ? ዘሌዋውያን 15 ላይ እንዲህ እንዲህ ይል የለም ? ... በሌላ ቦታም እንዲህ እንዲህ ይላል» ትላቸዋለች ፣ የተሻረውን የአሪት ሕግ እየጠቀሰች ። ካህኑ ትክክለኛውን ቢነግሯት እንደማትቀበል ፣ ለማስረዳት ቢሞክሩም አብራ ተጨማሪ ወንጀለኛ እንደምታደርጋቸው ስለታወቃቸው በውስጠ ወይራ አነጋገር «ልጄ እንቺማ መጽሐፍ ቅዱስን በልተሽው የለምን ?

ለመሆኑ ትዳር መሥርተሻል ? ይሏታል ። «አይ ! ባልስ ገና አላገባሁም ፤ ይጸልዩልኝ አባቴ ፤ እዚህ ሀገር ትዳር ዋዛ አይደለም» ትላቸዋለች ። እርሳቸውም «አዎ እንዲያው ጥሩ አድረገሽ ይዘሽዋል ፤ የቀረችሽ ነገር ብትኖር እንግዲህ ጎጆዋ ናት» በይ በርቺ እጸልያለሁ ብለዋት ተለያዩ ።

ካህኑ ያስተላለፉት መልእክት፤በአሪቱ ሕግ ሴት በወር አበባዋ ጊዜ ለሰባት ቀናት ለብቻዋ ከሰው ተለይታ በጎጆ መቆየት አለባት የሚለውን ነው። ስለዚህም ነበር በውስጠ ወይራ አነጋገር «ልጄ በጣም ጥሩ ነው የቀረችሽ ጎጆዋ ናት» ያሏት ።

እንደዚህ በክርስቶስ ደም የተባረከውን ፤ በክርስቶስ ደም የተቀደሰውን እንደገና «መርገም አለ» እያለ ፥ ያን የቀረውን የኦሪት ቃል ከወንጌል ጋር እየቀላቀለ የሚያስተምራችሁ ቢኖር የተረገመ ይሁን ። ቅዱስ ጳውሎስ «ከወንጌል የተለየ ሌላ ወንጌል ቢያስተምራችሁ የተረገመ ይሁን» ብሏልና ። (ገላ ፩ ፥ 6-9) ።

በውግዘት ውስጥ እንድትመላለሱ አልፈልግም ። አባቶቻችን ያስተማሩንንና ወንጌል የሚለውን በትክክል አስቀምጬዋለሁ ። የሚያረክስ ኃጢአት ብቻ ነው ።

የማይበሉ እንስሳትና ፤ አእዋፍን ጉዳይ አስመልክቶ እኔ «አሳማ ብሉ» ፤ «አሞራ ብሉም» አላልኩም ። ሆኖም «ኃጢአት ነው አትበሉ ፤ ያረከሳል ብላችሁ አትናገሩ» ነው ያልኩት ። በኦሪት ዘፍጥረት «እግዚአብሔርም የፈጠረውን ሁሉ ተመለከተ ፤ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ» ተብሎ እንደ ተጻፈ ። (ዘፍ ፩ ፥ 31) ። እግዚአብሔር ኃጢአተኛ የተገረመ ርኩስ ፍጥረት አልፈጠረምና ነው ። እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ መልካም ዓላማ አለው ። ሁሉም መልካም ነበረ ፤ ነገር ግን አዳም በኃጢአት ምክንያት ተረገመ ። በአዳም ምክንያት ምድር ተረገመች ። ስትረገም አንዱን ርኩስ ፥ አንዱን ርጉም ማለት ተቻለ ። ነገር ግን የተረገመችን ምድር ፥ የተረገመን አዳም እንደ ገና በአዲስ ተፈጥሮ መፍጠር የወደደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፤ ቅዱስ ሥጋው በዕለተ ዓርብ በመልአልተ መስቀል በተቆረሰ ጊዜ ፤ ፍጹም አምላክ ሲሆን ፍጹም ሰው የሆነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለኛ በሞተ ጊዜ ፤ የእኛ መርገም ተወገደ ፤ የተረገመችዋ ምድር ተባረከች ፤ የረከሰችው ምድር ተቀደሰች ፤ ያረከሳሉ ፥ ተረግመዋል የተባሉ ፍጥረቶች ሁሉ አዲስ ፍጥረት ሆኑ ። ያ ማለት ምንድነው? ከደመ ክርስቶስ መፍሰስ በኋላ እግዚአብሔር እንደገና ፍጥረትን ተመለከተ ። «እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ መልካም ነውና ፥ ከምስጋናም ጋር ቢቀበሉት የሚጣል ምንም የለም» እንዳለ ሐዋርያው ጳውሎስ (፩ጢሞ 4 ፥ 4) ።

በተጨማሪም በመጽሐፍ ቅዱስ በአዲስ ኪዳኑ ከፍል ፤ ፍትሐ ነገሥቱም ጭምር ተመሳሳይ መልእክት ያስተላልፋሉ ። (የሐዋ 10 ። ሮሜ 14 ። 1 ቆሮ 10 ። ቲቶ 1) ።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ማንበብ ባትችሉ እንኳን ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ ፤ እኚያ ጀግና ሊቀ ጳጳስ የጻፉትን «የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ» የተባለውን መጽሐፍ ገጽ 16 ከዚያም ወደ መጨረሻ አካባቢ «ኢኮሚኒዝም» በሚል ርእስ በተባበሩት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ስላለው ሁኔታ የጻፉትን ፤ በአፄ ገላውዴዎስ ጊዜ ምዕራባውያን የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን በአሳማ አለመብላት ምክንያት በከሰሱ ጊዜ አባቶቻችን ሊቃውንት የሰጡትን መልስ አንብቡት ። *(በዚህ መጽሐፍ ከገጽ 74 ጀምሮ የተያያዘውን ቅጂ ይመልከቱ)*

አሁንም እኔ «ያገኛችሁትን ብሉ» አይደለም እያልኩ ያለሁት ፤ ነገር ግን «በደመ ክርስቶስ የተቀደሰውን ነገር ርኩስ ነው አትበሉ ፤ በደመ ክርስቶስ የተባረከውን እርጉም ነው አትበሉ» ነው የምላችሁ ። ለምን ? ቢሉ ፤ ዛሬ እነዚህን የማይበሉ እንስሳትን ፤ አእዋፍን እርኩሳን ናቸው ብለው የሚያምኑ አይሁድ ናቸው እንጂ ክርስቲያኖች አይደሉምና ። ስለዚህ እኔ ማለት የፈለኩት ልጆቻችሁ ትምህርት ቤት ገብተው ስለሚመገቡት ምግብ ፤ ምን እንደሚባሉ እንድታውቁት ነው ። መቼም ልጆቻችሁን የአሳማ ሥጋ ብሉ እንደማትሉ እርግጠኛ ነኝ ። ስለዚህ ስትጠየቁ ልጄ አሳማ አይበላም ነው የምትሉት ። ቅጽ (ፎርም) ስትሞሉስ ምክንያት አድርጋችሁ የምትጠቀሙት ሃይማኖት «Religion» ነው ወይስ ባሕል «Culture» ነው ብላችሁ ነው? "Religion" ነው ካላችሁ ሃይማኖት ነው ፤ መብላት ያረከሳል ማለታችሁ ነው ። ደግሞ ያረከሳል ብለው የሚያምኑ አይሁድ ናቸው ። የዓለም ክርስቲያኖች ያረከሳል አይሉም ። በተለይም አርቶዶክስ ያረከሳል አትልም ። ነገር ግን የምትሞሉት ፎርም ቢኖር "Culture" ነው ፤ «ባሕላችን ስላልሆነ ነው» ብላችሁ ማስረዳት ትችላላችሁ ። አሜሪካውያን ውሻ አይበሉም ። ነጮች ውሻን የማይመገቡት የኦሪትን ሕግ አክብረው እንዲሁም በሃይማኖታቸው ሳይሆን በባሕላቸው ያልተለመደ ስለሆነ ነው ። አሜሪካኖች እባብ አይበሉም ፤ የማይበሉት ከሃይማኖት አንጻር አይደለም ፤ ከባሕልና ልምዳቸው አንጻር ነው ።

ነጮች ባሕላቸውን ወጋቸውን ሲያከብሩ ፤ ኢትዮጵውያን በሃይማኖታችሁ የምታፍሩበት ምን ምክንያት አሌ? በባሕላችሁ የምታፍሩበት ምን አለ ? ሥርዓታችን ባመጣው ልማድ የምናፍርበት ምን ነገር አለ ? እኛ ኢትዮጵያውያን የብሉይ ኪዳን አማኞች ስለ ነበርን በብሉይ ኪዳን የጠላናቸውን እንስሳትን ፥

አእዋፍን ፥ መብላት ስለማንችል አንበላም ። ደግሞ ባለመብላታችን የማይበላ አይብላ ተብሏል ። ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ «በራሱ ርኩስ የሆነ ነገር እንደሌለ በጌታ በኢየሱስ ሆኜ አውቄአለሁ ተረድቻለሁም ፤ ነገር ግን ምንም ርኩስ እንዲሆን ለሚቈጥር ለእርሱ ርኩስ ነው» ብሏል ። (ሮሜ 14 ፥ 13-23) ። ስለዚህ የሚበላው ተፈቅዶለታል ፤ የማይበላውም አልበላም ካለ መብት አለው ።

በደርግ ጊዜ አንድ ካድሬ ለስድስት ወር ኮርስ ወደ አንድ አፍሪካ ሀገር ተላከ አሉ ። እግዚአብሔር የለም ብሎ የሚያስተምር ሰው ነው ። ከስብሰባ በኋላ ምግብ ቀረበለት ። እየጣመው ጣቱን እስኪልስ ድረስ ግጥም አድርጎ ሲበላ ሰነበተ ። በኋላ አንዱን አሳላፊ «ይሄ ከምን ምግብ ቢሠራ ነው በሀገራችን በኢትዮጵያ እንዲህ ያለ የሚጣፍጥ ምግብ በልቼ አላውቅም ?» ይለዋል ። ነገር ግን በቋንቋ አልተግባቡም ስለዚህ ያ አሳላፊው ሥዕሉን አመጣለት ። ለካ የበላው ጉበና ነው ። ጉበና ሁለት ምላስ ያለው ፤ እባብ የሚመስል ፤ በሆዱ የሚሳብ ፤ አጋራ ተብሎም የሚታወቅ አውሬ ነው ። ያ ኢትዮጵያዊ ይህን ሲሰማ የበላውን ነገር ሁሉ ያስወጣል ፤ ታምሞ ሰባት ቀንም ሆስፒታል ይተኛል ። ለምን ? ኢትዮጵያዊ ስለ ሆነ አሳማ ፥ ውሻ ፥ አጋራ ፥ እባብ መብላት ባሕሉ ስለማይፈቅድለትና ስላለመደው ነው ።

ግን የማንበላው ከሃይማኖት አንጻር ነው አትበሉ ። ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 23ን ተመለከቱ ፤ ከላይ የተጠቀሱትን መጻሕፍት ተመልከቱ ። «ከሃይማኖት የተነሣ ነው ፤ ሃይማኖታችን ስለሚከለክል ነው» አትበሉ ። ቤተ ክርስቲያናችንን አታሰድቧት ፤ እምነቷ ክርስትና ነው ። ባሕላችንን እንድናከብር ግን አባቶቻችንና ታሪካችን ግድ ይለናል ። *(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 23 በገጽ 82 ላይ ቀርቧልና ይመልከቱት)*

አሜሪካ ሀገር ውስጥ አንድ ነጭ አሜሪካዊ ኮርያዊ ጎረቤት ነበረው ። ያ ኮርያዊ ጎረቤት ግልገል ውሾች ያመጣል ። ከሳምንት በኋላ እነዚያ ውሾች የሉም ። በኋላ ይሄ ነጭ ጎረቤቱ ኮርያዊው ውሻ እንደሚበላ ገባው ። «መከሰስ አለብኝ ፤ ውሻ የሚበላ የእሱ ጎረቤት ሆኜ አልኖርም» ብሎ ይናደድና ጠበቃ ያማክራል ። ጠበቃው «ኮሪያዊ ውሻ መብላት ባሕሉ ነው ፤ ውሻ በመብላቱ በፍርድ ቤት ልትረታው አትችልም» ብሎ ይመክረዋል ። ሕግ እንደሚፈቅድለትና ውሻ መብላት እንደማይከለክለው ስለሚያውቅ ነው ። ይልቅስ እንዲህ ብታደርግ ይሻልሃል ብሎ ሐሳብ ሰጠው ። ይኸውም «ፍቃድ (ላይሰንስ) ሳይኖረው በአካባቢያችን ውሻ በማረዱ የጤና ጥበቃ ሕግን ጥሷል እንደዚሁም የአካባቢያችንን ንጽሕና በመበከል የሰዎችን ጤና ለአደጋ

አጋልጧል » ብለህ ብትከሰሰው ትረታዋለህ አለው ። ልክ ጠበቃው እንዳለው ኮሪያዊውን ከሶት ፤ ረታ ። ኮርያዊው ከዚያ አካባቢ እንዲለቅ ስለተደረገ ተገላገለ ።

አስተውሉ !! ቤተ ክርስቲያንን አታሳፍሩ ። እንደምታሸንፉ ሁኑ እንጂ እንደምትረቱ አትሁኑ ። የአሳማ ሥጋ ለጤና ጠንቅ ይሆናል እያሉ የዓለም ሕክምና ጠበብት እየተናገሩ፤ የድሮዎች የከለከሉት ከበሽተኛነቱ የተነሣ ነው እያሉ ፤ የአሳማ ሥጋ ጠረን ይለውጣል ፤ ጤንነት ያበላሻል እየተባለ እኔ አሳማ ብሉ ብዬ እንዴት አስተምራለሁ ? ስለዚህ እናንተም ከባሕላችን ብቻ ሳይሆን ከጤንነታችንም አኳያ አሳማ አንበላም ብላችሁ ለማስረዳት ሞክሩ እንጂ ሃይማኖት ይከለክላል አትበሉ ።

ነገ ጠዋት አንዱ ፕሮቴስታንት ተነሥቶ ፤ ወንጌልን ገልበጥ ገልበጥ አድርጎ «የእናንተ ቤተ ክርስቲያን እኮ ድሮ የተወገዘን አሪት ይዛ ስለምትሄድ ፤ እናንተ ክርስቲያኖች ነን ብትሉም የብሉይ ኪዳን አሪታውያን የምትባሉት ለዚህ ነው» ብሎ አንዱን አርቶዶክሳዊ ቢከራከረው እና አርቶዶክሳዊው መልስ ቢያጣ ፤ ተሸንፎ ይህችን የመሰለች ቤተ ክርስቲያን ይህንን የመሰለ ዶክትሪን ትቶ አንደኛውን እንዳይሄድ ፤ እኛም ተረካቢ እንዳናጣ ባህልን ከቀኖና ቀኖናን ከእምነት እየለየን ትክክለኛውን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ማስረዳት መቻል አለብን ። በተለይ በውጭ ሀገር ለተወለዱና ለሚወለዱ ልጆች ስታስረዱ ሃይማኖት ሳይሆን ባሕላችን አይፈቅድም በሏቸው ። «ፈረንጅ ውሻ እንደማይበላ እኛም አንበላም» ብላችሁ መንገር ይገባል ።

የአምላካችን የእግዚአብሔር ስሙ የተመሰገነ ይሁንና በቀኖና ቤተ ክርስቲያን የምንጠቀምበት ሥርዓት ከመንፈሳዊ በረከትነት ፤ ከሃይማኖት መግለጫነት አልፎ ለእኛነታችን ምልክት ፤ ከሌላው የምንለይበት መታወቂያ ሆኖን የኖረ ነው።

እምነትና ሥርዓት ፥ ዶግማና ቀኖና ፥ ልማድና ቀኖና ፥ ወይም ዶግማና ልማድ ምን እንደሆነ ለይተን እንድናውቅ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የጨለመውን አእምሮ ያብራልን ።

ምዕራፍ ሦስት

ወንጌል በአሪት ላይ

በዚህ ርእስ ማስተማር ያስፈለገበት ምክንያት ከአጼ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ምዕራባውያን ሚሲዮኖች «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አሪታዊት እንጂ ወንጌላዊት አይደለችም» እያሉ ይከስሱበት የነበረው የመቃወሚያ ሃሳብ (አመክንዮ) ዳግም በመንጸባረቁ ነው። ይህም ተቃውሞ ተመልሶ ሊመጣ የቻለው ምሥጢር ሳያደላድሉ አባቶችን ሳይጠይቁ በቤተ ክርስቲያናችን መድረክ ላይ አናስተምራለን ብለው የተነሱ ሰዎች ፤ እኛ አሪትንና አዲስ ኪዳንን እንዳለ አንድ አድርገን እንደያዝን አስመስለው ስለሚያስተምሩ ነው ።

ስለዚህም ንግግራቸው የሚጠቅሱት ጌታ በማቴዎስ ወንጌል «አሪትና ነቢያትን ልፈጽም እንጂ ልሽር አልመጣሁም» የሚለውን ወስደው ነው ። ስለዚህ እነዚህ ምሥጢር ያላደላደሉና በቅጡ ያልተረዱ ሰዎች "እኛ የአሪቱንና የአዲሱን አንድ አድርገን የያዝን ስለሆነ ከአሪት አንድ ነገር የተቀነሰ ነገር የለም ፤ እንዳለ ይዘናል" ይላሉ ፤ ለሚጠየቁትም ጥያቄ ሲመልሱ የአሪቱን ምዕራፍና ቍጥር ብቻ ጠቅሰው ይናገራሉ ። በዚህ ምክንያት ቀድሞ ጥንት በአጼ ገላውዴዎስና ከዚያም በኋላ በነበሩት አባቶቻችን ሊቃውንት መልስ ተሰጥቶበት የምዕራባውያን ሚሲዮኖች አፍረው የተመለሱበትን ማደናገሪያ ሐሳብ እነዚህ ሰዎች ዳግመኛ ይዘው በመነሳት ቤተ ክርስቲያኗን የሚተቹ ተቃዋሚዎች እንዲበዙ ምክንያት ስለሆኑ ቤተ ክርስቲያናችንን ከመናፍቃን ለመመከት «ወንጌል በአሪት ላይ» በሚል ርእስ ማስተማር አስፈለገ ።

አዎን በትክክል እኛ ከአሪት የመጣን ክርስቲያኖች ነን ። ማለትም ክርስትናችን የተመሠረተው በአሪት ላይ ነው ። ግን የአሪት አምነት ያለን እኛ ኢትዮጵያውያን ክርስትናውን ስንቀበል ጌታ ራሱ ከአሪት ያስቀረውን ፤ ያሳለፈውን ፤ የሻረውንም በመገንዘብ ነው ። ከአሪት ያስቀረው ፥ የተወልን ፥ ያቀለለልን ፥ የሰረዘልንም አለ ። ስለዚህ እነዚያን የተወልንን ነገሮች «እነዚህን ትቶልናል ፤ ተሸሮልናል ነገር ግን ቢሻርም እኛ ዛሬ በባሕላችን እነዚህን እንጠብቃለን ፤ ሆኖም ግን የተሻረውን የምንጠብቀው እና ስናከናውነው የምንታየው በባሕል መልክ ነው እንጂ በሃይማኖት መልክ አይደለም ። በሃይማኖት መልክ የማይሆንበት ምክንያት ጌታ በደሙ ስላሳለፈው ጥላ ሆኖ አልፏል» ብለን መልስ መስጠት እንድንችል የተዘጋጀ ትምህርት ነው ።

«እኔ ኦሪትንና ነቢያትን ልፈጽም እንጂ ልሽር አልመጣሁም» የምትለውን ጥቅስ ለሁሉም ነገር በመጥቀስ ወደ ተሳሳተ ግንዛቤ እንዳንገባ መጠንቀቅ አለብን:: ለተሻረው የኦሪት ክፍል ይህችን ጥቅስ ከጠቀስን ፥ ቤተ ክርስቲያኗን አሳልፈን ለጠላት ሰጠን ማለት ነው ። በተጨማሪም ምእመናንን ማደናጋር ሲሆን ከሁሉም በላይ ደግሞ ክርስቶስ ያደረገልንን ውለታ ረሳን ማለት ነው ። ተጠያቂነቱም በመጀመሪያ ደረጃ የኛ የካህናት ነው።

ይህ እንዳይሆን ቤተ ክርስቲያናችን ኦሪትን በአራት ከፍላ ታስተምራለች (ታቀርብልናለች):: በጀግኖቹ የሊቃውንት ዘመን አባቶቻችን ጀግንነታቸውንና ፣ የቤተ ክርስቲያን ጠባቂነታቸውን በገሃድና በድፍረት ፥ በሙሉ ልብና በቆራጥነት ያስተማሩበትንና የጻፉትን ፥ አስቀምጠው ያወረሱንን ነው የምንማረው እንጂ እኛ አሁን አዲስ ፍልስፍና ወይም ትምህርት ፈጥረን አይደለም ። አባቶቻችን ጠመንጃቸውን ገዝተው ፣ ጥይቱን አቀባብለው በሉ እንግዲህ አውሬ ሲመጣ በዚህ ተከላከሉ ብለው አስቀምጠውልን ነው የሄዱት ። አሁን አውሬው ሲመጣ ተኩሰን ማስደንገጡ ስላቃተን ፣ ተኩስ ስለማንችል አውሬው በላን እንጂ ጠመንጃውም ጥይቱም ተሰጥቶናል ። ጥይቱም የእግዚአብሔር ቃል ነው ።

አንዲት እናት በደርግ ጊዜ መሠረተ ትምህርት ሊማሩ ሄዱ አሉ ። አስተማሪው «እማማ አምላት በጎች ቢኖርዎ ፣ አምላት ግልገሎችም ቢኖራቸው ፣ አምላቱ በጎች ቢሄዱ የቀሩት ስንት ናቸው?» ብሎ ይጠይቃል ። ሴትዮዋም «ልጄ የበጎቼን ጠባይ የማውቀው እኔ ነኝ ። እናቶቻቸው ሲሄዱ ግልገሎቹም ተከትለው ይሄዳሉ እንጂ ተነጥለው አይቀሩም» አሉት ይባላል ። አሱ የፈለገው ሂሳብ እንዲለማመዱለት ነበር ።

እኛም እንደዚህ እንዳንሆን ነው ከኦሪቱ የጸናውን የተሻረውን ፍጹም የሆነውንና የተሻሻለውን (ከሥጋዊ ወደ መንፈሳዊ የተሸጋገረ) በሚገባ መረዳት ያለብን ።

ምንም እንኳን ወንጌል የብሉይ ኪዳን ትርጓሜ ብትሆንም ፣ ወንጌል በኦሪት ላይ ሙሉ ሥልጣን አላት ። ከዚህም የተነሣ ወንጌል ከኦሪት ብዙውን አሳልፋለች ። ለመረጃ ያህል ከብዙ በጥቂቱ ምስክሮችን እንመልከት ። ይህም አባቶቻችን አዘጋጅተውልን ፣ ተማሩ አስተምሩ ብለውን አውርሰውን ያለፉት ነው ።

1ኛ፡ «ወአፈወርቅኒ ይቤ በእንተ ዝንቱ አሰመ እግዚአብሔር አብጠለ በዝንቱ ቃል መብዝኃታ ለትእዛዘ ኦሪት» «ዮሐንስ አፈወርቅም ስለዚህ ነገር እግዚአብሔር በዚህ ቃል ከኦሪት ትእዛዝ ብዙውን አሳለፈ» ብሏል ። (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 23 ቁ. 804) ።

2ኛ፡ « አሰመ ኩሉ ዘፍጹም ይደሉ በግብር ከመ ይሥዐሮ ለዘየሐጽጽ ወበእንተ ዝ ሠዐረቶ ሕገ እግዚእነ ለዘይቀድም እምኔሃ» በሥራ ፍጹም የሆነ ሁሉ ጎዶሎውን ሊሸረው ይገባልና ስለዚህም የጌታችን ሕግ ወይም ወንጌል ከእርስዋ የሚቀድመውን ኦሪትን ሻረችው ። (ፍትሐ ነገሥት መቅድም ገጽ 7) ።

3ኛ፡ « ወዓዲ አሰመ ሐሳውያን ሐዋርያት ኮኑ ይሜህርዎሙ ለሮማውያን ከመ ይዕቀቡ አሪተ ወወንጌለ ጎቡረ ወጸውሎስኒ ሜጠሙ እም ዝንቱ ስሕተት ውስተ አሚነ ወንጌል ርትዕት» ዳግመኛም ቢጽ ሐሳውያን ሕገ ኦሪትንና ሕገ ወንጌልን አንድ አድርገው እንዲጠብቁ ሮማውያንን ያስተምሩአቸው ነበርና ፣ ጳውሎስ ከዚህ ስሕተት ወደ ቀናችቱ ወደ ወንጌል ለመመለስ ጻፈላቸው» ይላል (ምክንያተ መልእክተ ጳውሎስ ኀበ ሰብአ ሮሜ - በሊቀ ሊቃውንት መሐሪ ትርፌ የተዘጋጀ ትርጓሜ ገጽ ii) ።

4ኛ፡ "ወባሕቱ ምንተ ይቤ መጽሐፍ ሰድዳ ለአመት ምስለ ወልዳ አሰመ ኢይወርስ ወልደ አመት ምስለ ወልደ ለግአዚት» ነገር ግን መጽሐፍ ምን ይላል :- የባሪያይቱ ልጅ ከጨዋይቱ ልጅ ጋር አይወርስምና ባሪያይቱን ከልጅዋ ጋር አውጣት» (ዘፍ 21፥10 ። ገላ 4፥ 30) [አመቤት የተባለችው ወንጌል ስትሆን ባሪያ የተባለችው ደግሞ ኦሪት ናት]።

እንደሚታወቀው ሚስቱ ሣራ ባለመውለድዋ ምክንያት በሣራ ፈቃድ አብርሃም ከአጋር ወልዶአል ፣ አጋር የቤት ውስጥ ሠራተኛ ነበረች ። ስለዚህ የቤተሰብ ግጭት ሲፈጠር አጋር ልጅዋን አስማኤልን ይዛ ከአብርሃም ቤት ወጣች ። ለካስ ይህ በእያንዳንዳችን ሕይወት ውስጥ የተከናወነው ታሪክ ለአዲስ ኪዳን ምሳሌ ነበር ። ሣራ የወንጌል ምሳሌ ናት ፥ አጋር ደግሞ የኦሪት ምሳሌ ናት ። ስለዚህ ታሪኩ የሚለው እመቤቲቱ ወንጌል በቤተ ክርስቲያን ስትጠበቅ ፣ ሠራተኛይቱ አጋር መልቀቅ አለባት ነው ።

«ወንህነሰ ይእዜ አኃዊነ ኢኮነ ውሉደ አመት ዘእንበለ ዘአግአዚት አሰመ ክርስቶስ አግአዘነ» ስለዚህ ፥ ወንድሞች ሆይ ፥ የጨዋይቱ የወንጌል ልጆች ነን እንጂ የባሪያይቱ የኦሪት አይደለንም ፣ ክርስቶስ ለኦሪት ፥ ለኃጢአት ከመገዛት ነጻ አውጥቶናልና ። (ገላ 4 ፥ 30-31) ።

«ሐሰ አመሰኬ ዝኮ ዘነሠትኩ ኪያሁ ከመ አሐንጽ ዐላዌ ረሰይኩ ርእስየ» ያንስ የተውኩትን ሕገ ኦሪትን የማስተምር ከሆነ ከሕግ የወጣሁ ሆንኩ «እንሰኬ እም ሕግ ዘቀዳሚ ሞትኩ» እኔስ ከቀደመው ሕግ ከኦሪት ተለይቻለው «ከመ እሕየው በካልዕ ሕግ ለእግዚአብሔር» ከኦሪትኑ ካልዕ (ሁለተኛ) በሚሆን ሕግ በወንጌል እግዚአብሔርን በማገልገል ጸንቼ እኖር ዘንድ «ወተሰቀልኩ ምስለ

ከርስቶስ » ከክርስቶስ ጋር ተዋሕዶ ለመኖር ክርስቶስ ነፍሱን ከሥጋው በመስቀል እንደለየ ከኦሪት ተለይቻለሁ ።(ገላ 2 ፥ 18-19) ።

እንዲህ እያለ የሚናገረው ቅዱስ ጳውሎስ ነው ። በነገራችን ላይ ቅዱስ ጳውሎስ የኦሪት ጠበቃ (የሕግ መምህር) የነበረ ሰው ነው ። ኦሪትን እንደ ቅዱስ ጳውሎስ የተገነዘበ የወንጌል መምህር አልነበረም ። ይህንንም ሊያደርግ የቻለው ከመንፈስ ቅዱስ ባገኘው ጸጋ ነው ።

«አስመ ኩልክሙ ውሉደ ብርሃን እንትሙ ወውሉደ መዓልት» ሁላችሁም የእውቀት የወንጌል ልጆች ናችሁና «ወኢኮንክሙ ውሉድ ሌሊት ወኢውሉድ ጽልመት » የድንቁርና የኦሪት ልጆች አይደላችሁም (በግእዝ የገላትያ ትርጓሜ)። ቅዱስ ጳውሎስ በኦሪት ላይ የሰላ ትችት ነው ያቀረበባት ። ምክንያቱም የተሰቃየው በኦሪት ስለ ነበር ነው ። ክርስቶስ የተወውን ትቶ በማስተማሩ እነዚያ የኦሪት ሕዝቦች ተነሥተውበት ያሰቃዩት ስቃይ ቢቃል ለመንገር ከባድ ስለ ነበር እንደዚሁም መንፈስ ቅዱስንም ስላሳዘኑት እጅግ በመረረ መልኩ ነበር የሚናገረው።

ከብዙ በጥቂቱ ከዚህ በላይ ጠቅለል ባለ መልኩ የቀረቡት መረጃዎች የሚያመለክቱት ወንጌል በኦሪት ላይ ሙሉ ሥልጣን ያላት በመሆንዋ ከኦሪቱ ክፍል ያሳለፈችው መኖሩን ነው ።

እንግዲህ በጳውሎስ ዘመን ለቀረው ለተሻረው ኦሪት ዛሬም እንደገና በሃያ እንደኛው መቶ ከፍለ ዘመን በእኛ ቤት ውስጥ አንዳንዶች ተከራካሪ ሆነው ተነሥተዋል ። የተከበረችውን ቤተ ክርስቲያናችንን እያስደፈሩብን ይገኛሉ ። ቤተ ክርስቲያናችንን ለተቃዋሚዎች ትችት አመቻችተው በመስጠት ቤተ ክርስቲያን አንገትዋን እንድትደፋ እያደረጉ ነው። እነዚህ ጥቂት ግለሰቦች በጳውሎስ ዘመን የነበረውን ኦሪታዊ መንፈስ ዛሬም በቤተ ክርስቲያናችን እንዳለ አድርገው ምሥጢርን ሳያደላድሉ ፣አባቶቻችንን ሳይጠይቁና እነርሱ ያስቀመጡልንን ሳያጤኑ ፣ በድፍረት በቤተ ክርስቲያን መድረክ እየቆሙ እየተናገሩ አስደፈሩን እንጂ አባቶቻችንስ አስቀድመው ጨርሰውልን ሄደዋል ።

እነዚህ ሰዎች የተሻረውን የኦሪት ክፍል አልተሻረም ለማለት የሚጠቀሙበት መሪ ጥቅሳቸው ከላይ እንደተጠቀሰው «ኢይምሰልክሙ ዘመጻእኩ አሥአሮሙ ለኦሪት ወለነቢያት ዘእንበለ ዳእሙ ከመ እፈጽሞሙ» ምን ማለት ነው "ኦሪትን ነቢያትን ልሻራቸው የመጣሁ አይምሰላችሁ ፣ ላጸናቸው እንጂ" ብሎአልና የተሻረውም የኦሪት ክፍል ጨምሮ ለምን ተነካ በማለት ያዙን ልቀቁን ይላሉ (ማቴ 5 ፥ 17 ። ሉቃ 16 ፥ 17) ።

አልፎ ተርፎም እነዚህ ግለሰቦች እኔን የቀደመውን የአባቶቼን ትምህርት በማስተማሬ ሲተቹኝ ይሰማሉ። እግዚአብሔር ይመስገን ለእኔ በረከት ነው ። ግን የተወሰኑ ያልገባቸው ሰዎች ይህን ይላሉ ተብሎ ቤተ ክርስቲያናችን አንገትዋን እየደፋች ፥ ምእመናንም መልስ እያጡ ሲሄዱ ዝም ማለት የለብንም ። እውነትን የምናስተምር በግድ ጅራፏን ልንቀምስ ይገባል ። ወይ ካህን አለመሆን ነው ፤ ወይ ቆብ አለመድፋት ነው ፤ ወይ መስቀል አለመጨበጥ ነው ። ከሆኑ ደግሞ ቤተ ክርስቲያናችንን ማሳፈር ጥሩ አይደለም ።

በመሆኑም የዚህ አይነት መደነጋገር እንዳይኖር አባቶቻችን ኦሪትን በአራት ከፍለዋታል ። ይሄ ነው ዋናው ። እኔ «ኦሪት በአጠቃላይ ተሽራለች ወይንም ስለ ኦሪት መስማትም መናገርም የለብንም» አላልሁም ወደፊትም አልልም ። የዚህ መልዕክት ዓላማ የጸናውን አጥብቀን እንድንይዝ የተሻረውን ከፍል ደግሞ ይሄ ተሸሮአል እንድንል ነው ። ለመረጃ የሚጠቀሱ ጥቅሶች ምድባቸውን አልፈው ያለቦታቸው እንዳይጠቀሱ እነዚህን አራቱን ከፍሎች ጠንቅቀን እንድናውቅ አባቶቻችን ጽፈውልን አልፈዋል ። ማንበብ፣ ማወቅ፣ መማርና ማስተማር የእኛ ኃላፊነት ነው ።

የቀደሙ አባቶቻችን ያስቀመጡልንን መረጃዎች ስንመለከታቸው «ለቀዳማዊሰ እም ቅድመ ተናግሮቱ ንበል ከመ ሕግ ቀዳማዊ ሰበ መጽአ ሕግ ደኃራዊ ኢጸንዐ ሕግ ቀዳማዊ በኩለንታሁ ፣ ወኢበጠለ ኩለንታሁ ፥ አላ ኀበ አርባዕቱ ከፍል ተከፍለ» ። **የመጀመሪያውን ሕግ [ኦሪትን] ከመናገሩ አስቀድሞ ፥ እንደ መጀመሪያው ኋለኛው ሕግ [ወንጌል] በመጣ ጊዜ፥ የፊተኛው ሕግ [ኦሪት] በአራት ክፍል ተከፈለ እንጂ መላውም አልተሻረም መላውም አልጸናም እንበል ። (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 45 ቁ. 1567)** - *(ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 45 በገጽ 88 ላይ ቀርቧልና ይመልከቱት)*

ወንጌል ሁለተኛ ሆኖ በመጣ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ሁለት ሆኗል ። ብሉይ ኪዳን ሐዲስ ኪዳን ተብሎ ። አባቶቻችን ኦሪት በሙሉም አልጸናም ፣ በሙሉም አልተሻረም ነው ያሉት ። ስለዚህ በአራት ከፍል ከፍለውልናል ። እነሱም፤

1/ ባለበት የጸና

2/ ፍጹም የሆነ

3/ የተሻሻለ (ከሥጋዊ ወደ መንፈሳዊ የተሸጋገረ)

4/ የተሻረ ናቸው ።

1) <u>ባለበት የጸና</u>

ባለበት የጸና ስለተባለው ፍትሐ ነገሥት ምን ይለናል ? «ኢሐዱስ ከፍል ተረፈ በህላዌሁ» (ፍት መን. አንቀጽ 45) ይህም ማለት ኦሥርቱ ትእዛዛተ ኦሪት አንዲሁም ከተሻረው ከኦሪት ከፍል በቀር በመጽሐፍ ቅዱስ ያለው የእግዚአብሔር ቃል በሙሉ ባለበት የጸና ነው ። አንደኛው ይሄ ነው ። «እኔ ኦሪትንና ነቢያትን ልሽር አልመጣሁም ልፈጽም እንጂ» (ማቴ 5 ፥17 ። ሉቃ 6 ፥ 16) የሚለው ጥቅስ የሚጠቀሰው ለዚህ ባለበት ለጸናው ነው እንጂ ለተሻረው አይደለም ።

2) ፍጹም የሆነ

ፍጹም የሆነ ማለት በኦሪቱ ጎዶሎ ነበር ፥ በአዲስ ኪዳን ሙሉ ሆኖአል ማለት ነው ። ይኸውም «ወኢሐዱ ከፍል ኮነ ፍጹመ» ... «አንደኛው ከፍል ፍጹም ሆነ ።» (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 45 ቁ. 1568) እንደሚል።

ያም ምንድነው ? «ባልንጀራህን ውደድ ፤ ጠላትህንም ጥላ እንደ ተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለው ፥ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ ፥ የሚረግሙአችሁንም መርቁ ፥ ለሚጠሉአችሁም መልካም ኢድርጉ ፥ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ ፤ እርሱ በክፉዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና ፥ በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናብን ያዘንባልና ። የሚወዱአችሁንም ብትወዱ ምን ዋጋ አላችሁ ? ቀራጮችስ ያንኑ ያደርጉ የለምን ? ወንድሞቻችሁን ብቻ እጅ ብትነሡ ምን ብልጫ ታደርጋላችሁ ? አሕዛብስ ያንን ያደርጉ የለምን ? እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እናንተም ፍጹማን ሁኑ» ። (ማቴ. 5 ፥ 43-48) ።

ልብ በሉ ! በኦሪት ወዳጅህን ውደድ ፤ ጠላትህን ጥላ ነበር ፤ አሁን ግን መውደድ ወዳጅህን ብቻ አይደለም ጠላትህንም ነው ። ፍጹም ማለት ይህ ነው ። ለሚያሳድድህ ጸልይ ። የሚረግምህን መርቅ ፤ ጠላትህን ውደድ ፍጹም ማለት ይህ ነው ። ክርስቲያኖች ፍጹማን ናቸው የሚባለው ለዚህ ነው ። ይህንን አድርጎ ያሳየ ራሱ ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ። ስለዚህ ልጅ አባቱን እንደሚመስለው ፥ እኔን ምሰሉ ብሎአል ። ይህን የመሰለው ሁሉ ፍጹም ሆነ ይባላል ። በፊት የሚጠበቅብን ወዳጃችንን መውደድ ብቻ ነበር ። አሁን ግን ጠላታችንንም ጭምር መውደድ ስለ ሆነ ያልብን ፍጹም ሆነ የተባለው ይህንን የመሰለው ነው ።

3) የተሻሻለ

ሕጉ በመሻሻሉ በዚህ ላይ ሁላችንም ደስ ሊለን ይገባል ። ምክንያቱም

እንዳለ ቢኖር ኖሮ ዕዳውን አንችለውም ነበር ። ፍትሐ ነገሥቱ ምን ይላል ? «ወኢሐዱ ከፍል ኮነ ሥጋዌ፥ ወፈለሰ ጎበ ግብር መንፈሳዊ» ...«አንዱ ከፍል ሥጋዊ ነበረ ። ወደ መንፈሳዊም ሥራ ተላለፈ ።» ሥጋን በውኃና በደም ስለ ማንጻት ፈንታ በንስሐና በሥራዓቶቿ ነፍስን ማንጻት ሆነ ። (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 45 ቁ.1568) ።

ሀ) የእንሰሳት መሥዋዕት

በኦሪቱ አንድ ሰው ኃጢአት ሲሠራ ወደ ካህኑ ይሄዳል ። ካህኑ ያን የኃጢአት ርኩሰት ሊያስተሰርይለት የሚችለው በውኃ እንዲታጠብ በማድረግ ፤ የበግ (የእንሰሳት) ደም በማፍሰስ ነበር ። አሁን ግን ያ አይሠራም ተሽሯል ነው የሚለው ። አንድ ሰው ኃጢአት ሲሠራ በውኃ ታጠብ «ትነጻለህ ፤ ስለ አንተ የእንሰሳ ደም ይፍሰስልህ» የሚል ነገር የለም ። ዛሬ በሐዲስ ኪዳን ግን መንጻት የሚቻለው በንስሐና በቅዱስ ቊርባን ነው ። ዛሬ ሰው ኃጢአት ሲሠራ በውኃ ታጥቦ ይነጻል ማለት አይቻልም ። ዛሬ ለኃጢአት ሥርዬት የበግ የፍየል ደም ይሠዋ የሚል ነገር የለም ። ዋና ማንጻያው ቅዱስ ቊርባን ነው ።

ለ) የኦሪት ፍርድ (ፍትሐ ኦሪት)

«ማናቸውም ሰው አባቱን ወይም እናቱን ቢሰድብ ፈጽሞ ይገደል ፥ አባቱንና እናቱን ሰድቦአልና ፤ ደሙ በራሱ ላይ ነው» (ዘሌ 20 ፥ 9) ።ይህ በኦሪቱ ሲደረግ የኖረ ነው ። ማንም ሰው አባቱን ወይም እናቱን ከሰደበ በአደባባይ በድንጋይ ተወግሮ ይሞት ነበር ። ምሕረት የሚባል ነገር አልነበረም ። ይህ ከሆነ እንግዲህ በተለይ ውጭ አገር የተወለዱ ልጆች አለቁ ማለት ነው ። ለምን ቢባል እናትና አባትን ከመገላመጥ አልፈው በ911 ለፖሊስ እየደወሉ ብዙ ወላጆችን አሳስረዋል ።

በተጨማሪም ወንድም ሆነ ሴት በአመንዝራነት ቢገኙ ፈጽመው እንዲገደሉ ታዝዟል (ዘሌ. 20 ፥ 11-21) ። እንደዚሁም ዐይን ለዐይን ፤ ጥርስ ለጥርስ ፤ የገደለ ይሙት የመሳሰለው በሙሉ የምሕረት ሕግ በሆነች በወንጌል በንስሐ ተሻሽሎአል ። ዛሬ ማንም ሰው ኃጢአት ቢሠራ ወንጌል እስከ ኃጢአቱ ይገደል አትልም፤ንስሐ ይግባ ፥ ትግባ ነው የምትለው ። በቀኙ የተሰቀለውን ወንበዴ (ፈያታዊ ዘየማንን) የማረ አምላክ ይምረዋልና ንስሐ ይግባልን ነው የምትለው ቤተ ክርስቲያን ። ክርስቲያኖችም እንደዚሁ ነው ማለት ያለብን ።

በቅዱስ መጽሐፍ «ጻፎችና ፈሪሳውያንም በምንዝር የተያዘችን ሴት ወደ እርሱ አመጡ በመካከልም እርስዋን አቁመው ፦ መምህር ሆይ! ይህች ሴት

ስታመነዝር ተገኝታ ተያዘች ሙሴም እንደነዚህ ያሉት እንዲወገሩ በሕግ አዘዘን ፤ አንተስ ስለ አርስዋ ምን ትላለህ ? አሉት ። የሚከሱበትንም እንዲያገኙ ሊፈትኑት ይህን አሉ ። ኢየሱስ ግን ጐንበስ ብሎ በጣቱ በምድር ላይ ጻፈ ፤ መላልሰው በጠየቁት ጊዜ ግን ቀና ብሎ ፦ ከእናንተ ኃጢአት የሌለበት አስቀድሞ በድንጋይ ይውገራት አላቸው ። ደግሞም ጐንበስ ብሎ በጣቱ በምድር ላይ ጻፈ ። እነርሱም ይህን ሲሰሙ ሕሊናቸው ወቀሳቸውና ከሽማግሌዎች ጀምረው እስከ ኋለኞች አንድ አንድ እያሉ ወጡ ፤ ኢየሱስም ብቻውን ቀረ ሴቲቱም በመካከል ቆማ ነበረች ። ኢየሱስም ቀና ብሎ ከሴቲቱ በቀር ማንንም ባላየ ጊዜ ፤ አንቺ ሴት ፥ እነዚያ ከሳሾችሽ ወዴት አሉ ? የፈረደብሽ የለምን ? አላት ። አርስዋም ፦ ጌታ ሆይ ፥ አንድ ስንኳ አለች ። ኢየሱስም ፦ እኔም አልፈርድብሽም ፤ ሂጂ ከአሁንም ጀምሮ ደግመሽ ኃጢአት አትሥሪ አላት ። (ዮሐ. 8 ፥ 3-11) ።

ወንጌል የምትለው ይሄንን ነው ። ስለዚህ አራተኛው ደስ የሚያሰኘው ልናልቅ የነበረው እንዳናልቅ ስለ ሆነ ነው ። የሙሴ ሕግ እስካሁን ድረስ ቢኖር ኖሮ አልቀናል በዚህ የኃጢአት ዘመን ። ወንጌል ወደ ንስሐ እንድንመለስ ለንስሐ አብቅታናለች ።

4) <u>የተሻረ</u>

ለዚህ ለተሻረው ክፍል «አኔ ኦሪትንና ነቢያትን ልፈጽም እንጂ ልሽር አልመጣሁም» የሚለው ጥቅስ አይጠቀስም ። አደራ እንጠንቀቅ! የተሻረውን ክፍል ፍትሐ ነገሥት እንዲህ ይለዋል ።

«ወአሐዱኒ ክፍል ተጸርዐ በምልው አሰመ ግብረ ቀዊም ቦቱ ተጸርዐ በምልው ወዘይትፈቀድ አምኔሁ ኮነ ዘከመ ሕርመተ ሐራውያ አሰመ መፍቅድ አምኔሁ ውሰተ ሕግ ቀዳማዊ ኮነ ከመ ኢይደመሩ ሕዝበ አግዚአብሔር ምስለ አሕዛብ አለ ኢያመልከዎ ለአግዚአብሔር ዘበኀቤሆሙ ሀሎ ብዙኀ አሕርው ከመ ኢይትመየጡ ኀበ አምልኮቶሙ ወልማዳቲሆሙ አኪት ። ወሶበ ሰፈነ አሚን ላዕለ ኩሉ አሕዛብ ወኢተርፉ ዘአንበለ ጎዳጣን ዐላውያን በፈቃድ አምላካዊ ደለወ ፈቂድ ኀበ ተጋብኦቶሙ ለመሃይምናን ወደለወ አጽርኦቱ ለዘይከልእ ወለዘይከልእዎሂ » (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 45 ቍ1567)

ትርጉሙ «አንደኛውም ክፍል ጸንቶ እንዳይኖር በሙሉ ተሻረ ። ይኸውም ከአሪያ [ከአሳማ] እንደ መከልከል ያለ ነው» በማለት በኦሪት ዘሌዋውያን ፲፩ ላይ ሰኮናው ድፍን የሆነ ፤ የማያመሰኳ አይበላም ፥ አይነካም የሚለውንና የመሳሰለውን መሻሩን ይገልጻሉ::

ትርጉሙ አላበቃም ... «በቀደመው ሕግ ወይም በኦሪት የተከለከለውን የእግዚአብሔር ወገኖች እግዚአብሔርን ከማያመልኩት በአነርሱ ዘንድ ብዙ አሪያ (አሳማ) ካላቸው ከአሕዛብ ጋር እንዳይገናኙ ነበርና ፤ ወደ አምልኮአቸውና ወደ ክፉ ልማዳቸው እንዳይመለሱ ። ሃይማኖት በአሕዛብ ሁሉ ላይ በሰፈነ ጊዜ ከጥቂቶችም ዐላውያን በቀር ባልቀሩ ጊዜ ፥ ሁሉም ክርስቲያኖች በሆኑ ጊዜ ፥ በአምላካዊ ፈቃድ ምእመናንን ወደ መሰብሰብ መሻት ተገባ ። የሚከለክለውንና የሚከለክሉትን ነገርም መሻር ተገባ" ይላል ፍትሐ ነገሥቱ ።

በአጠቃላይ ከኃጢአት በቀር በተፈጥሮ የረከሰ ወይም የተረገመ ነው የተባለው ሁሉ ተሽሮአል ይለናል። «ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው ። አሮጌው ነገር አልፎአል ። እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል» እንዳለ ሐዋርያው ። (2 ቆሮ 5 ፥ 17) ።

መጀመሪያም ቢሆን እግዚአብሔር ርኩስ ፍጥረት አልፈጠረም ። «እግዚአብሔር የፈጠረውን ሁሉ ተመለከተ ፤ እነሆ ሁሉም መልካም ነበር» (ዘፍ ፩ ፥ 31) ። ነገር ግን መልካም ሆነን ይልቁንም በአርአያውና በአምሳሉ የተፈጠርነው እኛ የሰው ልጆች በኃጢአታችን ምክንያት ስንረከስ ፤ ስንረገም በእኛ ምክንያት ምድር ተረገመች ። በእኛ ምክንያት ምድር ረከሰች ። ስለዚህ ዘመኑም ዘመነ መርገም ዘመነ ርኩሰት ሆነ ።

ያም ዘመን በሊቃውንቱ አነጋገር ዓመተ ፍዳ ዓመተ ኩነኔ ይባል ነበር ። ነገር ግን ያ የሚያልፍበት ጊዜ ነበረው ። ይኸውም አካላዊ ቃል ወልደ እግዚአብሔር ሰው ሆኖ በቀራንዮ ደሙን ሲያፈስ የእኛ መርገም እንደሚደመሰስ ፤ በእኛ ምክንያት የተረገመች ምድርም እንደምትቀደስ ፤ እንደምትባረክ ፤ ትንቢት ተነገረ ። ያ የተስፋው ዘመን ሲፈጸም አምላክ ሰው ሆኖ በቀራንዮ ደሙ ሲፈስስ ፍጥረት ወደ ቀደመ ተፈጥሮው ተመለሰ ። ማለትም የመርገም ምክንያት የሆነው የእኛ መርገም ሲደመሰስ ፤ በእኛ ምክንያት የተረገመች ምድርም ተባረከች ። ቅዱስ ያሬድ እንዳለው «ወምድርኒ ትገብር ፋሲካ ተሐጺባ በደመ ክርስቶስ» *(ቅዱስ ያሬድ የትንሣኤ መዝሙር)* ። ምድርም በደመ ክርስቶስ ታጥባለች ደስታን አድርጋለች ። ቅዱስ ያሬድ እንዲህ ያለው በዚያ መሠረት ነው ። በመሆኑም ክርስቶስ በደሙ ዓለምን እንደገና ፈጥሯታል ፤ እንደገና አድኗታል ፤ ወደ ጥንተ ተፈጥሮዋ መልሶቷል ።

ከደመ ክርስቶስ በኋላ ማንኛውም ነገር በተፈጥሮው ርኩስ ነው ካልን ከህደት ይሆንብናል ። ምክንያቱም ይህንን ማለት እግዚአብሔር ርኩስ ፍጥረት ፈጥሮአል ማለት ነውና ። እግዚአብሔር ቅዱስ ስለ ሆነ ርኩስ ፍጥረት አይፈጥርም ። የፈጠረው ሁሉ ቅዱስ ነው ። እግዚአብሔር ንጹሕ ነው ፤

የፈጠረውም ሁሉ ንጹሕ ነው ። ቡሩክ ነው የፈጠረውም ሁሉ ቡሩክ ነው ። በእኛ ምክንያት ፍጥረት ተረግሞ ነበረ ፤ መርገም ተደመሰሰ ። በእኛ ምክንያት ፍጥረቱ ቆሸሸ ነበር ። በእኛ ምክንያት የመጣው መርገም ሲደመሰስ ፍጥረት ሁሉ ወደ ቀደመ ተፈጥሮው ተመለሰ ። ስለዚህ ዛሬ በአዲስ ኪዳን ዓለምን ስናያት እግዚአብሔር የፈጠረውን ሁሉ ተመለከተ ፤ እነሆ ሁሉም መልካም ነበር የሚለው ቃል ተመልሶልናል ።

አሁን እንግዲህ እንደዚህ ከሆነ ይህን የተሻረውን ከፍል ደግሞ በሁለት ከፍለን ነው የምናየው ። «ለምን?» ቢሉ እኛ ኢትዮጵያውያን አርቶዶክሳውያን ከአሪት የመጣን ስለሆንን ከርስትናችንም የተመሠረተው በአሪት ላይ ስለሆነ ፤ በአሪትና በአዲስ ኪዳን መካከል ያለውን ልዩነት ጠንቅቀን ማወቅ ግድ ነውና ። በሁለት የተከፈለው፡-

1) የተሻረ - በልማድም ሆነ በሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን እንዳንጠቀምበት **ፈጽሞ** የተከለከለ፤

2) የተሻረ - ቢሻርም በልማድም ይሁን በሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን እንድንጠቀምበት የተፈቀደ፤

ሁለቱንም ከዚህ በታች በዝርዝር እንመለከታለን።

1) ፈጽሞ የተሻረ

ተሽሮአልና በልማድም ሆነ በሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን እንዳንጠቀምበት ፈጽሞ የተከለከለ ነው ። ተሽሮአልና በልማድም ይሁን በሥርዓት ምክንያት ልንጠቀምበትም አንችልም ። ፈጽሞ ስለተደመሰሰና ስለተሻረ በሕልምም ማስታወስ አንችልም።

ሀ) መሥዋዕተ አሪት

ራሱ ክርስቶስ አንድ ጊዜ ለመጨረሻ ጊዜ ስለ ተሠዋ ። በዮሐ (1 ፥ 29 ። ዕብ 7 ፥ 27 ። 9 ፥ 13 ። 10 ፥ 3-14) ። እንደምናየው ለመጨረሻ ጊዜ አምላክ ሰው ሆኖ ስለ እኛ ደሙን ስላፈሰሰና ስለ ተሠዋልን ሌላ የእንስሳ ደም አያስፈልገንም ። ይሄ ፈጽሞ ተደምስሶአል ። በባሕልም በሥርዓትም በልማድም ልናከናውነው አንችልም ።

ለ) ከህነት በዘር

በአሪት ካህናት የሚሆኑት ከነገደ ሌዊ ነበሩ ፤ ሐዋርያት ከነገደ ሌዊ ብቻ

አልነበሩምና ቀርቶአል ። ድሮ በአሪት ከአሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል አንዱ ነገድ ብቻ ነበር ካህን መሆን የሚችለው ። ያም ነገደ ሌዊ ነበር ። በአዲስ ኪዳን ግን ዘር መቁጠር የለም ። አሮሞ፣ አማራ፣ ትግሬ ይሁን ሌላ ማንኛውም ዘር እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ታስፈልገኛለህ ብሎ የጠራው ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ይሾማል ። ዘር ቁጠራ ቀርቷል ፤ ፈጽሞ ተደምስሶአል ። ዛሬ ምንም እንኳ የማሠርና የመፍታት እንዲሁም ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ለመፈጸም ሥልጣን ባይኖራቸው አዲስ ኪዳን እንደሚነግረን የየድርሻቸውን መንፈሳዊ የአገልግሎት መሥዋዕት ለመሠዋት ሁሉም ከርስቲያኖች ካህናት ይባላሉ ። ለመረጃ ያህል «በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኘውን መንፈሳዊ መሥዋዕትን ታቀርቡ ዘንድ ቅዱሳን ካህናት እንድትሆኑ መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሠሩ» ይላል ። (1ጴጥ 2 ፥ 5 ። ራእ 1 ፥ 6 ። ዕብ 13 ፥ 15 ። ሮሜ 12 ፥ 1) ።

አሁን እንግዲህ እዚህ ላይ ሁሉም ቄሶች ሆኑ ማለት አይደለም ። ምሥጢራተ ቤተ ክርስትያንን የመፈጸም ፥ የአዲስ ኪዳንን መሥዋዕት የማከናወን ፥ የማሠርና የመፍታት ሥልጣን የተሰጣቸው ጳጳሳትና ቀሳውስት ብቻ ናቸው ። ነገር ግን በአዲስ ኪዳን ከርስቲያኖች ዝማሬአቸውን ፣ ገንዘባቸውን ፣ ጉልበታቸውን ፣ ማቅረባቸው ማንኛውም ለቤተ ክርስቲያን የሚያከናውኑት ነገር ሁሉ መሥዋዕት ተብሎ ስለሚጠራ አዲስ ኪዳን ያንን የሚያከናውኑ ከርስቲያኖች ካህናት ይባላሉ ብሎናል ። በሌላ አነጋገር ካህናት ማለት አገልጋዮች ማለት ነው ። እንግዲህ ከህነት በዘር ቀርቶአል ።

ሐ) የባሪያ ንግድ

ዛሬ በባሕልም ይሁን በልማድ ፈጽሞ ሊከናወን የማይገባው የባሪያ ንግድ - እንደ መግዛት እንደ መሸጥ ያለው ነው ። አሪት ስለዚህ ጉዳይ ሲናገር ባሪያ የገዛ ቢኖር ፣ ስድስት ዓመት ገዝቶ በሰባተኛው ዓመት ነጻ ያውጣው ይላል ። ዛሬ እንዲህ ያለ አባባል የለም ። ይሄ ጨርሶ ተደምስሶአል ። ለምንድነው የተደመሰሰው ቢባል ወንጌል «ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም ፥ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው ፥ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና» ስለሚል ነው (ገላ 3 ፥ 27-28) ። ሐዋርያት ይህን ቃል አንግበው ለሰው ልጆች ነጻነት ሕይወታቸውን እስከማሳለፍ የደረሱ ናቸው ። ለምን ቢባል የቀረን የአሪት መርገም እንደ ገና በአዲስ ኪዳን እንዳልቀረ አድርገው በዓለም ዙሪያ አንዱ አንዱን የሚሸጡ የሚለውጡ ስለ ነበሩ እነዚያን በጽናት ተቃውመዋልና ። ባሪያ መሸጥ መለወጥ የመጣው አንዱ ጎሳ ሌላውን ጎሳ

በጦርነት ድል ሲያደርግ ድል ያደረገውን የማረከውን ጎሳ ቀጥቅጦ መግዛት ተለምዶ ያ እያደገ ሲሄድ እዚህ ደረጃ ላይ ደረሰ ። መጽሐፍ ቅዱስ አንዱ ሌላውን ሲገዛ የተገዛው ለገዥው ባሪያ ነው ይለናል። ሲገዛው ደግሞ ያለደሞዝ ነው የሚያሠራው ። ለዚህ ነው ነጭ ነጩን ሲሸጥ ሲገዛ የኖረው ። በኋላ ግን ነጩ በማንኛውም ነገር እያደገ ሲሄድ ፣ እኛ ደግሞ በተለይ አፍሪካውያን እየደኸየን ስንመጣ ፣ ድህነታችን በመልካችን በቀለማችን መስፍርት ተደረገ እንጂ ባሪያ ነጭም ጥቁርም አይልም ፣ አንዱ ለአንዱ ተገዥ ከሆነ ባሪያ ነው የሚባለው ። መጽሐፍ ቅዱስ የሚለን ይሄን ነው ። ያም ሆነ ይህ አልፎአል ። ወንጌል አንድ ሰው ናችሁ ነው የሚለን ። ስለዚህ እንደዚህ ዓይነት ነገሮች ጨርሰው ስለተሻሩ በልማድም በሥርዓትም ልናከናውናቸው አንችልም ።

መ) <u>የሞተ ሰው ፣ የእንስሳ በድን ፣ ለምጽ ፣ ደዌ እና የስውነት ፈሳሽ</u>

የሞተ ሰውንና የእንስሳን በድን መንካት እንደርኩሰት ይቁጠር ነበር ። አስከሬን ራሱ እንደርኩስ ይቁጠር ነበር ። አስከሬን የሚነካም እንደዚሁ ረከሷል ይባል ነበር። (ዘኍ 19 ፥ 11) ፤ ዘሌ (11 ፥ 39) ። ምናልባት በአከሱም ዙሪያ ይህ ልማድ የነበረ ሊሆን ይችላል ። በጎንደር ከተማ ዙሪያ ያያችሁ ካላችሁ ፈላሾች ብለን የምንጠራቸው ቤተ አስራኤሎች አሉ ። ከነሱ መካከል አንድ ቤተ አስራኤላዊ ሲሞት አስከሬኑን ተሸክመው የሚሄዱት ክርስቲያን ጎረቤቶቻቸው (አርቶዶክሶች) ናቸው ። ያ የሞተው አስከሬን ያረከሰናል ብለው ስለሚያምኑ ፣ በወንጌል ስለማያምኑ አስከሬኑን ተሸክመው የሚወስዱላቸው ጀግኖች አርቶዶክሶች ጎረቤቶቻቸው ናቸው ። ለምን ቢባል ክርስቲያንን ከኃጢአት በቀር የሚያረክሰው ነገር የለም ። የነካው ሁሉ ቅዱስ ነው ። በብሉይ ኪዳን ዘመን በሕገ አሪቱ ረክሷል ያስብል ነበር። ዛሬ ግን በሐዲስ ኪዳን ዘመን በሕገ ወንጌል ፣ ክቡር አስከሬኑን አጥበን ገንዘን ፥ ስመን ፥ ቤተ ክርስቲያን አስገብተን ፈትተን ፣ በዕጣን ዐጥነን ፥ ጸልየን ፥ ባርከን በክብር ነው የምንሸኘው ።

ለምጽ ያለበት ሰው እንደ ርኩስ ይቁጠር ነበር ። ሰዎች ለምጻሞችን አይቀርቡም ነበር። ቤትና ልብስ በመነካካት ፣ በመልበስ ቢበላሽ ቤቱም ልብሱም እንደ ርኩስ ይቁጠር ። (ዘሌ 13 ፤ ዘሌ 14) ። በወንጌል ግን ይህ ተሽሮአል ። ምክንያቱም ጌታ ኢየሱስ በቢታንያ በለምጻሙ በስምዖን ቤት ገብቶ ተስተናግዷል ። ከለምጻሞች ጋር በልቷአል ፣ ጠጥቶአል ፣ ለምጻሞችን እየዳሰሰ አንድቷቸዋል ። በመሆኑም አንዱ የተከሰሰበት ምክንያት ከለምጻሞች ጋር በላ ተብሎ ነው (ማቴ 26 ፥7) ።

በዘሌዋውያን ምዕራፍ 15 ላይ እንደምናየው በስውነቱ ቁስልና ፈሳሽ ያለበት ሁሉ እንደረከሰ ይቆጠር ነበር ። ቁስላም ሰው ወደ ቤተ መቅደስ

እንዳይገባ ትእዛዝ ነበረ ። ሴት በወር አበባዋ ጊዜ እንደረከሰች ትቁጠር ነበር ። ይህንን አስቀድመን ተመልከተናል አንመለስበትም ። ነገር ግን ያ ሕግ ዛሬ አይሠራም ። የአስዋም ይሁን የሌላ «አትንካ ፥ አትቅመስ ፥ አትያዘ ፥ ትረካሳለህ» የሚለው በሙሉ ተሽሮአል ።

ከተሻረውና ከሁለተኛው ክፍል ቢሻርም በልማድም ይሁን በሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን እንድንጠቀምበት የተፈቀደ አለ ። አስተውሉ ! ቀደም ሲል የተሻረው በሁለት ይከፈላል ተባብለናል ። ከዚያም ውስጥ አንደኛው ፈጽሞ በልማድም ይሁን በሥርዓት ልናከውነው ፣ በሕልምም ልናስበው የማንችለው ነው ። ሁለተኛው ግን ቢሻርም በልማድም ይሁን በሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን ማከናወን የሚቻል ነው:: ብቻ ከሃይማኖት እናውጣው ማለትም ይህን እንዳናደርግ ሃይማኖታችን ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ከልክሎናል እንዳንል እንጂ ከዚያ ውጭ በሆነ በሥርዓትም ይሁን በልማድ ማከናወን እንችላለን ።

2) <u>ቢሻርም በልማድ ወይም በሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን የሚከናወን</u>

ሀ) <u>ግዝረት</u>

በልማድ ከምናከናውናቸው ነገሮች ውስጥ አንደኛው ምሳሌ ግዝረት ነው ። ግዝረት ብዘመነ አሪት ሃይማኖት ነበር ። ዛሬ ግን በግዝረት ፈንታ ጥምቀት ስለ ተተካ ግዝረት ተሽሯል ። ስለዚህ ዛሬ ሰው ቢገረዝ አይጸድቅም ፥ ባይገረዝም አይኮነንም ። ዛሬ የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች የሚገረዙት በልማድ ወይም በባሕል እንጂ እንደ አሪቱ በሃይማኖት አይደለም ። መጽሐፍ ቅዱስን በመጥቀስ አይደለም ። ስለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ «እነሆ እኔ ጳውሎስ እላችሁአለሁ :- ብትገረዙ ክርስቶስ ምንም አይጠቅማችሁም ... በክርስቶስ ኢየሱስ ሆኖ በፍቅር የሚሠራ እምነት እንጂ ፣ መገረዝ ቢሆን ወይም አለመገረዝ አይጠቅምምና» ብሏል ። (ገላ. 5 ፥ 2-6) ።

መገረዝ ቢሆን አለመገረዝም ቢሆን ከንቱ ነው ፥ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መጠበቅ ነው እንጂ። (ነቆሮ 7 ፥ 19) ።

ለ) <u>የማይበሉ እንስሳትና አዕዋፍ</u>

ዛሬ በልማድ የምናከናውነው ነገር በዘሌዋውያን አሥራ አንድ ላይ ስለማይበሉ እንስሳትና አዕዋፍ የተጻፈው ነው ። ይህንን ክፍል ቀደም ሲል ብንነካካውም አሁን በስፋት ለማየት እንገደዳለን ። ምክንያቱም በአዲሱ ትውልድ እና በጎብረተሰባችን በተለይም በምዕራቡ ዓለም በሚኖሩ ዘንድ እጅግ

አነጋጋሪና አጠያያቂ የሆነ ክፍል ነውና።

አዲስ ኪዳን የሚለውን እንመልከት «ወኢንሥዐር ግብረ እግዚአብሔርን እንበይነ መብልዕ ፤ ወባሕቱ ኩሉ ንጹሕ ለንጹሐን ፤ ወእኩይሰ ለሰብእ በኑፋቄ በሊዕ» በመብል ምክንያት የእግዚአብሔርን ሥራ አታፍርስ ። ለንጹሐን ሁሉ ንጹሕ ነው ፥ በመጠራጠር የተበላ እንደሆነ ግን ለዚያ ሰው ክፉ ነው ። (ሮሜ. 14 ፥ 20) ።

ይህ ቃል የእኔ አይደለም ። እኔ የተጻፈውን የቅዱስ ጳውሎስን መልእክት ነው የምጠቅሰው ፤ ቤተ ክርስቲያናችን የምትለው ነው ። በዚህ ምክንያት ጥያቄ ሲመጣ እንዲህ ብላችሁ መልሱ ብለው አባቶቻችን ያስተላለፉልን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ነው ።

ሌላው መረጃችን ምን ያላል? «በሥጋ ገበያ የሚሸጠውን ሁሉ ከሕሊና የተነሣ ሳትመረመሩ ብሉ ፤ ምድርና በእርስዋ የሞላባት ሁሉ የጌታ ነውና ። ከማያምኑ ሰዎች አንዱም ቢጠራችሁ ፤ ልትሄዱም ብትወዱ ከሕሊና የተነሣ ሳትመረመሩ የሚያቀርቡላችሁን ሁሉ ብሉ ። ማንም ግን ፦ ይህ ለጣዖት የተሠዋ ነው ቢላችሁ ከዚያ ካስታወቃችሁና ከሕሊና የተነሣ አትብሉ» ይላል ቅዱስ ጳውሎስ ። (1ቆሮ. 10 ፥ 25-29) ።

የቅዱስ ጳውሎስን መልእክታት የተረጎሙት አባቶች እንዲህ ይላሉ በአንድምታ ትርጓሜያቸው ። «ኢትብሉ ዘከልኤ ጥረሲሁ ወዘጽፉቅ ሰኮናሁ ... ጥርሱ ሁለት የሆነ ሰኮናው ከፍት ያልሆነውን አትብላ የሚለውን ባታውቅ እንጂ ነው ትለኝ እንደ ሆነ ... አእምር ፥ እውቃለሁ ... ወእትአመን በእግዚእነ ኢየሱስ ከመ አልቦ ዘይማስን በእንቲአሁ ። ነገር ግን አምኖ ቢበሉት እንዳያስጎዳ በኢየሱስ ክርስቶስ አምናለሁ ። ... ለሙሱን ዳዕሙ ኩሉ ይማስን ። ለሙሱነ ልብ ላንተ ሁሉ የሚያስጎዳ ይመስልሃል እንጂ» ። ብለው ተርጕመዋል ። (ሮሜ ሰዎች 14 ፥ 14 ። ማቴ 15 ፥ 11 ። ሐዋ 10 ፥ 15 ። ቲቶ 1 ፥ 15) ።

ሌላው መረጃ ምንድነው የሚለው «እንግዲህ በመብል ወይም በመጠጥ ማንም አይፍረድባችሁ» ። ድሮ በኦሪት ይፈረድ ነበር ። አሁን ግን ማንም አይፍረድባችሁ ፤ ጥላ ሆኖ አልፎአል (ቈላ 1 ፥ 16) ።

ሌላው የአዲስ ኪዳን ክፍል ምን ይላል-«ወይከልኡ መባልዕተ ዘእግዚአብሔር ፈጠረ ለምእመናን» እግዚአብሔር ለምእመናን ንጹሕ አድርጎ የፈጠረውን ሥነ ፍጥረት ርኩስ ነው የሚሉ (ከዘፍ 9 ፥ 3 ጋር ያነጻጽሩ) ። «ከመ ይሴሰዩ ወያእኩቱ እለ የአምርዋ ለጽድቅ» ሃይማኖትን የሚያውቋት ሰዎች በልተው ያመሰግኑ ዘንድ ንጹሕ አድርጎ የፈጠረውን የሚከለክሉ «እስመ ኩሉ

ተግባረ እግዚአብሔር ሠናይ» እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ ንጹሕ ነውና ። «ወርእየ እግዚአብሔት ከመ ሠናይ» እግዚአብሔር ያ መልካም እንደሆነ አየ እንደተባለ (ዘፍ፣ ፥ 25) ። «ወአልቦ ግዱፍ ወኢምንትኒ ለእመ ተወክፍዎ እንዘ የአኩቱ» ስመ እግዚአብሔር ጠርተው ፥ አቡነ ዘበሰማያት ደግመው ፥ አምነው ቢመገቡት ምንም ምን የሚጣል የለምና ወይም ርኩስ የለምና ። «እስመ ይትቄደስ በቃለ እግዚአብሔር ወበጸሎት » ስመ እግዚአብሔር ጠርቶ አቡነ ዘበሰማያት ደግሞ ቢበሉት የሚከብር የሚቀደስ ስለ ሆነ ።«ወዘንተ መህሮሙ ለኢኃዊከ» ለወንድሞችህ ይህን አስተምራቸው «ወትከውን ኅሩየ ላእከ ኢየሱስ ክርስቶስ» እንዲህ የሆነ እንደ ሆነ ወይም እንዲህ ብለህ ያስተማርክ እንደ ሆነ የኢየሱስ ክርስቶስ ደግ አገልጋይ ትሆናለህ ። (1ጢሞ. 4 ፥ 2-6 ፤ ዘፍ. 1 ፥ 31 ፤ የሐዋ. 10 ፥15) ።

አባቶቻችን እንግዲህ ጠመንጃቸውን እስከ ጥይቱ አቀባብለው ሄዱ ያልኩአችሁ ይህንን ነው ። እኔ አሁን ተኮስኩ እንጂ የእኔ አይደለም ። ያቀባበሉትን ተኩሻለሁ ትደነግጡ እንደ ሆነ አላውቅም ። አባቶቻችን ያቆዩልን እንደዚህ ነው ። ይህን ሲሉም ብሉ ለማለት አይደለም ። በላ አልበላ ሆድ ለመብል ነው ፥ መብልም ለሆድ ነው ፤ ሁሉም አፈር ነው ። ግን ማለት ያለብንን ነገር እንድንል ነው ። ደግሞ አባቶቻችን ምን አሉ ?

«እስመ ኩሉ ዘኮነ ንጹሕ ለንጹሐን» እግዚአብሔር የፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ለንጹሐን (ከርስቲያኖች) ንጹሕ እንጂ ነው «ወለርኩሳንሰ እለ ኢየአምኑ አልቦ ንጹሕ ምንትኒ ፤ ድል ለተነሡ ላላመኑ ሰዎች ግን ምንም ምን ንጹሕ ነው የሚሉት የላቸውም «እስመ ርኩስ ሕሊናሆሙ» ልቦናቸው ድል የተነሣ ነውና «ወበልቦሙ የአምኑ ከመ ዘየአምርዎ ለእግዚአብሔር» በልቦናቸው እግዚአብሔርን እንደሚያውቁት አድርገው እናምናለን ይላሉ «ወይከህድዎ በምግባሮሙ» በሥራቸው ግን ይክዱታል ። «ርኩሳን እሙንቱ ወከህድያን» ድል የተነሡ ከህድያን ናቸው «ወምኑናን በውስተ ኩሉ ምግባረ ሠናይ» «በበጎ ሥራ ሁሉ ተርታዎች ናቸው ። (ቲቶ. 1 ፥ 15-16 ፤ 2ጢሞ. 3 ፥ 5 ፤ ሮሜ. 14 ፥ 20 ፤ ማቴ. 15 ፥ 11) ።

አርቶዶክሳውያን !! የአባቶቻችን ትምህርት ይሄ ነው ። ለሚጠይቁአችሁ እንዲህ ብላችሁ ነው መመለስ ። መብላት አለመብላት የግለሰቡ ነው ። እኛ ባሕላችንን መጠበቅ አለብን ። የማንበላውን አለመብላት ነው ። እንኳን እኛ አሜሪካውያን አህያ አይበሉም ፤ ፈረስ አይበሉም ። እነሱ አሪት አልነበራቸውም ።

የቤተ ክርስቲያን የቀኖና መጽሐፍ ፍትሐ ነገሥቱስ ይህን አስመልክቶ ምን ይላል ? ። በዘሌዋውያን እንዳይበላ የተከለከለው በሙሉ የተሻረ መሆኑን ፍትሐ ነገሥት ከዚህ በፊት እንዳየነው አረጋግጦአል ። (አንቀጽ 45 ቍ 1567) ።

በተለይም በአንቀጽ 23 ቍ.802 ላይ የተጻፈውን ከዚህ በታች በጥሞና እንመልከት ። «በግድ ከምትተዉት ከዚህ በቀር የበለጠ ከባድ ሸክም በላያችሁ እንዳናኖር እነሆ መንፈስ ቅዱስ ፈቅዷል ። እኛም ደግሞ ፈቀድን ብለው ከከለከሉት በቀር በክርስቶስ ሕግ የሚከለከል መብል የለም» ። የክርስቶስ ሕግ ወንጌል ነው ። ቅዱሳን ሐዋርያት በስም ጠቅሰው ከከለከሏቸው በቀር ፥ በክርስቶስ ሕግ (ወንጌል) የሚከለከል መብል የለም ። የተከለከለውም ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስ ነግሮአቸው የከለከሉአቸው ነገሮች አሉ ። ከእነዚያ በቀር የተከለከለ መብል የለም ። እነዚያ የተከለከሉት ምን እንደሆኑ ቀደም ሲል ብናይም አሁንም በመጠኑ እናያለን ።

እነዚያ የተከለከሉ ነገሮች - ደም እንዳንበላ ፥ ታንቆ የሞተውን ፥ ለጣዖት የተሠዋውን ፥ አውሬ የነከሰውን እነዚህን ነው ። ከእነዚህ በቀር በወንጌል የተከለከለ ነገር የለም ። አባቶቻችን ይህንን ሲከለክሉ ተጠንቅቀው አብራርተውልን ነው የሄዱት ። ፍትሐ ነገሥት ቍ. 803 ላይ «እነዚህም የከለከሉአቸው ጤንነት የሚጎዱ ስለ ሆኑ እንጂ በተፈጥሮአቸው የረከሱ ስለ ሆኑ አይደለም ። እግዚአብሔር ከፈጠረው ወገን ናቸውና ፥ እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ» ተብሎ ተጽፎአልና ። (ዘፍ. 1 ፥ 25 ፤ 1ጢሞ. 4 ፥ 4) ።

በቀጥታ እኔም የምለው በፍትሐ ነገሥቱ ላይ ያለውን ነው ። ዮሐንስ አፈወርቅም ስለዚህ ነገር «እግዚአብሔር በዚህ ቃል ከአሪት ትእዛዝ ብዙውን አላለፈ» ብሎአል ። «ክርስቲያኖች ስለ እግዚአብሔር ብለው በራሳቸው ፈቃድ ከሚተዉት ምግብ በቀር ቁሱ ፥ ኤጲስ ቆጶሱ ከመባልዕት ወገን ሁሉ ማንኛውም መብል ርኩስ ነው አይበል» ይላል። (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 23 ፤ ቍ 810) ።

ቁሱ ኤጲስ ቆጶሱ ፥ ሰባኪው ፥ አርቶዶክሳዊ ምእመኑ ከማንኛውም እንስሳት አእዋፍ ወገን የረከሰ ነው አይበል ። እንደዚህ ነው አባቶቻችን ነግረውን የሄዱት ።

«ይህ ሁሉ መረጃ ከተሰጠ በኋላ ይህ ነገር የተፈቀደው የአሪት እምነት ላልነበራቸው ከአሕዛብ ለተመለሱ ክርስቲያኖች እንጂ የአሪት እምነት የነበረንን እኛን አይመለከትም ። በእኛ ላይ አሁንም የጸና ነው» የሚሉ ደግሞ አሉ ። ነገር ግን ይህን አባባል ፍትሐ ነገሥት ያፈራርሰዋል ። ቃሉም እንዲህ የሚለው ነው

«ሰድስት ሰዓት ሲሆን ጴጥሮስ ሊጸልይ ከሰገነት ላይ ወጣ ። ያን ጊዜ ተርቦ ሊበላ ሽቶ ነበር ። ምግቡንም አስኪያዘጋጁለት ድረስ እንቅልፍ መጣበት ። ሰማይ ተከፍቶ አየ ። በታላቅ ልብስ አምሳል በአራቱም ማእዘን መጋረጃ ወደ ምድር ሲወርድ አየ ። በውስጡ አራት እግር ያለው እንስሳ በምድር የሚነቀሳቀስም ሁሉ የሰማይ ወፎችም አሉ ። ጴጥሮስ ሆይ ! ተነሥ ፥ አረድና ብላ የሚል ቃል ወደ እርሱ መጣ ። ጴጥሮስም ጌታዬ ሆይ እኔ ንጹሕ ያልሆነ የረከሰ ምግብ ከቶ በልቼ አላውቅምና ልበላ አይገባኝም አለው ። ዳግመኛም ጠርቶ «እግዚአብሔር ያነጻውን አንተ አታርክሰው አለው» ። ይህም ቃል ሦስት ጊዜ ሆነ ። (ፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 23. ቍ. 805 ። የሐዋ 10 ፥ 9-12) ።

አሁን እንግዲህ በቍጥር 806 እንደ ተመለከተው ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅና ሌሎች ቅዱሳን መምህራን በጴጥሮስ ታሪክ ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ ሁለት ነገሮች እንዳሉበት ተረዱ ። አንደኛው ስውር ነው ። ሁለተኛው ግልጽ ነው ።

<u>ስውሩ</u> ገና ያላመኑ አሕዛብ በአሪት ሕግ እንደ ታዘዘው ምእመናን ሊገናኙአቸው የማይገባቸው ርኩሳን ናቸው ብለን ከዛሬ ጀምሮ እንዳናስብ ነው ። ያልተገረዙ አሕዛብን መንካት ፥ ከእነሱ ጋር አብሮ መብላት ፥ እነሱን መጋባት እንደ ርኩሰት ነበር ። አሁን ግን በክርስቶስ አምነዋልና ይህን አባባልህን አንሣ ፤ እንዳውም ጴጥሮስን አሁን የምታጠምቀው ሰው አለና ተነስ ወደ እርሱ ሂድ አለው ። ስውሩ ይህ ነው ።

<u>ሁለተኛ ግን ግልጽ ነው</u> ። አለምሮ ጠባይዕ ያለን ከመሆናችን የተነሣ እንስሳት ሁሉ ንጹሐን እንደሆኑ አውቀን የሚገባውን (የምንወደውን) ከመመገብ እንዳንከለከል ነው ። የምንወደውን የሚገባውን እንጂ የማትወዱትን ብሉ አላሉም አባቶቻችን ። ግን ሐዋርያት ያሉትን እንዳትረሱ ይላሉ አባቶቻችን ። ደምን ፥ ታንቆ የሞተውን ፥ ለጣዖት የተሠዋውን ፥ ከአውሬ የተረፈውን ከመብላት በቀር እንስሳት ሁሉ ለምግብ ተፈጥረዋልና ። እንዲህ የሚለው ፍትሐ ነገሥት ነው ። ይህችን ግን ገልጾ የነገረን ስለሌለ ገበሬው ደም እየቆላ ይበላል ። የበሬውን ደም አቁቶ በብረት ምጣድ ቆልቶ እንደ ዱለት ይበላዋል ። አንድ የከለከለው ሰው የለምና ። እኔ የከለከለ አይቼ አላውቅም ። እኔ ራሴ ስኮመኩመው ነው የኖርኩት ። በኋላ ግን ኃጢአት መሆኑን ያውቅሁት መጽሐፍ ቅዱስ ሳነብ ነው ። እርግጠኛ ነኝ ከመካከላችን የበላችሁ ትኖራላችሁ ። ቀኖና የሚያስፈልጋችሁ ለዚያ ነበር ። ግን ለሚያስፈልገው ቀርቶ ለማያስፈልገው ቀኖና ይሰጣል ።

ታዲያ እኛ ከእስራኤላዊው ዕሪት እምነት ተከታይ ከነበረው ሰው ከቅዱስ ጴጥሮስ የተለየ እምነት አለን ማለት ነው ? ለእሱ እንኳ እንዲህ ሲነገረው ።

ወይስ ደግሞ እንደነ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ካሉ ከቤተ ክርስቲያን አባቶች እንበልጣለን? እነሱ ተርጉመው እንዲህ ተማሩ ፥ እንዲህ አስተምሩ፣ እንዲህ እመኑ ፤ እንዲህ አሳምኑ ብለውን ከሄዱት እንበልጣለንን ? ይልቁንም አምስት መቶ ዓመት ወደ ኋላ እንዳንሄድ የሚያስጠነቅቀንን ታሪክ ከዚህ በታች እንመልከት ።

ይህ ታሪክ በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመነ በአጼ ገላውዴዎስ ዘመን መንግሥት ጊዜ ምዕራባውያን ሚሲዮኖች የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን አሪታዊት እንጂ ወንጌላዊት አይደለችም በማለት የአሳማ መብላቱን ፣ የግዝረቱን ጉዳይ እንደ መረጃ በመቀጠር ላቀረቡት ክስ ፣ በሊቃውንት ጉባኤ የተሰጠ መልስ ነው ። «ወይራ ዶግ ይወልዳል» ፣ «የአሳት ልጅ አመድ» ይባላል ። እኛ እንደዚያ ሆንን ። ጀግኖቹ ያን ጊዜ በጨለማው ዘመን ምዕራባውያን ሚሲዮኖች ቤተ ክርስቲያንዋን የከሰሱበትን ክስ እንዴት ውድቅ እንዳደረጉት እዚህ ላይ እናንብብ ።

<u>የምዕራባውያን ሚሲዮኖች ክስ</u> :-

አንደኛው ክስ :- *"ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አሪታዊት አንጂ ወንጌላዊት አይደለችም ፤ ምክንያቱም የተሻረን ግዘረት አሰካሁን ድረስ ታከናውናለች ።"*

ሁለተኛው ክስ :- *"በደመ ክርስቶስ የተሻረን አሳማ አሰካሁን የረከሰ ነው ትላላችሁ ። የሴቶችንም ልማድ የመሰሰለውን የተመለከተ ነው።"*

<u>ሊቃውንቱ የሰጡት መልስ</u> :-

«አሳማንም ስለ መብላት ፣ ከመብላት የተከለከልነው አንደ አይሁድ የአሪትን ሕግ ለመጠበቅ ብለን አይደለም ። የሚበላውንም አንጸየፈውም ፥ አናረከሰውም ፤ የማይበላውንም ብላ ብለን አናስገድደውም ፤ አባታችን ጳውሎስ ለሮም አንደ ጻፈው የሚበላ የማይበላውን አይንቀፈው (አይናቀው) አግዚአብሔር ሁሉንም ተቀብሏቸዋልና የአግዚአብሔር መንግሥት በመብልና በመጠጥ አይደለችም ። «ለንጹሐን ሁሉ ንጹሕ ነው ለሰው ክፉው ከጥርጣሬ ጋር መብላት ነው» (ሮሜ 14 ፥ 3 -17 ። ፩ቆሮ 8 ፥ 9-13) ።

ወንጌላዊ ማቴዎስም «ከአፉ ከሚወጣው በቀር ሰውን የሚያረክሰው የለም ፤ ወደ ሆድ የሚገባ ጥቂት ቆይቶ ይወድቃል ፥ ይፈሰሳል ፥ ምግቦችን ሁሉ ያነጻል» አለ ። (ማቴ 15 ፥ 11) ።

ይህ አባባሉ ከአሪት መጽሐፍ የተማሩ የአይሁድን የስሕተት ሕንጻ ሁሉ አፈረሰው። የአኔና በግዛቴ ውስጥ ያሉ በትእዛዜ የሚያስተምሩ ዐዋቂዎች ካህናት

ሃይማኖት ይህ ነው ። ከወንጌል መንገድ ከጻውሎስም ትምህርት ወደ ቀኝና ወደ ግራ አይሉም ። በአኛም የታሪክ መጽሐፍትን ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ በግዛት ዘመኑ የተጠመቁትን አይሁድ ሁሉ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ዕለት የአሳማ ሥጋ አንዲያበሉአቸው አዘዘ የሚል ጽሑፍ አለ ።

ነገር ግን ሰው በልቡ ደስ አንዳለው የአንስሳትን ሥጋ ከመብላት ይወሰናል ። የዓሣ ሥጋ የሚወድ አለ ፣ የዶሮ ሥጋ መብላት የሚወድ አለ ፣ የበግ ሥጋ ከመብላት የሚወሰን አለ ። ሁሉ ለልቡ ደስ ያለውን ይከተላል ። የሰው ውዴታውና ፈቃዱ እንደዚህ ነው ። ስለ አንስሳት ሥጋ መብል በአዲሲቱ መጽሐፍ ውስጥ (አዲስ ኪዳን) ሕግም ቀኖናም የለም ። ለንጹሐን ሁሉ ንጹሕ ነው ። ጳውሎስም የሚያምን ሁሉን ይብላ አለ ። ሮሜ 13 ፥ 22 ። የሃይማኖቱን እውነት ታውቅ ዘንድ ይህን ሁሉ ለመጻፍ ተጋሁ ። ዳሞት በሚባል አገር በሰኔ 23 ቀን 1555 ዓ.ም ተጻፈ ።»

ይህ ጽሑፍ የተወሰደው በዳሞት የተጻፈውን ምላሽ ከጠቀሰው <u>የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ</u> ከተባለው ከብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ መጽሐፍ ነው ። ገጽ 154-155 ።

በተጨማሪም በቅዱስ ሲኖዶስ ፈቃድ እንድንማርበትና እንድናስተምርበት በደቀ መዝሙራን ማሠልጠኛዎች ሁሉ የታደለው ይህ የብፁዕ አባታችን የአቡነ ጎርጎርዮስ መጽሐፍ ገጽ 14 ላይ እንዲህ ይላል «ከክርስትና በፊት ኢትዮጵያ ብሉይ ኪዳንን ለመቀበልዋ የታሪክና የጽሑፍ ብቻ ሳይሆን በሕዝቡ ዘንድ ሲሠራባቸው የሚኖሩ አያሌ ልማዶችና ባሕሎች አሉ። እነዚህ የብሉይ ኪዳን ባሕሎችና ልማዶች በአሁኑ ጊዜ ማለትም በክርስትና ሃይማኖታችን ውስጥ እንደ ዶግማ ወይም እንደ ቀኖና ሳይሆኑ እንደ ልማድ ሆነው የሚጠበቁ ናቸው ። እነዚህም የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንዳይበሉ የሚከለክሏቸውን እንስሳትና አእዋፍ ዛሬም የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች አይመገቧቸውም ። ይህ በወንጌል ለሚያምን ሁሉ የተከለከለ አይደለም» ይላል።

ከላይ እንደገለጽነው ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው የህገር ልማድ መሠረት ነው እንጂ በወንጌል ሕግ ለሚያምኑ ሁሉ የተከለከለ አይደለም ። በዚህ መሠረት በአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ እነዚህን የማይበሉ እንስሳትና አእዋፍ ዛሬም አይበላም ። አሜሪካውያኖች ከባሕላቸው የተነሣ የማይበሉአቸው እንስሳትና አእዋፍ እንዳሉ ሁሉ ፥ እኛም ከባሕላችን የተነሣ ነው ብለን መመለስ እንጂ «ሃይማኖት ከልክሎን ነው አሪት ዘሌዋውያን ጭዐራፍ ፲፩ አግዶን ነው» ብለን በመናገር ቤተ ክርስቲያናችንን እንዳናሳፍር ከአጼ ገላውዴዎስ ትምህርት መውሰድ አለብን ።

በተጨማሪም ፣ እንደዚህማ ከሆነ ፣ ከተፈቀደማ አሳማውንም እንብላ ሌላውንም ያገኘነውን ሁሉ እናጠራቅም እናግበስብስ እንዳንል ፣ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ስለዚህ መብል ወንድሜን የሚያሰናክለው ከሆነ ፥ ወንድሜን እንዳላሰናክለው ለዘላለም ከቶ ሥጋ አልበላም» ይላል ። (1ቆሮ 8፣13) ።

አስተውሉ ! ወንድሜን ፣ ኢትዮጵያዊ ወገኔን የእኔ ሥጋ መብላት የሚያሰናክለው ከሆነ እድሜ ልኬን ሥጋ አልበላም ነው የሚለው ሐዋርያው።

በተጨማሪ «ሥጋን አለመብላት ፣ ወይንንም አለመጠጣት ፣ ወንድምህም የሚሰናከልበትን አለማድረግ መልካም ነው» ይላል ። (ሮሜ 14 ፥ 21) ።

በመሆኑም ፣ ለሆድ ሲባል ወንድምህን ማሰናከል እንዳይኖር ጥንቃቄ ያስፈልጋል ። ይሁን እንጂ ወንድም እንዳይሰናከል ተብሎ የማይበላውን እንስሳ ያረከሳል ፥ ኃጢአት ነው ማለት የበደል በደል ነውና ፥ የማንበላው ከሀገር ልማድ የተነሣ ነው ብሎ መናገር ይልመድብን ።

ሐ) የሴቶች ልማድ

የሴት የየወሩ አበባዋ በአሪቱ ያረከሳል የተባለው ፣ ሙሴ ማንኛውንም ፈሳሽ በንጽሕና በሃይማኖት ውስጥ አስገብቶ «ያረከሳል» እያለ ይጽፍ ስለነበር ፣ ዘመኑም ርኩሰት ስለነበር ፣ ሙበትም ስለነበር ነው ። ከዚህ አንጻር እንጂ የሴቷ የወር አበባ የሚያረክስ ሆኖ አይደለም ። የተፈጥሮ ጸጋዋ ነው ።

ለምሳሌ በዚህ ዓለም ያሉ ተክሎችን እንውሰድ እስከተወሰነ እድሜ ድረስ አያብቡም ። የማበብ ዕድሜአቸው ሲደርስ ያብባሉ ፣ ያፈራሉ ። እንደገና ደግሞ የማያብቡበትና የማያፈሩበት ዕድሜ ሲደርስ ያቆማሉ ። የእናቶቻችንም እንደዚያ ነው ። የእናቶቻችን ማኅፀን እኛን ያፈራ የሥላሴ ተክል ነው ። የሰው ልጆችን የሚያፈራው ማኅፀን ነው ። ስለዚህ ያ ማኅፀን እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ አያብብም ። መርገም ቢሆን ኑሮ ከተወለዱበት ጊዜ ጀምሮ ነበር የሚመጣው ። ነገር ግን እስከተወሰነ እድሜ ድረስ የለም ። እድሜው ሲደርስ ያብባል ያፈራል ። በምድር ላይ ያለው ሰው ሁሉ የማኅፀን ፍሬ ነው ። እንደ ገና ሲያፈራ ቆይቶ አንድ ቀን ያቆማል ። ምክንያቱም እናቶቻችን ያረጃሉ ፣ ሲሸመግሉ ያቆማሉ ። እንደ ተክል ነው ። የተሰጣቸው የተፈጥሮ ጸጋ እንጂ መርገም አይደለም ። በመጽሐፍ ቅዱሳችን ከዘፍጥረት እስከ ራእይ «መርገም ነው» የሚል በየትኛውም መጽሐፍ አይገኝም ።

ሙሴ በወር አበባ ጊዜ ቤተ መቅደስ እንዳይገቡ የከለከለው በንጽሕና ምክንያት ነው። ዛሬም በፍትሐ ነገሥታችን ፥ ሴቶች እንዳይገቡ የሚል ጽሑፍ

(ሕግ) አለ ። ይህ ደግሞ መርገም ስለሆነ ሳይሆን ወይም ርኩሰት ስለሆነ ሳይሆን የቤተ መቅደሱን ንጽሕና ለመጠበቅ ፣ የእነሱንም ሞራል ለመጠበቅ ሲባል ነው ። የከተሜውን አለባበሱና ንጽሕና አያያዙን ብቻ አትመልከቱ ፤ የአብዛኛውን የገጠሬ ማኅበረሰብ ማሰብ ግድ ይላል። ከመቶ ዘጠናው እጅ በገጠሩ ያሉ የእናቶቻችን አለባበስ እንዲሁም የኑሮ ሁኔታ የምታውቁት ነው ። ከሙሴ ዘመን ቢብስ እንጂ የሚሻል አይደለም ፣ ገና እንደ ሙሴ ዘመን ነው ። የወር አበባቸውን ምንም የሚቈጣጠሩበት መንገድ የላቸውም። በዚያ ምክንያት በሕግ ተጽፎአል ። ለንጽሕና ተብሎ ነው ሥርዓት የወጣለት ። ነገር ግን የእናቶቻችን አኗኗር አያያዛቸው እድገታቸው የንጽሕና አጠባበቁ ልክ እንደ ከተማዎቹ እናቶቻችን ከተስተካከለ ቅዱስ ሲኖዶስ ከዛሬ ጀምሮ ይሄ ሕግ ተነሥቶአል መግባት ትችላላችሁ ማለት ይችላል ።

የወር አበባን አስመልክቶ ከወንጌል አልፎ ውዳሴ ማርያም ሁሉ የሚለው ነው ። የወር አበባን አስመልክቶ በዘሌ 15 ፥ 12 ላይ ያለው ብቻ ሳይሆን ሴቶች በወለዱ ጊዜም እንደዚሁ እስከ አርባ እና እስከ ሰማኒያ ቀን የረከሱ ናቸው የሚል በዘሌ 12 እና በመሳሰሉት ተጽፎ ነበር ። ይሄ ሁሉ ዛሬ የለም ። ለምን ቢባል «ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን ? በዋጋ ተገዝታችሁአልና ለራሳችሁ አይደላችሁም ፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ» (1ቆሮ. 6 ፥ 20) ። «በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትእዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰው» ተብሎ ተጽፏልና ። (ቈላ. 2 ፥ 14) ።

ሌላው በውዳሴ ማርያም ላይ የምናገኘው ምን ይላል? «ወወሰደት ዘእንበለ ዘርዐ ብእሲ ዘይስዕር መርገመ እም ዘመድኃ» ... «ከባሕርያችን መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስን የሚያጠፋልንን ጌታን ዘር ምክንያት ሳይሆናት ወለደች ።» ስለዚህ ጌታ መርገመ ነፍስን ብቻ ሳይሆን መርገመ ሥጋንም ነው ያጠፋልን ለማለት ነው ። (የሐሙስ ውዳሴ ማርያም) ።

የሰኞ ውዳሴ ማርያምም እንደሚለው «ለሔዋን እንተ አስሐታ ከይሲ ፈትሐ ላዕሌሃ እግዚአብሔር እንዘ ይብል ብዙኅ አበዝኖ ለሕማምኪ ወለጻእርኪ ሠምረ ልቡ ኀበ ፍቅረ ሰብእ ወአግአዛ» ... «ከይሲ (ዲያብሎስ) ያሳታት ሔዋንን እግዚአብሔር ምጥሽንና ጣርሽን አበዛዋለሁ ብሎ ፈረደባት ፣ ነገር ግን ሰውን ወደደና ነጻ አደረጋት» ። በምኑ አንዴት ቢባል በደሙ ማለት ይቻላል ።

ዛሬ በተፈጥሮ መርገም የሚባል ነገር በሴቶች ላይ የለም ። በደሙ ነጻ ሆነዋል ። ኃጢአት ብቻ ነው ዛሬ ሴትን የሚያረክሳት ። «ወሰጠጠ መጽሐፈ

ዕዳሆሙ ለአዳም ወለሔዋን ወረሰዮሙ አግአዝያነ ዘተወልደ ለነ በህገረ ዳዊት መድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ» ... «የአዳምንና የሔዋንን የዕዳ ደብዳቤያቸውን አጠፋላቸው /ቀደደላቸው/ ፤ በዳዊት ሀገር ከዳዊት ባሕርይ የተወለደ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አዳምና ሔዋንን ነጻ አደረጋቸው ። » (የሰኞ ውዳሴ ማርያም)።

«ከዓለማዊ ከመጀመሪያ ትምህርት [ከኦሪት] ርቃችሁ ከክርስቶስ ጋር ከሞታችሁ ፥ እንደ ሰው ሥርዓትና ትምህርት ፦ አትያዝ ፥ ትረከሳለህ ፥ አትቀመስ ትረከሳለህ ፥ አትንካ ትረከሳለህ ፤ ለሚሉት ትእዛዛት «በዓለም እንደምትኖሩ ስለ ምን ትገዛላችሁ ? እነዚህ ሁሉ በመደረግ ሊጠፉ ተወስነዋልና» (ቈላ. 2 ፥ 22) ። በተለይም ይህ መረጃ ከዚህ በላይ ያረከሳል ተብሎ የተጠቀሰውን ሁሉ ያፈርሰዋል። በተለይ የሴትዋን ወርኃዊ ልማድ በተመለከተ መርገም ርኩሰት ባንልም ሥርዓቱን መጠበቅ ግን አስፈላጊ ነው ።

እንግዲህ የተሻረው ከፍል በሁለት ተከፍሎ አይተናል ። አንደኛው ከፍል ፈጽሞ የተሻረ ፤ ልናደርገው ፤ ልናስታውሰው የማይገባን ፤ ጨርሶ የተደመሰሰ ነው ። ሁለተኛው ከፍል ደግሞ ቢሻርም በልማድ ወይንም በሥርዓትም ብንጠብቀው የተፈቀደ ነው ። **የሴቶችን ልማድ በተመለከተ በሥርዓት ነው ። ግዝረትና የማንበላቸው እንሰሳትና አእዋፍ በልማድ ነው ። ልማድ የሆነውን ልማድ ፤ ሥርዓት የሆነውን ሥርዓት ፤ ሃይማኖት የሆነውን ሃይማኖት እንድንል ነው ።**

ማጠቃለያ

ኦሪትን በአራት ከፍለን አይተናል፦

1) <u>ባለበት የጸና</u> ፦ ከተሻረው ከኦሪት ከፍል በቀር አሥርቱ ትእዛዛት በሙሉ የእግዚአብሔር ቃል ባለበት የጸና ነው ።

2) <u>ፍጹም የሆነው</u> ፦ ፍጹም የተባለው ጎዶሎ ስለ ነበር ነው ። ጎደሎ የተባለው ደግሞ ወዳጅህን ውደድ ጠላትህን ጥላ ሲል የነበረ ቃል አሁን ጠላትህን ጥላ የሚለው ተነሥቶ ጠላትህን ውደድ በሚለው ስለተተካ ፍጹም ነው ።

3) <u>የተሻሻለው</u> ፦ የተሻሻለው ማለት እንደኛው ኃጢአት ስንሠራ ኃጢአትን በውኃ አጥቦ ነጽተሃል ማለት ፤ የተወሰነ ጊዜ ይቆያል ፤ የርግብ ደም ፤ የላም ደም ይሠዋለታል ። ነጻ ይባላል ። ያ አልፎአል ። ዛሬ ኃጢአት ስንሠራ በንስሐና በቍርባን እንጂ በውኃ በምን የሚባል ነገር የለም ።

ሌላው የተሻሻለው ከፍል ፍትሐ ኦሪት (የኦሪት ፍርድ)ነው ። በኦሪት የገደለ ይሙት ነበር አሁን ንሥሐ ገብቶ ይሙት ነው ። በኦሪት በአመንዝራነት የተገኙ ይገደሉ ነበር በወንጌል ግን ንሥሐ ይግቡ ነው ።

4) <u>የተሻረ</u> ፦ የተሻረው በተፈጥሮ ያረከሳል የተባለው ነው ። ይህንንም ደግሞ በሁለት ከፍለን አይተናል ።

<u>አንደኛው ከፍል</u> ፦ ፈጽሞ የተሻረ ፤ ልናደርገው ፤ ልናስታውሰው የማይገባን ጨርሶ የተደመሰሰ ነው ።

<u>ሁለተኛው ከፍል</u> ፦ ቢሻርም በልማድ ወይም በሥርዓትም ብንጠብቀው የተፈቀደ ነው ። ብቻ ከሃይማኖት እንድናወጣው ነው ። ከኦሪት ጠቅሰን እንዲህ ይላል እንዳንል ነው እንጂ በልማድም በሥርዓትም እንድንጠቀምበት ተፈቅዶአል ።

በመጨረሻ አንድ የተሸፈነ ነገር ልግለጽላችሁ ። በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 7 ከቁጥር 14-23 የተጻፈ ነው ። «ዛሬ በአዲስ ኪዳን ሰውን የሚያረክሰው እጅ ሳይታጠቡ መብላት አይደለም ። ሰውን የሚያረክሰው ከአፍ የሚወጣው ነው እንጂ ከአፍ የሚገባው አይደለም» እጅ ሳይታጠቡ መብላትም ያረከሳል ተብሎ በኦሪት ይታመን ስለ ነበር ነው ። ዛሬ በአዲስ ኪዳን ሰውን የሚያረክሰው ከአፍ የሚወጣ ነው ። እርሱም መግደል ፤ ዝሙት ፤ ምቀኝነት...እያለ ይሄድና ስድብም ይላል ። ስድብ ከአፍ የሚወጣ ነው ። ክርስቲያናዊ ሕይወትን የሚያረክሰው ይሄ ነው ። ስድብ ክርስቲያናዊ ሕይወትን ስለሚያረክስ ኃጢአት ነው ። «የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው» (ሮሜ.6 ፥ 23) ።

ኢትዮጵያውያን ክርስቲያኖች ሆይ! የአሳማ ሥጋ መብላት ሳይሆን «አሳማ»

ብሎ በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረውን መሳደብ ነው ክርስቲያኖችን የሚያረከሰው ። ዛሬ የሰው ልጆችን የሚያረከሰው «አህያ» ብሎ መሳደብ ነው እንጂ በባሕላችን የማንበላው የአህያው ሥጋ አይደለም ። ለመከፋፈላችን አንዱ ምክንያት ስድብ ነው። በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረውን ሰው «አህያ» ብለን ፣ «ባርያ» ብለን፤ «አባብ» ብለን ስንሳደብ፤ እንረከሳለን ። ይህ ርኩሰት ነው ፥ ይህ ኃጢአት ነው ። ሰው «ውሻ ፣ አህያ ፣ አባብ ባርያና ሌላም» ተብሎ አይሰደብም ።

እኛን ክርስቲያኖችን የሚያረከሰን በባሕላችን የማንበላው ፈረሱ ሳይሆን «ፈረስ» ብለን መሳደብ ነው ። እኛ አርቶዶክሳውያንን የሚያረከሰን በቅሎ መብላት ሳይሆን በፍቃዷ ያደረገችው ይመስል አንዲት ሴት ልጅ ያልወለደች እንደ ሆነ «በቅሎ» ብሎ መሳደብ ነው ። እግዚአብሔር ለዚች ሴት ልጅ ያልሰጠበት ምክንያት ይኖረዋል ። ምናልባትም ባይጠቅማት ይሆናል እንጂ እግዚአብሔር ማኅፀንን ማለምለም አቅቶት አይደለም ሥራው ነው ። ልጅ ያልወለደች እንደሆነ ልክ እንደ መርገመ አሪት «በቅሎ» ብለው የሚሳደቡ ስንቶች እንዳሉ ጆሮዎች ሰምተዋል ። ሰውን የሚያረከሰው ይህንን የመሳሰለው ነው ።

ሰውን የሚያረከሰው እኛ ክርስቲያኖች በባሕላችን የማንበላው ጥቂቶች የሚኮመኩሙት አይጡ ሳይሆን ፥ ወንድምን «አይጥ» ብሎ መሳደብ ነው:: በባሕላችን አይታችሁ ከሆነ የጋምቤላ አርቶዶክሶች ፣ የጉምዝ አርቶዶክሶች አይጥዋን ከሽነው ነው የሚበሏት ። በአንድ ወቅት ለዚህ አካባቢ የተላኩ ሊቀ ጳጳስ ሲናገሩ «ባርኩልኝ» ይሉኛል እባርከላቸዋለሁ፣ «ብላ» ሲሉኝ «እንደምታውቁት ጨጓራዬ በሽተኛ ነው አልበላም ፤ በሶ ብቻ ነው የምጠጣው» አላለሁ አሉ ፤ እንዳይቀየሚቸው ። ተመልከቱ እንግዲህ ኢትዮጵያውያንም ሆነ እኛ ብዙዎቻችን የማንመገባቸውን የሚመገቡ አሉ ። የሰውን ምግብ መተቸት ነውር ነው ። የኢትዮጵያ ባሕል የተወሰኑ ሰዎች ባሕል ብቻ ነውን ? የማንኛውም ባሕል መከበር ነው ያለበት ። የሚበሉትን ልናንቋሸሽ እና ዝቅ አድርገን ልናይ አይገባም ነውር ነው ።

ዛሬ ሰውን የሚያረከሰው ለምጽ ሳይሆን «ለምጻም» ብሎ መሳደብ ነው ። ድሮ ለምጽ ካለው ሰው ጋር መነካካት ርኩሰት ነበር ። ዛሬ ግን ለምጽ ያለበትን ሰው አቅፌ አስመዋለው። ወገኔ ነው ፥ ወንድሜ ነው ፥ ክርስቲያን ነው ፥ አካሌ ነው ፥ ከቆዳው ላይ ለምጽ ስላለበት ረከሰ አልለውም ። ነገር ግን የሚያረከሰኝ «ለምጻም» ብዬ ሰውን ስሳደብ ነው ።

በአሪት አስከሬን መንካት ያረከስ ነበር ። ዛሬ ግን ስመን ፈትተን ነው

የምንሸኘው ። ነገር ግን ክርስቲያኖችን ዛሬ የሚያረከሰን «በድን ፥ ሬሳ» ብለን ያልሞተውን ሰው መሳደብ ነው ። ይሄ ኃጢአት ነው ።

ዛሬ ሰውን የሚያረከሰው «ቅማላም» ብሎ መሳደብ ነው ። ለነገሩ ኢትዮጵያዊው ኢትዮጵያዊውን «ቅማላም» ብሎ ሲሳደብ አይገርማችሁም ? ራሱ ወይም ወገኑ ቅማል ከሰውነቱ የሌለው ማን አለ? የእኔ ወገኖች እኮ አብዛኞቹ ቅማል አለባቸው ። ድህነቱ ነው ወደው አይደለም ። ዓመት እስከ ዓመት የሚለብሱት አንድ ልብስ ነው ። የሚታጠቡበት ሳሙና የላቸውም ። ስለዚህ ማን ከማን ተሽሎ ነው በኢኮኖሚ ያደጉት አሜሪካኖች እንኳ «ቅማላም» ብለው አይሳደቡም ። «ቅማላም» ብሎ መሳደብ ርኩሰት ነው ።

ስለዚህ እኛ ኢትዮጵያውያንን እስከ መከፋፈል ያደረሰን ፣ በዘር በጎሳ በከፍለ ሀገር ከተከፋፈልንበት ነገር አንዱና ታላቁ ስድብ ነው ። አንዳችን አንዳችንን ማከበር ሲገባን ኦሮሞው ትግሬውን ወይም ደግሞ አማራው ትግሬውን ፥ ኦሮሞውን ፤ አንዱ ጎሳ ሌላውን ጎሳ ፣ አንዱ ከፍለ ሀገር ሌላውን ፣ አንዱ ባልንጀራ ሌላውን በእግዚአብሔር ቃል መሠረት በማክበር በመከባበር ፈንታ የስድብ ኢኮኖሚ ፣ የስድብ ፋብሪካ አብዝተን ፣ የስድብ ፋብሪካ ፈብርከን ይኸው ፍርክርካችን ወጣ ። ርኩሰት ከመሆን አልፎ ኃጢአት ከመሆን አልፎ በማኅበራዊ ኑሮአችን የጎዳን ስድብ ነው ። ብዙውን ትዳር ያፈረሰ ስድብ ነው ። ብዙውን ኢትዮጵያዊ አንዱን ከአንዱ የሚያገዳድል ስድብ ነው ። መገዳደል የሚጀምረው ከስድብ ነው ። እንዲያውም የእግዚአብሔር ቃል «ወንድሙን ጨርቃም ብሎ የተሳደበ ፣ በየአደባባይ ደንቆሮ ብሎ የተሳደበ ግን የገሃነም ፍርድ ይገባዋል ነው» የሚለው ።

ስድብ ርኩሰት ነው ። ይሄ ነው ኢትዮጵያውያንን የሚያረከሰው ። ከአፋችን የሚወጣው ይህን የመሰሰለው እንጂ ፥ በተፈጥሮ በአሪቱ ያረከሳል የተባለው አይደለም ። ዛሬ እግዚአብሔር ርኩስ ፍጥረት የለውም ። ከኃጢአት በቀር የሚያረክስ የረከሰ ፍጥረት የለም ። ዲያብሎስን እንኳ ቀድሶ መልአክ አድርጎ ነበር የፈጠረው ። ራሱ በራሱ በግብሩ ነው የረከሰው ። ስለዚህ እኛም ዛሬ ራሳችን በራሳችን እንዳንረክስ ጥንቃቄ ያስፈልጋል ። ማንኛውንም በተፈጥሮ ርኩስ ነው የሚል አርሱ አራሱ ርኩስ ነው ይላል የእግዚአብሔር ቃል ።

«ሲም እግዚአ ዐቃቤ ለአፉየ» «ለአንደበቴ ጠባቂ አኑር» አለ ቅዱስ ዳዊት ። ለአንደበታችን ጠባቂ ያኑርልን ። «ወማዕዶ ዘአቅም ለከናፍርየ» ለከንፈሬ መዝጊያ ስጠኝ» ነው ያለው ። መዝጊያን ይስጠን ። (መዝ 140 ፥ 3) ።

መደምደሚያ.

ስለ ቤተ ክርስቲያናችን ስንጠየቅ እግዚአብሔር የምንመልሰውን እንዲሰጠን የምንማረውን በሚገባ ማስተዋልና ንቁ ሆነን መገኘት አለብን ። በዚህ ረገድ ይህ አነስተኛ መጽሐፍ እጅግ ጠቃሚ መረጃዎችን ለአንባብያን እንዳስጨበጠ እናምናለን ። ሃይማኖትን ከሥርዓት ፣ ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያንን ከሀገር ባሕልና ወግ ለይቶ ማወቅ እጅግ አስፈላጊ መሆኑን አሳይተናል ። በኦሪትና በወንጌል መካከል ያለውን ልዩነትና አንድነት ፤ በሕግና በጸጋ ፣ በአካልና በጥላ መካከል ያለውን ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስን እና ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን መሠረት በማድረግ ለአንባብያን አቅርበናል ። ክርስቲያን ሁሉ የእምነት ቀኝና ግራውን የለየ ፣ በቅዱስ ቃሉ ላይ ተመሥርቶ የሕይወትን አቅጣጫ ማከናወን የሚችል ፤ ዕለት ዕለት በቃለ እግዚአብሔር የሚያድግ ልበ-ሰፊ መሆን ይገባዋል ። እውነተኛ ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን በልማድ ሳይሆን በእውነት ፣ በእውቀት (በአእምሮተ እግዚአብሔር) ፣ በሞገስና በጸጋ ዕለት ዕለት የሚያድግ መሆን አለበት ። ክርስቶስን በማወቅ በሃይማኖት ሙሉ ሰው የሆነ ክርስቲያን ደግሞ ከሕጻናት አእምሮ የሚሰነዘረውን ጥያቄ ሁሉ ለመመለስ ይችላል ። በዚህም ማስተዋል የተመላበት ሃይማኖታዊ አቋሙ የጠያቂዎችን ጥያቄ ጎሊናን በማያሳፍር ስልትና ጸጋ ለመመለስ ይችላል። በዚህ መጽሐፍም ጥረት የተደረገው ያለውንና የነበረውን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት በቀላል መንገድ በአጭሩ በማሳየት ጥያቄዎችን መመለስ ነው ። ጥያቄው ያልተመለሰለት ሰው ሁልጊዜ ይቸገራል። ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር ለማቅርብ ከኑፋቄም የሰዎችን ጎሊና ለመጠበቅ መልስ ሰጭ መሆን ያስፈልጋል።

ለሚጠይቁአችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት የተዘጋጃችሁ ሁኑ ይላልና እግዚአብሔር ስለ እምነታችን ስንጠየቅ የምንመልሰውን እንዲሰጠን እንጸልይ (1ጴጥ 3 ፥ 15) ። በምናምነው ጸንተን ፣ ለሚጠይቁን ሁሉ መልስ እየሰጠን እስከ መጨረሻው እንደ አባቶቻችን በሃይማኖት ጸንተን ለማታልፈው መንግሥተ እግዚአብሔር እንድንበቃ የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን።

እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን ። አሜን ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ
ከተባለው የአቡነ ጎርጎርዮስ መጽሐፍ የተወሰደ

ክፍል

ኢትዮጵያ በሃይማኖት

ከመጀመሪያው እስከዚህ ባጭሩ የገለጥነው የኢትዮጵያንና የኢትዮጵያውያንን ሀልውና ለማስተዋወቅ ፤ ያህል ነበር ። ከዚሁ በማያያዝ ከክርስትና በፊት ስለ ነበራት ሃይማኖት በመጠኑ እናወሳለን ።—ከክርስትና በፊት ስለ ኢትዮጵያ ሃይማኖት ስንናገር የአቅኒዎቿን የሕይወት ታሪክ መመርመር ሊኖርብን ነው ። ከላይ እንደ ገለጥነው ኢትዮጵያን ያቀኑ ሰዎች የመምለኬ እግዚአብሔር የናህ የልጅ ልጅ (ሳባ) እና አቢስ (ሰብታ) ስለሆኑ የአያታቸውን አምላክ አንድ እግዚአብሔርን ያመልኩ ነበር ቢባል እውነት ይመስላል ። ነገር ግን እምነቱ በትምህርት የተደገፈ ስላልሆነና ኑሯቸውም ከፍልስጥኤም ውጭ ስለሆነ አንዳንድ የአምልኮ ባዕድ ልማዶች ሰርገው ሳይገቡ አልቀሩም ። ለምሳሌ ፡— ከጌታ ልደት በፊት ፮ሺህ ዓመት አካባቢ ይኖሩ የነበሩ ኢትዮጵያውያን ለዘንዶ ይገብሩ ፣ ዘንዶ ያመልኩ እንደ ነበር በኢትዮጵያ ታሪክ ነገሥት ተጽፏል ። ይኸው የኢትዮጵያ ታሪክ ነገሥት እንደሚለው በኢትዮጵያ ሲመለክ የኖረውን ዘንዶ የገደለው የንግሥተ ሰባ አባት አንጋቦስ የተባለው ሰው ነው ። ይኸው ታሪክ ነገሥት ታሪኩን በመቀጠል ፡— ንግሥተ ሳባ የሰሎሞንን ጥበብ ለመረዳት ከኢትዮጵያ ወደ ኢየሩሳሌም መሄዷንና ከሰሎሞን ምኒልክ የሚባል ልጅ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሳ መውለዷን ልጁም አድጎ የአባቱን አገር ኢየሩሳሌምን ጐብኝቶ ሲመለስ የሙሴን ጽላትና ካህናተ ኦሪትን ፣ እንዲሁም አያሌ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ከሊቆቻቸው ጋር ይዞ እንደ መጣና ከዚያም ጊዜ ጀምሮ ብሉይ ኪዳን ወደ ግእዝ ቋንቋ መመለሱን ፣ ባንድ አምላክ ማመንም ከዚያ ጊዜ ጀምሮ መሆኑን በሰፊው ይተርካል ። ሌሎች የውጭ አገር ጸሐፊዎች ግን ያን ጊዜ በኢትዮጵያ አካባቢ በየመንና በግብጽ የነበረውን የአይሁድ ኃይልና የብሉይ ኪዳን እምነት መስፋፋት በታሪክ ስለሚያውቁ ምናልባት ኢትዮጵያ ከነዚህ ከጐረቤቶቿ ጋር በነበራት የንግድና የሥልጣኔ ግንኙነት የብሉይ ኪዳንንም እምነት ከዚያው ከነሱ ሽምታው ይሆናል ብለው የግምት ሐሳባቸውን በጽሑፍ ገልጠዋል ። ፲፭/ ከዚህም ሌላ በ፯፻፹ ዓመት ከጌታ ልደት በፊት ኢየሩሳሌም በባቢሎናውያን በተቃጠለች ጊዜ እሥራኤላውያን ብዙዎቹ ተማረኩ ። አንዳንዶቹም ነፍሴን አውጭኝ በማለት በየበረሀው ታሰደዱ ። ከነሱም ዮሐናን በሚባለው ሰው መሪነት ወደግብጽ የተሰደዱ ነበሩ ፤ ወደ ግብጽ ከተሰደዱት ውስጥ ደግሞ ተከፍለው ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ነበር ይባላል ።

በዚህ ጊዜ ሃይማኖታቸውንና ሥርዓታቸውን ለማስፋፋትና ለማጠና ከር አመች ነበር ማለት ነው ። በኤርምያስ ፶፬ እንደ ተጻፈው ከባቢ ሎን ምርኮም በፊት በግብጽ በዝርወት የሚኖሩ ብዙ አይሁድ ስለነበሩ ምናልባት በየምክንያቱ ወደዚች አገር እየገቡ ሃይማኖታቸውንና ባህ ላቸውን ሳያስፋፉ አልቀሩም ። ምንጩና የጸሐፊዎቹ ግምት የተለያየ ቢሆንም ኢትዮጵያ ከክርስትና በፊት የብሉይ ኪዳንን እምነትና ባህል ለመቀበሏ ፥ በሐዋ. ሥራ በምዕራፍ ስምንት የተመዘገበው ታሪክ ምስ ክር ሊሆን ይችላል ። ይህ ሰው ወደ ኢየሩሳሌም የሄደው ሊሰግድ ሊጸ ልይ መሆኑ ተብራርቶ ስለተተረከና ሲያነበው የነበረው ከብሉይ ኪዳን ነቢያት የታላቁን የኢሳይያስን መጽሐፍ ስለ ነበር ነው ።

ከክርስትና በፊት ኢትዮጵያ ብሉይ ኪዳንን ለመቀበሏ የታሪክና የጽሑፍ ብቻ ሳይሆን በሕዝቡ ዘንድ ሲሠራባቸው የሚኖሩ አያሌ ልማ ዶችና ባህሎች አሉ ፤ እነዚህ የብሉይ ኪዳን ልማዶችና ባህሎች ባሁኑ ጊዜ ፥ ማለት በክርስትና ሃይማኖታችን ውስጥ እንደ ዶግማ ወይም እንደ ቀኖና ሳይሆኑ እንደ ልማድ ሁነው የሚጠበቁ ናቸው ። እነዚህም ፦—

ሀ/ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት እንዳይበሉ የሚከለክሏቸውን እን ስሳትና አዕዋፍ ዛሬም የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች አይመገቧ ቸውም ። ይህ በወንጌል ለሚያምን ሁሉ የተከለከለ አይደ ለም ፥ ከሳይ እንደ ገለጥነው እኛ ግን ሲወርድ ሲዋረድ በመ ጣው ልማድ መሠረት ነው ።

15. A drian Fortescue, The Lesser Eastern Churches (London 1913) P. 294

ለ/ ግዝረት ፥ በብሉይ ኪዳን ለማመን ምልክት ሲሆን በአዲስ ኪዳን ግን በክርስቶስ ላመኑ ሁሉ መለያ ምልክታቸው ወይም ማኅተማቸው ጥምቀት ነው ። በሀገራችን ግን ከብሉይ ኪዳን በተወረሰው ልማድ ልጅ ሲወለድ ይገረዛል ፥ ግዝረቱ ግን የሕግ ሳይሆን የፈቃድ ነው ፥ ይህም ማለት በቤተ ክርስቲ ያን ቀኖና ግዝረት ሕግ አይደለም ፤ ምእመናን ልጆቻቸውን ቢያስገርዙም ባያስገርዙም የራሳቸው ፈቃድ ነው ፤ ማለት ነው ።

ለምሳሌ ያህል እነዚህን ሁለቱን ጠቀስን እንጅ ጠቅላላው በሕዝቡ የኑሮ ሥርዓትና ሃይማኖታዊ ስሜት ፥ በጎዘንና በደስታ ጊዜ ያለው ሁኔታ የበዓላት አከባበር ፥ የሴቶችና የሕፃናት ጌጣጌጥ ሁሉ ፥— የብሉይ ኪዳ ንን ሥርዓትና የሴማውያንን ሥልጣኔ የሚያሳይ ነው ። በቤተ ክርስቲያ ንም ውስጥ የማኅሌት ሥርዓት ፥ የካህናቱ ልብሰ — ተክህኖ ፥ ካባው ፥ ድርቡ ፥ ጸናጽሉ ፥ ከበሮው ፥ ኩፋሩ ፥ መጠምጠሚያው ፥ የታቦቱ ክብ ርና ሌላውም ሁሉ ከብሉይ ኪዳን ሥርዓት ጋር ይመሳሰላል ። ይህ ሁሉ የሚያሳየው ከክርስትና በፊት ኢትዮጵያ የብሉይ ኪዳን አገር እንደ ነበ ረች ነው ። በሌሎች ከአረማዊነት በተመለሱ አገሮች በግሪክ ፥ በላቲ ንና በሌሎችም ይህ ሁሉ አይታወቅም ። አንዳንድ የአረማዊነት ጠባይ ግን ይታይባቸዋል ። የመጀመሪያዎቹ የወንጌል መምህራን ሐዋርያትና ሊቃውንትም በጥንተ ስብከታቸው ሃይማኖትን የሚጐዱ ልማዶችን ብቻ እንጅ የሕዝቡን ጥቃቅን ልማድ ግን ማጥፋት አስፈላጊ መስሎ ስላላገኙት ብዙ አልታገሉለትም ። ስለዚህም ፦— ከብሉይ ኪዳን የተ መለሱት እንደ ኢትዮጵያ ያሉት አንዳንድ የብሉይ ኪዳን ሥርዓቶች ሲኖሯቸው ፥ ከአረማዊነት የተመለሱት ደግሞ በአረማዊነት በነበሩ በት ጊዜ የሚበሏቸውን ይበላሉ ፥ ግዝረትም ምን እንደሆነ አያውቁም ።

በሃያኛው መቶ ዘመን በጥንት ቅርሶች ጥናት (Archeology) በኢትዮጵያ ውስጥ በየሀና በአድቤደራ በሌሎችም ሥፍራዎች አያሌ

ጣኦት ምስሎችና የቤተ ጣኦት መገልገያ ዕቃዎች እየተቆፈሩ ወጥተ ዋል ፤ የጣኦት ቤተ መቅደሶችና የፀሐይና የጨረቃ ምስል የተቀረጸባ ቸው የመገበያያ መዶ ለቆች ተገኝተዋል ። አንዳንድ ባለታሪኮችም እንደ ሚሉት ፦— በአዞሱም ነግሦ የነበረው አይዛና (ኤዛና) (ምናልባት የአ ብርሃምና የእጽብሐ አባት ሳይሆን አይቀርም) ራሱ የረቂቁ የማሕሬም ልጅ ነኝ እያለ ይጠራ ነበር ብለዋል ። «ማሕሬምን» ግሪኮች «አሪስ» ይሉታል ። የጦር ፥ የጦረኞች ፥ የጀግኖች የአርበኞች አምላክ ማለት ነው ። ይኸው ማሕሬም ለብዙ ዘመን ለአዞሱም ንጉሣውያን ቤተ ሰብ ውቃቢ አምላክ ሳይሆን አልቀረም ። በኋላ ግን ይኸው አይዛና ኑብያን ድል አድርጎ ከያዘ በኋላ ምንም ዓይነት የጣኦት ስም አላነሣም ፤ ያገኘ ውም ድል የሰማይ አምላክ ድል እንጅ የሱ እንዳልነበረ ጽፏል ። «በሁሉ ላይ ሥልጣን ያለው በሰማይም በምድርም ለዘለዓለም የሚገዛ» ብሎ ድል የሰጠውን አምላክ ገልጧል ። ፲፯/ በአይዛና በመጀመሪያው የግ ዛት ዘመኑ የተሠሩ መሐለቆች የጣኦታት ምስል ፥ የግማሽ ጨረቃን የከዋክብት ምስል ነበረባቸው ፤ በኋላ የወጡት መሐለቆች ግን መስቀል ቅርጽ ታትሞባቸው ነበር ። እዚህ ላይ ባጭሩ የተገለጠው በጥንታዊ ቅርስ መርማሪዎችና በባለ ታሪኮች የተከሠተው የአረማውያን ጎብረ አምላል የፊተኛውን ታሪክ አይንደውም ፤ በጣኦት ማምለክና የአሕ ዛብን ልማድ በማደጎ መውሰድ ከከነዓን ውጭ ይቅርና በከነዓንም ምድር የተለመደ ነበር ፤ ለልዑል እግዚአብሔር መመስገኛ ቤተ መቅደስን ለመጀመሪያ ጊዜ የሠራው ሰሎሞንም እንኳ ለግብጻዊት ሚስቱ መስገኛ ቤተ ጣኦት አሠርቶ ነበር ። ይህን የመሰለ አድራጐት በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ጊዜ ተነግሯል ። ነገር ግን የእሥራኤል እምነት የሚነገረው ባንድ አምላክ ማመናቸው ነው ፤ መታወቂያቸውም ይኸው ነው ። በኢትዮ ጵያም እንዲሁ ነው ፤ ብዙ የተለያዩ መሪዎች እየተነሡ ላመራር እንዲ መቻቸው ሲሉ ብዙ ነገሮችን ቢለውጡና ቢያዳቅሉም ፥ የሀገሪቱንና የሕዝቡን ታሪክ አይለውጠውም ። ስለ ኢትዮጵያ የሃይማኖትና የሞራል

16 "Lithman D. A. E. ir 32 - 34

ክብር የተናገረ ሶፎንያስ ፦— ኢትዮጵያ በእንድ አምላክ የምታምን አገር መሆኗን ሲገልጥ ፦— «እምነ ማዕዶተ አፍላገ ኢትዮጵያ ያመጽኡ ሊተ መሥዋዕተ» ፦— «ከኢትዮጵያ ወንዝ ወዲያ ማዶ የሚሰግዱልኝ የተበተኑት ልጆቼ መባዬን ይዘው ወደኔ ይመጣሉ » ብሏል ። ይህም አነጋገር ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ኢየሩሳሌም ድረስ ሄዶ ኢየሱስ የአ ግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አምኖ በተጠመቀ ጊዜ ተፈጽሟል ። 17*

17- የሐዋ ፤ ሥራ ፰—፳፯—፵ ፤

የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን ታሪክ
ከተባለው የአቡነ ጎርጎርዮስ መጽሐፍ የተወሰደ

ምዕራፍ ፲፣

ኤኩሜኒዝም (Ecumenism) ና

የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

ኢኩሜኒዝም ማለት በአብያተ ክርስቲያናት ያለውን ጥላቻና ክፉ አስተሳሰብ ለማሰወገድና አብሮ ለመሥራት የተቋቋመ ዓለም አቀፍ የክርስቲያኖች ንቅናቄ ነው ።

ቤተ ክርስቲያናችን «የኢኩሜኒዝምን» መንፈስ በትክክለኛ ዓላማው ትቀበለዋለች ፣ ማለትም በአብያተ ክርስቲያናት መካከል ጥላቻን አልይህ አልይህ መባባልን እርቆ ሁሉም የየራሱን ጠብቆና አክብሮ የሌላውንም መብት ጠብቆ መኖር «የኢኩሜኒዝም» ዓላማ ነውና ። «በኢኩሜኒዝም» ስም ለገንዘብ ብሎ ራስን መቸርቸር ወይም የሌላውን ትውፊት ከራስ ጋር ማዳበል ግን በታሪክና በትውፊት ላይ ማመፅ ነው ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከላይ የተጠቀሰው የኢኩሜኒዝም መንፈስ መተዋወቅን ፤ መጠናናትንና መረዳዳትን የሚያስገኝ ድልድይ መሆኑን ተረድታ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር መሥራች አባል ናት ። ራቅ ባሉት ዘመናት በተመዘገበው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደምንረዳው ፣ ምንም እንኳ እንደዛሬ ስም ባይወጣለት ኢኩሜኒዝም» ነበረ ። ለዚህም ክርስቲያኖች የጋራ ጠላት በተነሣባቸው ጊዜ የምሥራቁ ከምዕራቡ ጋር ያደርጉት የነበረው ግንኙነት ያስረዳል ።

በኢትዮጵያ ዐፄ ካሌብ የመን ተሻግረው የሀገረ ናግራንን ክርስቲያኖች ከወራሪ ያዳኗቸው በዚሁ መንፈስ ነው ። በአካባቢያቸው ከሚኖሩ አረባውያን ጋር ግጭት ሲገጥማቸው ክርስቲያኖች ይላላኩ ነበር ። ለምሳሌ ፣ የሀገረ ናግራን እልቂት ዜና ከቍስጥንጥንያ ወደ እስክንድርያ ከዚያ ወደ እጡስም እንደመጣ እናውቃለን ።

«የኢኩሜኒዝም» መንፈስ ይኸ ከሆነ ባንዲት አገር ከተጠመቁ ባት ቤተ ክርስቲያን ተታለው የወጡትን በማኅበር ተደራጅተዋልና ፤ «በኢኩሜኒዝም» መንፈስ ራሳቸውን የቻሉ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው እንቀበላቸው ማለት ግን ቤቴዎሎጂ እለመብሰልና የቤተ ክርስቲያንን ማእከላዊ አሠራር መናድ ነው ። የኢኩሜኒዝምን መንፈስ በሚቃረን ሁኔታ እንዳንድ በሀብታቸውና በግዘፍ ከነሱ በታች የሆኑትን አብያተ ክርስቲያናት ንኡሳን እያሉ በመሰየም ሲንቋቸውና ሲያዋርዷቸው ምእመኖቻቸውንም

እየነጠቁ ሲወስዱባቸው ኑረዋል። ለዚህም አድራጎት አንጋፋዋ ፥ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ናት ።

በቤተ ክርስቲያን ታሪካችን የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የተዋወቁት በፍሎሬንስ ጉባኤ ነው ። 158 * የጉባኤው መንፈስ «በኢኩሜኒዝም» ላይ የተመሠረተ ነው ፤ ማለትም የክርስቲያኖች ጠላት የነበረውን የኦቶማን መንግሥት መስፋፋት የሚመለከት ነበር ።ነገር ግን በጉባኤው የነበሩት የሮማ ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖች ንግግር ፤ ዓላማውን የለቀቀ ስለነበር ፥ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ተወካዮች ሳይስማሙ ተመልሰዋል ።

ከዚያ ወዲህ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ኢየሱሳውያን እየ ተባሉ የሚጠሩ ሚሲዮኖቹዋን እየላከች ፥ ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲ ያን ብዙ መረጃዎችን ሰብስባለች ። መረጃዎቹ ግን በጥላቻና በንቀት ቀለም የተጻፉ ስለሆኑ ፥ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ሕልውና የሚያ ንቋሸሹ ነበሩ ። እርግጥ ነው በ፲፯ኛው መቶ ክፍለ — ዘመን ግራኝ መሐ መድ የኢትዮጵያን ክርስቲያኖች ለመደምሰስ ቢነሣ ፤ ኢትዮጵያ «በኢኩሜኒዝም» መንፈስ የፖርቱጋልን ካቶሊካዊ መንግሥት ርዳታ ጠይ ቃለች ። ነገር ግን የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖች ካቶ ሊካዊ የሆነውን መንግሥት ሁሉ በሃይማኖት ብቻ ሳይሆን በሌላም ስለ ሚያዙት ንጉሡ የኢትዮጵያ መልእክተኞች ወደባቲካን ላካቸው ። ይህም የሆነበት ምክንያት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክር ስቲያን ተቀጽላ ስላልሆነች ፥ ለፖፓው ሳያማክር ርዳታውን ቢሰጥ ፖፓው እንዳይቆጣው ነው ። በዚሁም ምክንያት ርዳታው ዘግይቶ ደረሰ ። ግራኝም የልቡን ሠራ ፤ በዐፄ ገላውዴዎስ ዘመነ መንግሥት ከፖ ርቱጋል ወታደሮች ጋር አብረው መጥተው የነበሩ ኢየሱሳውያን ደግሞ ኢትዮጵያን የባቲካን ሀገረ ስብከት ለማድረግ የነበራቸውን ሙከራ አልሳካላቸው ስላለ ፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አሪታዊት እንጅ ወን ጌላዊት አይደለችም በማለት አንዳንድ በሕዝቡ ዘንድ የሚፈጸሙ ባህ ሎችን እንደ ነውር በመቍጠር ወሬውን ያናፍሱት ጀመር ።

በዚህ ምክንያት ንጉሡ ዐፄ ገላውዴዎስ የኢትዮጵያ ትክክለኛ እምነት የሚያስረዳ ጽሑፍ በወሬው ለተወናበዱት ሁሉ አስተላለፉ ። (ጽሑፉ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ያቀናበሩት መሆኑ አያጠራጥርም ፤ በንጉሡ ስም መሆኑ ግን የሃይማኖት ኃላፊ አቡኑ ግብጻዊ ስለነበሩ ፤ የሀ

158- ፩ሺህ፬፻፸—፩ሺህ፭፻፸፩ ፤

ገሪቱን ቋንቋ አያውቁም ። ነገሩ ደግሞ ኃላፊነት ያለበት እንደመሆኑ በባለሥልጣን መነገር ስላለበት ፥ ሊቃውንቱ አርቀው በንጉሡ በኩል እንዲተላለፍ ያደረጉት ይመስላል ።)

«በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ፥ ዝንቱ ውእቱ ሃይማኖትየ ወሃይማኖተ አበውየ ነገሥት እሥራኤላውያን ወሃ ይማኖተ መርዔትየ እለ ሀለዉ በዐጸደ መንግሥትየ ። ንሕነ ነአምን በአ አሐዱ አምላክ ወበወልዱ ዋሕድ ኢየሱስ ክርስቶስ ፤ ውእቱ ቃሉ ፥ ወው እቱ ኃይሉ ፤ ውእቱ ምክሩ ፤ ወውእቱ ጥበቡ ፤ ዘሀለወ ምስሌሁ እምቅ ድመ ይትፈጠር ዓለም ፤ ወበደኃሪ መዋዕል መጽአ ኀቤነ እንዘ ኢየአርቅ እመንበረ መለኮቱ ወተሰብአ በመንፈስ ቅዱስ ወእማርያም እምቅድስት ድንግል ፤ ወተጠምቀ በዮርዳኖስ በሠላሳ ክረምት ወኮነ ብእሴ ፍጹመ ወተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል በመዋዕለ ጲላጦስ ጰንጤናዊ ፤ ሐመ ወሞተ ወተቀብረ ወተንሥአ በሣልስት ዕለት ፤ ወእምዝ በአርብዓ ዕለት አርገ በሰብሐት ውስተ ሰማያት ወነበረ በየማነ አቡሁ ፥ ወካዕበ ይመጽእ በስ ብሐት ይኴንን ሕያዋነ ወሙታነ ወአልቦ ማኅለቅት ለመንግሥቱ ፤ ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ እግዚእ ማኅየዊ ዘሠረጸ እምአብ ፥ ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለስርየተ ኃጢአት ወንሴፎ ትንሣኤ ሙታን ለሕይ ወት ዘይመጽእ ለዓለም አሜን ። ንሕነሰ ነሐውር በፍኖተ ንጉሥ ጽዮሐ አማናዊ ወኢናጸንን ኢለየማን ወኢለጸጋም እምትምህርተ አበዊነ ፤ ዐሥ ርቱ ወክልኤቱ ሐዋርያት ፥ ወጳውሎስ ፈልፈለ ጥበብ ፤ ወሰብዓ ወክልኤቱ አርድዕት ፥ ወሰለስቱ ምእት ዐሥርቱ ወሰመንቱ ርቱዓን ሃይማኖት ዘተ ጋብኡ በኒቅያ ፤ ወምእት ወሃምሳ በቍስጥንጥንያ ወክልኤቱ ምእት በኤ ፌሶን ፤ ከመዝ እሰብክ ወክመዝ እሜህር አነ ገላውዴዎስ ንጉሥ ዘኢት ዮጵያ ወስመ መንግሥትየ አጽናፍ ሰገድ ወልደ ወናግ ሰገድ ወልደ ናየድ ወበእንተ ምክንያተ አክብሮትነ ዕለተ ቀዳሚት ሰንበት አኮ ዘናኪብራ ከመ አይሁድ እለ ሰቀልዎ ለክርስቶስ እንዘ ይብሉ ደሙ ላዕሌነ ወላዕለ ውሉ ድነ ፤ እስመ እሙንቱሰ አይሁድ ኢይቀድሁ ማየ ወኢያነድዱ እሳተ ወኢያበስሉ ጸብሐ ፥ ወኢየኀብዙ ኀብስተ ፥ ወኢይትፋለሱ እምቤተ ውስተ ቤት ። ወባሕቱ ንሕነሰ ናክብራ እንዘ ናዓርግ ባቲ ቍርባነ ወንጎ ብር ባቲ ምሳሐ በከመ አዘዙነ አበዊነ ሐዋርያት በዳድስቅልያ ፤ አኮ ዘናክ ብራ ከመ ሰንበተ እሑድ እንተ ይዕቲ ዕለት ሐዳስ ዘይቤ ዳዊት በእንቲ አሃ ፤ ዛቲ ዕለት እንተ ገብረ እግዚአብሔር ንትፈሣሕ ወንትሐሠይ ፤ ባቲ፤ እስመ ባቲ ተንሥአ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ። ወባቲ ወረደ መንፈስ ቅዱስ ላዕለ ሐዋርያት ፥ በጽርሐ ጽዮን ፤ ወባቲ ተሰብአ ውስተ ከርሠ ቅድስት ማርያም ድንግል ። በዙሉ ጊዜ ፤ ወባቲ ይመጽእ ዳግመ

ለዕሴተ ጸድቃን ወለፍዳ ኃጥኣን ፤ ወበእንተ ሥርዓተ ግዝረትኒ አኮ ዘን ትገዘር ከመ አይሁድ ፤ እስመ ንሕነ ነአምር ቃለ ምህርሁ ለጳውሎስ ፈልፈለ ጥበብ ዘይቤ ተገዝሮሂ ኢይበቁዐ ፤ ወኢተገዝሮሂ ኢያሠልጥ ዘእ ንበለ ዳዕሙ ሐዳስ ፍጥረት ዘውእቱ አሚን በእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ወካዕበ ይቤ ለሰብአ ቆሮንቶስ ዘሂ ነሥአ ግዝረተ ኢይንሳእ ቁልፈተ ። ሁሉ መጽሐፈ ትምህርቱ ለጳውሎስ ሀለወ በኀቤነ ወይሜህረኒ በእንተ ግዝረት ወበእንተ ቁልፈት ። ወባሕቱ ግዝረትሰ ዘኮነ በኀቤነ በልማደ ሀገር ከመ ብጥሐተ ገጽ ዘኢትዮጵያ ወናባ ፥ ወከመ ስቁረተ እዝን ዘሰብአ ሕንድ ፤ ዘንተሰ ዘንገብር አኮ በዐቂበ ሕገ ኦሪት ዳዕሙ በልማደ ሰብእ ።

ወበእንተ በሊዓ ሐራውያኒ እኮ ዘንትከላዕ በዐቂበ ሕገ ኦሪት ከመ አይሁድ ፤ ለዘኒ በልዓ ኢናስቆርሮ ወኢናረኩሶ ፤ ወለዘኒ ኢበልዓ ከመ ይብላዕ ኢናኄብሮ ፥ በከመ ጸሐፈ አቡነ ጳውሎስ ለብሔረ ሮሜ እንዘ ይብል ዘኒ በልዓ ኢይመንኖ ለዘኢይበልዕ ወለዙሉሙ እግዚአብሔር ተወ ከፎሙ ። መንግሥተ እግዚአብሔርሰ ኢኮነት በመብልዕ ወበመስቴ ፤ ሁሉ ንጹሕ ለንጹሓን ፤ ወእኩይሰ ለሰብእ በሊዖ ምስለ ዕቅፍት ፤ ወማ ቴዎስ ወንጌላዌ ይቤ አልቦ ዘይክል አርኩሶቶ ለሰብእ ዘእንበለ ዘይወፅእ እምአፉሁ ፥ ወዘሰ ውስተ ከርሥ ይበውእ ወይትገመር ጽመ ፥ ወይትገደፍ ወይትከዓዉ ፤ ወያነጽሕ ሁሉ መባልዕተ ፤ ወብሂለ ዝንቱ ቃል ነሥተ ሁሉ ሕንጻ ስሕተቶሙ ለአይሁድ እለ ተምህሩ እመጽሐፈ አሪት ።

ሊተሰ ሃይማኖትየ ወሃይማኖተ ካህናት ማእምራን እለ ይሜህሩ በጥእዝዘየ በዐጸደ — መንግሥትየ—ወኢይትገሐሡ እምፍኖተ ወንጌል ወእምትምህርተ አቡነ ጳውሎስ ኢለየማን ወኢለጸጋም ።

ወበመጽሐፈ ታሪክኒ ጽሑፍ ሀሎ በመጽሐፈ ዚአነ እስመ ቄስጠን ጢኖስ ንጉሥ አዘዘ በመዋዕለ መንግሥቱ ለሁሉሙ እለ ተጠምቁ አይ ሁድ ከመ ያብልዕዎሙ ሥጋ ሐራውያ በዕለተ ትንሣኤሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ። ወባሕቱ በከመ አደሞ ልቡ ለሰብእ ይትሐረም እም በሊዐ ሥጋ እንስሳ። ቦ ዘያፈቅር ሥጋ'ዓ'ዛ ወቦ ዘያፈቅር በሊዓ ሥጋ ዶርሆ ወቦ ዘይትሄረም እምበሊዓ ሥጋ በግዕ ፤ ወሁሉ በከመ አደሞ ልቡ ይተሉ፥ ከመዝ ውእቱ ሥምረቱ ወፈቃዱ ለሰብእ በእንተ መብልዓ ሥጋ እንስሳ አልቦ ሕግ ወአልቦ ቀኖና ውስተ መጽሐፍ ሐዳስ ፤ ሁሉ ንጹሕ ለንጹ ሐን ፤ ወጳውሎስኒ ይቤ ዘሰ ዘየአምን ሁሎ ለይብላዕ ።

ዘንተ ሁሎ ጽሕቁ ለጽሑፍ ከመ ታእምሮ ጽድቀ ሃይማኖትየ ተጽ ሕፈ በዐሠርቱ ወሃምስቱ ምእት ፹ሃምሳ ወሃምስቱ ዓመት እምልደተ እግ ዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ አመ ዕሥራ ወሠሉሱ ለሰኔ በሀገረ ዳሞት ።»

በአብ ፥ በወልድ ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም በአንድ አምላክ ሃይማኖቴና የአባቶቼ የእሥራኤላውያን ነገሥታት ሃይማኖት በመንግሥቴም (በረት) ግዛት ውስጥ የሚገኙ ምእመናን (የመንጋየ) ሃይማኖት ይህ ነው። እኛ በአንድ አምላክ ፥ በአንድ ልጁ ም በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን ፤ ይኸውም ቃሉ ፥ ኃይሉ ፥ ምክሩ ፥ ጥበቡ ነው ። ዓለም ሳይፈጠር ከርሱ ጋር የነበረ ነው ። በ ለኛው ዘመን ከመለኮታዊ መንበሩ ሳይለይ ወደኛ መጣ ፤ ከመንፈስ ቅዱስና ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው ሆነ ። በ፴ ዓመቱ በዮርዳኖስ ተጠመቀ ፥ ፍጹም (ምሉእ) ሰው ሆነ ። በጳንጠናዊው ጲላጦስ ዘመን በዕንጨት ላይ ተሰቀለ ፥ ታመመ ፥ ሞተ ፥ ተቀበረ ፥ በሦስተኛውም ዕለት ተነሣ ፤ ከዚህ በኋላ በአርባ ቀን በክብር ወደ ሰማይ ዐረገ ፥ ባባቱ ቀኝ ተቀመጠ ፥ ዳግመኛም በክብር ይመጣል ፥ በሕያዋንና በሙታን ላይ ይፈርድ ዘንድ ፥ ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም ፥ ከአብ በሠረጸ ጌታ አዳኝ በሆነ በመንፈስ ቅዱስም እናምናለን ። ባንዲት ጥም ቅትም እናምናለን ። ኃጢአትን ለማስተሰረይ ፥ ትንሣኤ ሙታንን የሙታንንም መነሣት) ተስፋ እናደርጋለን ፥ ለዘለዓለም ሕይወት ፥አሜን። እኛስ እውነተኛ በሆነው በጥርጊያውና በዋናው መንገድ እንሔዳለን ፤ ከአባቶቻችን ትምህርት ወደ ግራም ሆነ ወደ ቀኝ አናዘነብልም ፤

ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ፥
የጥበብ ምንጭ ጳውሎስ ፥
ሰባ ሁለቱ አርድእት ፥

በኒቅያ የተሰበቡ ሦስት መቶ ዐሥራ ስምንቱ አርቶዶክሳውያን በቍስጥንጥንያ የተሰበሰቡ አንድ መቶ ሃምሳው ፥

በኤፌሶን የተሰበሰቡ ሁለት መቶው ፥ የናያድ ልጅ የወናግ ሰገድ ልጅ በመንግሥቴ አጽናፍ ሰገድ የምባል የኢትዮጵያ ንጉሥ እኔ ገላው ዴዎስ ፥ እንዲህ እሰብካለሁ እንዲህ አስተምራለሁ ። ቀዳሚት ሰንበትን የምናከብርበት ምክንያት ደሙ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይሁንብን ብለው ክርስቶስን እንደ ሰቀሉት እንደ አይሁድ የምናከብራት አይደለምን ። 159 * እነዚህ አይሁድ ውጎ አይቀዱም ፥ እሳት አያነዱም ፥ ወጥ አይ ሠሩም ፥ እንጀራ አይጋግሩም ፥ ከቤት ወደቤት አይሔዱም እኛ ግን የምናከብራት ሐዋርያት በዲድስቅልያ እንዳዘዙ ቅዳሴን በመቀደስና ግብር (ማዕድ) በመሥራት ነው ። (ሰንበቴ-ማኅበር-ተዝካር ።) እንደ እሑድ ሰንበት አይደለም የምናከብራት ይህችውም አዲሲቱ ዕለት ናት እግዚአብሔር የሠራት ዕለት ይህች ናት ፤ እንደሰንበት ሐሤትም እናድ

159. ማቴ ፡ ፳፮ ፡ ፳፰ ፡

ርግባት ብሎ ዳዊት ስለርሷ የተናገረላት ። 160 * በዚች ዕለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተነሥቶባታልና ፥ በዚችው ዕለት መንፈስ ቅዱስ በጽርሐ ጽዮን ለሐዋርያት ወርዶአልና ፥ በዚች ዕለት ሁል ጊዜ ድንግል በሆነች በቅድስት ድንግል ማርያም ማኅፀን ሰው ሆኗልና ፤ በዚች ዕለት ዳግመኛ ይመጣል ፥ ለጻድቃን ሽልማት ለኃጥአን ውርደት (ዕዳ) ።

ስለ ሥርዓተ ግዝረትም እንደ አይሁድ የምንገዘር አይደለንም የጥበብ ምንጭ የጳውሎስን ትምህርት እናውቃለንና ።—«መገዘር አይጠቅምም ፥ አለመገዘርም ግዳጅ አይደለም ። አዲስ ፍጥረት ነው እንጂ ይኸውም በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን ነው ። 161 * ዳግመኛም ለቆሮንቶስ ሰዎች «የተገዘረ ቁልፈትን አይሻ» አለ ። 162 * የጳውሎስ የትምህርቱ መጽሐፍ ሁሉ በኛ ዘንድ አለ ። ስለ ግዝረትና ስለቁልፈት ያስተምረናል ። ነገር ግን በኛ ዘንድ ያለው ግዝረት እንደ ኢትዮጵያና እንደ ኖባ የፊት መተልተል እንደ ሀንድ ሰዎች የጆሮ መነደል ያለ የአገር ልማድ ነው ። ይህን የምናደርገው በአሪት ሕግ አይደለም ። በሰው ልማድ ነው እንጅ ።

አሣማንም ስለ መብላት ፥ ከመብላት የተከለከለ ነው እንደ አይሁድ የአሪትን ሕግ ለመጠበቅ ብለን አይደለም ። የሚበላውንም አንጸየፈውም አናረክሰውም ፤ የማይበላውንም ብላ ብለን አናስገድደውም ፥ አባታችን ጳውሎስ ለሮም እንደ ጻፈው«የሚበላ የማይበላን፥ አይንቀፈው(አይናቀው) እግዚአብሔር ሁሉንም ተቀብሏቸዋልና የእግዚአብሔር መንግሥት በመብልና በመጠጥ አይደለችም ። ለንጹሐን ሁሉ ንጹሕ ነው ፥ ለሰው ክፉው ከጥርጣሬ ጋር መብላት ነው ። 163 * ወንጌላዊ ማቴዎስም -«ካፋ ከሚወጣው በቀር ሰውን የሚያረክሰው የለም ፤ ወደ ሆድ የሚገባ ጥቂት ቆይቶ ይወድቃል ፥ ይፈሳል ፥ ምግቦችን ሁሉ ያነጻል» አለ ። 164 * ይህ አባባሉ ከአሪት መጽሐፍ የተማሩ የአይሁድን የስሕተት ሕንጻ ሁሉ አፈረሰው ። የኔና በግዛቴ ውስጥ ያሉ በትእዛዜ የሚያስተምሩ ዐዋቂዎች ካህናት ሃይማኖት ይህ ነው ። ከወንጌል መንገድ ፥ ከጳውሎስም ትምህርት ወደ ቀኝና ወደ ግራ አይሉም ። በኛም የታሪክ መጽሐፋችን ንጉሥ ቈስጠንጢኖስ በግዛት ዘመኑ የተጠመቁትን አይሁድ ሁሉ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ዕለት ያሣማ ሥጋ እንዲያበሏቸው አዘዘ የሚል ጽሑፍ አለ ።

160. መዝ. ፩፻፲፯ ፡ ፳፬ ፡
161. ገላ. ፭ ፡ ፮—፲፭ ፡
162. ቀዳ. ቆሮ ፡ ፯ ፡ ፲፰ ፡
163. ሮሜ . ፲፬ ፡ ፫ ፡ ፲፯ ፡ ቲቶ ፡ ፩ ፡ ፲፭ ፡ ቀዳ ፡ ቆሮ ፡ ፰ ፡ ፱ ፡—፲፫ ፡
164. ማቴ . ፲፭ ፡ ፲፩—፲፯ ፡ ማር ፡ ፯ ፡ ፲፰ ፡

ነገር ግን ሰው በልቡ ደስ እንዳለው የእንስሳትን ሥጋ ከመብላት ይወሰናል፡- የአሣ ሥጋ የሚወድ አለ ፤ የዶሮ ሥጋ መብላት የሚወድ አለ ። የበግ ሥጋ ከመብላት የሚወሰን አለ ። ሁሉ ለልቡ ደስ ያለውን ይከተላል ። የሰው ውዴታውና ፈቃዱ እንደዚህ ነው ። ስለ እንስሳት ሥጋ መብል በአዲሲቱ መጽሐፍ ውስጥ (አዲስ ኪዳን) ሕግም ቀኖናም የለም ። ለንጹሐን ሁሉ ንጹሕ ነው ጳውሎስም ፡-«የሚያምን ሁሉን ይብላ» አለ 165* የሃይማኖቴን እውነት ታውቅ ዘንድ ይህን ሁሉ ለመጻፍ ተጋሁ ። ዳሞት በሚባል አገር በሰኔ ፳፫ ቀን ፲፭፻፶፭ ዓ/ም ተጻፈ።

ከዚያም ወዲህ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መልእክተኞች በጽሑፋቸው የሚያሰፍሩዋቸው አስተያየቶች ሁሉ ምርቅና ፍትፍት የሆኑ ናቸው ። ማለትም ባንድ ፌት ስለ ኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ አስበው ለመጻፍ የሰነዘሩ ይመስሉና በዚያው ውስጥ ደግሞ ቤተ ክርስቲያኒቱ የምትዋረድበትንና የምትጋለጥበትን ፣ ማንኛውንም ሁሉ እንደመሰላቸው በመተርጐም ለአንባቢ ያቀርባሉ ። በእኛም በኩል የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት በሀብት እጥረት ምክንያት እንደነሱ በማኅተም ባያሳትሙትም ፣ ባልሞት ባይ ተጋዳይነት በቅኔያቸውም ሆነ በጽሑፋቸው መልስ ሲሰጡበት ኑረዋል ፤ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ፡-(ወኢሆርኩ ኀበ ተሰምየ ክርስቶስ ከመ አይሕንጽ ዲበ መሠረተ ባዕድ ፤ » የክርስቶስ ስም ወደ ተጠራበት አልሔድሁም ፣ በሌላ መሠረት ላይ እንዳላንጽ 166* ያለውን የቅዱስ ጳውሎስን አርአያነት ረስታ በጎችን ከእረኞቻቸው ስትነጣጥል ኑራለች ።

አሁን በኢትዮጵያ ከሚገኙት የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች ብዙዎቹ በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተጠመቁ ናቸው ። ይህ ሁሉ ተጽዕኖና ግፊት ቢኖርም ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ባንዳንድ ስብሰባዎች የኢትዮጵያና የሮማ ቤተ ክርስቲያኖች ተወካዮች መገናኘት ጀምረዋል ፣ ለወደፊትም ቢሆን በሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችን የምናሳስበው በሃይማኖት ስም እኛን ለመከፋፈል የዘመቱብንን የፈረንጆች አስተሳሰብ እንዲያስወግዱና አንዲት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናቸውን እንዳይረሷት ነው ። ስለ ሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በመጠኑ ይህ ነው ።

165. ሮሜ. ፲፫ ፡ ፩፤ ፩፬ ፤
166. ሮሜ፡ ፲፭ ፡ ፳ ፡

ከፍትሐ ነገሥት የተወሰደ

በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩አ ፡ አምላክ ፡ ክፍል ፡ ዳግ ማዊ ፡ በእንተ ፡ ምግባራት ፡ እንተ ፡ ይሜግቡ ፡ ባቲ ፡ ወእንተ ፡ ይፈልጥዋ ፡ መእንተ ፡ ይክልኡ ፡ ኪያሃ ፡ ወበእንተ ፡ ግጎደር ፡ ወናሁ ፡ አቅደምነ ፡ ፈሊጠ ፡ አናቅጺሁ ፡ በክፍል ፡ ቀዳማዊ ።

እንቀጽ ፡ ፩ወ፲፡ ።

በእንተ ፡ መብልዕ ፡ ወአልባስ ፡ መግኦደር ፡ ወተግባረ ፡ እድ ፡ ዘይደሉ ፡ ለመኒሓውያን ።

፩ወ፩ መመብልዕሰ ፡ በውስተ ፡ ሕግ ፡ መሚሓዊት ፡ አልቦ ፡ ውስቴቱ ፡ ሕርመት ፡ ዘእንበለ ፡ ዘክ ልኡ ፡ ሐዋርያት ፡ እምኔሁ ፡ በመጽሐፈ ፡ አብ ረከሰሰ ፡ ወበቅኖናሆሙ ፡ በብሂሎቶሙ ፡ ናሁ ፡ ውምረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወሠመርነ ፡ ንሕ ነኒ ፡ ካዕበ ፡ ከመ ፡ ኢናንብር ፡ ላዕሌክሙ ፡ ያረ ፡ ክቡደ ፡ ዘይፈደፍድ ፡ ዘእንበለ ፡ ዝንቱ ፡ ዘተጎድጉ ፡ ኪያሁ ፡ በግብር ፡ ወውእቱ ፡ ከመ ፡ ትርጎቱ ፡ እምበለይ ፡ ደም ፡ ወሕንቅ ፡ መመሥ ዋዕተ ፡ ጣዖት ፡ ወብላዐ ፡ አርዌ ።

፩ወ፪ ወለእሉሂ ፡ የሐርምዎሙ ፡ በእንተ ፡ ዘበሉ ፡ ውስቴቶሙ ፡ እምሕግም ፡ ነፍሳዊ ። እስመ ፡ ተሰናእዎ ፡ ምስለ ፡ መምለኪያን ፡ ጣዖት ፡ በዐ ሊወ ፡ ዘያዘብሕም ፡ ለአግልክት ፡ ይከውን ፡ ዘይሳተፎሙ ፡ በአምልኮቶሙ ፡ ወይሴሰዐ ፡ ዝንቱ ፡ ነገ ፡ አምልኮ ፡ ጣዖታት ። ወበእንተ ፡ ዘዘሰ ፡ ውስቴቱ ፡ እምሕግም ፡ ሥጋዊ ፡ ወነፍ ሳዊ ፡ እስመ ፡ ይእቲ ፡ ታግስን ፡ ቱስሕተ ፡ ሥጋ ፡ ግስና ፡ ዘያብጽአ ፡ ኀበ ፡ ሙስና ፡ ፍጥ ረት ፡ መጓዲ ፡ ትመስድ ፡ ኅበ ፡ ዘጥለ ፡ አባል ።

፩ወ፫ ወአከ ፡ ዘአሕረምዋ ፡ እስመ ፡ ርኵስት ፡ ይእቲ ፡ በፍጥረታ ፡ እስመ ፡ እምፍጥረተ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ይእቲ ። ወናሁ ፡ ተጽሕፈ ፡ ለነ ፡ በውስተ አረት ፡ ዘይብል ፡ "ወርእየ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ እንድ ፡ አምላክ ። ሁለተኛ ክፍል ። ስለ ፡ ምግባራት ፡ ለይጥው ፡ ስለሚያስተዳድሩባትና ፡ እርኢንም ፡ ስለሚከለክሉባት ፡ ስለቤትም አሠራር፡ ይናገራል ። እነሆ ፡ እንቀጾችን ፡ በመ ጀመሪያው ፡ ክፍል ፡ ለይተን ፡ ተናግ ረናል ።

እንቀጽ ፡ ፳፪ ።

ስለ ፡ መብልና ፡ ስለ ፡ ልብስ ፡ ስለ ፡ ቤትም ፡ ለክርስቲያኖች ፡ ስለሚገባው ፡ የእጅ ፡ ሥራ ።

፳፪፩ ሐዋርያት ፡ በግብረ ፡ ሐዋርያትና ፡ በሲኖዶሳ ቸው ፡ በግድ ፡ ከምትትጨት ፡ ከዚህ ፡ በቀር ፡ የበለጠ ፡ ክባድ ፡ ሸክም ፡ በላያችሁ ፡ እንዳና ኖር ፡ እነሆ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፈቅዷል ፡ እኛም ፡ ደግሞ ፡ ፈቀድን ፡ ብለው ፡ ከክለኩሉት ፡ በቀር ፡ በክርስቶስ ፡ ሕግ ፡ የሚከለከል ፡ መብል የለም ። (የሐዋ ፡ ፲፭ ፡ ፳፰ - ፳፱) ። ይኸውም ፡ ጾምን ፡ ታንቆ ፡ የሞተውን ፡ ሰጣዖት ፡ የተሠ ዋውን ፡ አሙሬ ፡ የነከሰውን ፡ ከመብላት ፡ ትነ ለከሉ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

፳፪፪ እኒህንም ፡ የሚከለክሏቸው ፡ በውስጣቸው ፡ ነፍስን ፡ (ሰውነትን) ፡ የሚጎዳ ፡ ሕግም ፡ ስላለ ፡ ነው ። ለጣዖታት ፡ የተሠዋውን ፡ በመብላት ፡ ጣዖትን ፡ ከሚያመልኩ ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ መሆን ፡ በአምልኮታቸው ፡ አንድ ፡ የሚያደርጋቸው ፡ ይሆናልና ። ይህም ፡ ጣዖትን ፡ ወደ ፡ ግምለክ ፡ ይስበዋል ። ነፍስንም ፡ ሥጋንም ፡ የሚጎዳ ፡ ሕግም ፡ በውስጡ ፡ ስላለ ፡ ነው ። ይህች ፡ መፈ ጠርን ፡ ወደማጥፋት ፡ በሚያደርስ ፡ ጥፋት ፡ የሥጋን ፡ ባሕርያት ፡ ስምንት ፡ ታጠፋልችና። ዳግመኛም ፡ አካልን ፡ ወደማጉደል ፡ ታደርሰ ለች ።

፳፪፫ በተፈጥሮዋ ፡ የረከሰች ፡ ናት ፡ ብለው ፡ የክለከ ሏት ፡ አይደለም ። እግዚአብሔር ፡ ከፈጠረው ፡ ፍጥረት ፡ ወገን ፡ ናትና ። እግዚአብሔር ፡ የፈ ጠረው ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ መልካም ፡ እንደሆነ ፡ አንተጽ ፡ ፳፫ ።

ሁሉ ፡ ዘፈጠረ ፡ ከመ ፡ ሠናይ ፡ ውእቱ" ። ወበመንጌኒኒ ፡ ይቤ ፡ እግዚእነ ፡ አኮ ፡ ኵሉ ፡ ዘይበውእ ፡ ውስተ ፡ አፈ ፡ ሰብእ ፡ ዘይክል ፡ አርኵሶቶ ። ወአፈ ፡ ወርቅኒ ፡ ይቤ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብጠለ ፡ በዝ ንቱ ፡ ቃል ፡ መብዝኃታ ፡ ለትእዛዘ ፡ አራት ።

፳፪፬ ወያጸንፅ ፡ ዘንተ ፡ ምክረ ፡ ዘተንግረ ፡ በአብረከ ሲስ ፡ ወውእቱ ፡ ቃለ ፡ ሉቃስ ፡ ወንጌላዊ ፡ ዘይቤ ፡ ወወርገ ፡ ጴጥሮስ ፡ መልዕልተ ፡ ናሕሰ ፡ ጊዜ ፡ ፮ት ፡ ሰዓት ፡ ከመ ፡ ይጸሊ ፡ ወነሥ ፡ ርኀበ፡ ወይፈቅድ ፡ ይብላዕ ፡ መእንዘ ፡ ያስተዳልዉ ፡ ሎቱ ፡ መጽአ ፡ ድቃስ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወርእየ ፡ ሰማየ ፡ ርጉወ ፡ ወናሁ ፡ ሞጣሕት ፡ ዘእንገ ፡ በፅቱ ፡ ጽንፈ ፡ እምላለ ፡ ልብስ ፡ በዚያ ፡ እንዘ ፡ ይወርድ ፡ ዲበ ፡ ምድር ። ወሀሎ ፡ ውስ ቴቱ ፡ ኵሉ ፡ እንሰሳ ፡ ዘፀቱ ፡ እገሪሁ ፡ ወሀሉ ፡ ዘይትሐወስ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ መአዕዋፈ ፡ ሰማይ ፡ ወመጽአ ፡ ቃል ፡ ኀቢዙ ፡ ዘይብል ፡ ተንሥኣ ፡ አ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሕርድ ፡ ወብላዕ ። ወይቤሎ ፡ ''ዘእግዚአብሔር፡ አንጽሖ ፡ አታስተራህስ ፡ አንተ ፡ ወከነ ፡ ዝንቱ ፡ ቃል ፡ ፫ተ ፡ ጊዜያተ'' ።

፳፪፭ ወቅዱሳንሂ ፡ ሙሃዘራን ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ወከል አኂው ፡ አበው ፡ ለበዉ ፡ እምዝንቱ ፡ ከመ ፡ መፍቅድ ፡ ኮነ ፡ ቦቱ ፡ ጽቱ ፡ ምግባራት ፡ ጸጸ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘንበአ ፡ ወውእቱ ፡ ከመ ፡ ኢን ሐሲ ፡ እምይእዜ ፡ ከመ ፡ አሕዛብ ፡ አለ ፡ ኢአ ምኑ ፡ ዓዲሆሙ ፡ ርኵሳን ፡ እሙንቱ ፡ ዘኢይደ ልዎሙ ፡ ለምእመናን ፡ ተራክበ ፡ ምስሌሆሙ ፡ ዘከመ ፡ እዘዘ ፡ ፍትሐ ፡ ብሊት ። ወነገልእኒ ፡ ከሠት ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ ነሲሒ ፡ ከመ ፡ ነሶሙ፡ እንስሳት ፡ ንጹሓን ፡ እሙንቱ ፡ ወኢንትከላእ ፡ እምተሴሰየ ፡ ዘይደሉ ፡ እምልዛዊ ፡ ጠባይዕ ፡ ወሲሳይኒ ፡ ከሙ ፡ ሀሎ ፡ ዘእንበለ ፡ በሊዐ ፡ ደም ፡ ወሕንቅ ፡ ወመሥዋዕተ ፡ ጣዖት ፡ ወብላዐ ፡ አርዌ ።

፳፪፮ ወብዉሕ ፡ ለነ ፡ ከመ ፡ ኢንትከላእ ፡ እምነ ፡

ስለ ፡ መብልና ፡ ልብስ ፡ ስለቤትም ።

አየ ፡ የሚል ፡ እነሆ ፡ በአራት ፡ ተጽኂልና ። (ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፳፭) ። በወንጌልም ፡ ወደሰው ፡ አፍ ፡ የሚገባ ፡ ሁሉ ፡ ሊያረክሰው ፡ የሚችል ፡ አይ ይለም ፡ ብሎ ፡ ጌታችን ፡ ተናግሮአል ። (ማቴ ፡ ፮ ፡ ፲፭) ። አፈ ፡ ወርቅም ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ እግዚ አብሔር ፡ በዚህ ፡ ቃል ፡ ከአራት ፡ ትእዛዝ ፡ ብዙ ዉን ፡ አሳለፈ ፡ ብሏል ።

፳፪፯ ይህንንም ፡ ቃል ፡ በግብረ ፡ ሐዋርያት ፡ የተነገ ረው ፡ ያጸናዋል ። ይኸውም ፡ ወንጌላዊ ፡ ሉቃስ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ የተናገረው ፡ ነው ። ስድስት ፡ ሰዓት ፡ ሲሆን ፡ ጴጥሮስ ፡ ሲጸልይ ፡ ከሰገነት ፡ ላይ ፡ ወጣ ። ያንጊዜ ፡ ተርቦ ፡ ሊበላ ፡ ሽቶ ፡ ነበር ። ምግቡንም ፡ እስኪያዘጋጁለት ፡ ድረስ ፡ እንቅልፍ ፡ መጣበት ። ሰማይ ፡ ተከፍቶ ፡ አየ ። በታላቅ ፡ ልብስ ፡ አምሳል ፡ በአራቱ ፡ ማዕዘን ፡ የተያዘ ፡ መጋረጃ ፡ ወደምድር ፡ ሲወርድ ፡ አየ ። በውስጡ ፡ አራት ፡ እግር ፡ ያለው ፡ እንስሳ ፡ በምድር ፡ የሚንቀሳቀስም ፡ ሁሉ ፡ የሰማይ ፡ ወፎችም ፡ አሉ ። ጴጥሮስ ፡ ሆይ ፡ ተነሥ ፡ እረ ድና ፡ ብላ ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ወደርሱ ፡ መጣ ። ጴጥሮስም ፡ ጌታዬ ፡ ሆይ ፡ አእ ፡ ንጹሕ ፡ ያል ሆነ ፡ የረከሰ ፡ ምንም ፡ ከቶ ፡ በልቼ ፡ አላውቅ ምና ፡ ልበላ ፡ አይገባኝም ፡ አለው ። ዳግመኛም፡ ጠርቶ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያንጻውን ፡ አንተ ፡ አታ ርክሰው ፡ አለው ። ይህም ፡ ቃል ፡ ምስት ፡ ጊዜ ፡ ሆነ ። (የሐዋ ፡ ፲ ፡ ፱ - ፲፮) ።

፳፪፰ ትዒሳን ፡ ሙምህራን ፡ አፈ ፡ ጠርቅ ፡ ሊሉትም አባቶች ፡ ከዚህ ፡ የተነሣ ፡ የሚያስፈልጉ ፡ ሁሉን ፡ ነገሮች ፡ እንዳሰብን ፡ ተረዱ ። ከእነር ሱም ፡ አንዱ ፡ ስመ፫ ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ነፃና ፡ ያላሰኑ ፡ አሕዛብ ፡ በእረት ፡ ሕግ ፡ እንደ፫ዝ ዘው ፡ ምእመናን ፡ ሊገናኙዋቸው ፡ የማይገባ ችው ፡ ርኩሳን ፡ እንደሆኑ ፡ ከነገረ ፡ ጅምር ፡ እን ዳናስብ ፡ ነው ። (ዘሊዋ ፡ ፲፩ ፡ ፩ - ፴ ። ኖኅ ፡ ፰ - ፯) ። ሁሉንም ፡ ግን ፡ ግልጽ ፡ ነው ። ይኸ ውም ፡ አእምሮ ፡ ጠባይዕ ፡ ያለን ፡ ከመሆናችን ፡ የተነግ ፡ እንስሳት ፡ ሁሉ ፡ ንጹሓን ፡ እንደሆኑ ፡ ሀውቃን ፡ የሚገባውን ፡ ከመመገብ ፡ እንዳንከ ለክል ፡ ነው ። ደምን ፡ ታንቆ ፡ የሞተውን ፡ ለጣ ዖት ፡ የተሠዋውን ፡ ከአሙሬ ፡ የተረፈውን ፡ ከመብላት ፡ በቀር ፡ ምግብነት ፡ እንርሱ ፡ አለ ችው ።

፳፪፱ አእምሮን ፡ ወደማጉደል ፡ ባሕሪይን ፡ ወደማና ወጽ ፡ አካልን ፡ ወደማጉደል ፡ የሚያደርስ

— ፱፱ —

አንቀጽ ፡ ፳፫ ።

ሁሉ ፡ ግብር ፡ ዘእንበሰ ፡ ዘአሕረም ፡ ፍትሐ ፡ ሕግ ፡ በእንተ ፡ ከሞናቱ ፡ ዘያበጽሕ ፡ ጎበ ፡ ሙስና ፡ ሕሊና ፡ ወእግስና ፡ ጠባይዕ ፡ ወሙስና ፡ ሥጋ ። ወገንት ፡ ይትከፈል ፡ ጎበ ፡ ፪ቱ ፡ ክፍል ። ፩ኛ ፡ እምኔሆሙ ፡ በእንተ ፡ ዘኢይሜኒ፡ ለሲባዩ ፡ ወኢለመድኒኒት ፡ አኮ ፡ እምነ ፡ እን ስላ ፡ ባሕቲተ ፡ አላ ፡ እምነ ፡ በቍላትኒ ፡ ካዕበ፡ ወገንት ፡ ዘከመ ፡ እንስሳት ፡ እለ ፡ በሙ ፡ ሕምዝ ፡ ወዘከመ ፡ አራዊት ፡ መሣጥያን ፡ እለ ፡ በሙ ፡ ፅፍራት ፡ ወመጦሪጽ ። ወእለ ፡ ይሴሰዩ ፡ ሕምዛተ ፡ ወበቍላተኒ ፡ ቀተልያነ ፡ እለ ፡ ያማስንዎ ፡ ለልብ ፡ ወለነሱ ፡ ሥጋ ፡ በበሲያቱ። ወላሰለ ፡ ዝንቱ ፡ ፍትሕ ፡ እመ ፡ ተረክበ ፡ እምነ ዝንቱ ፡ ከፍል ፡ ጸዳ ፡ ፫ታ ፡ ዘያማስን ፡ ጥዑየ ፡ ወይፈውስ ፡ ድዉየ ፡ ይትጉነሥ ፡ ጥዑይ ፡ እም በሲያቱ ፡ ወለድዉይሰ ፡ ብዙሕ ፡ ከመ ፡ ይብላዕ ፡ እመንገለ ፫ታ ፡ መድኀኒት ። ወጸግማዊኒ ከፍል ፡ ዘይናፍቅ ፡ በመብልዕ ፡ እው ፡ ዘያናፍቅ ቢጸ ፡ ለእመ ፡ በልዐ ፡ ኪያሁ ።

ስለ ፡ መብልና ፡ ልብስ ፡ ስለቤትም ።

ስለሆነ ፡ የሕግ ፡ መጽሐፍ ፡ ከክለከለው ፡ በቀር ፡ ከምግብ ፡ ሁሉ ፡ እንዳንከለከል ፡ መሆን ፡ ይገባናል ። (ዘሌዋ ፲፩ ፡ ፩ - ፵፯) ። ይህም ፡ ከሁለት ፡ ይከፈላል ። ከእነርሱም ፡ አንዱ ፡ ለምግብ ነትና ፡ ለመድኀኒት ፡ ስለማይጠቅም ፡ ነው ። መከልከላችንም ፡ ከእንስሳት ፡ ብቻ ፡ አይደለም እንዲሁም ፡ ከእጥክልትም ፡ ነው ፡ እንጂ ። ይኸ ውም ፡ መርዝ ፡ ያላቸውን ፡ እንስሳት ፡ የሚነጣ ጥቁ ፡ አራዊትን ፡ ጥፍርና ፡ መውጊያ ፡ ያላቸ ውንና ፡ መርዞችን ፡ የሚመገቡ ፡ አራዊትን ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰሉትን ፡ ከመብላት ፡ ከእትክ ልትም ፡ ወገን ፡ ቢበዛቸው ፡ አእምሮ ፡ የሚያ ጠፉትን ፡ አካል ፡ የሚያጎድሉትን ፡ ከመብላት ፡ እንድንከለከል ፡ ነው ። በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ (ፍርድ) አትብሉ ፡ ከተባለው ፡ ወገን ፡ እንዳ ፡ ምግብ ፡ ጤንኛ ፡ ቢበላው ፡ የሚጎዳ ፡ በሽተኛ ፡ ቢበላው ፡ የሚፈውስ ፡ ቢሆን ፡ ጤነኛው ፡ እርሱን ፡ ከመ ብላት ፡ ይከልክል ። በሽተኛው ፡ ግን ፡ የሚያድ ነው ፡ ከመሆኑ ፡ የተነሣ ፡ ሊበላ ፡ ይገባዋል ። ሁለተኛውም ፡ ከፍል ፡ እየተጠራጠረ ፡ የሚበ ላውን ፡ ወይም ፡ እርሱ ፡ በልቶ ፡ ሌላውን ፡ እን ዲጠራጠር ፡ የሚያደርገውን ፡ ሰው ፡ ነገር ፡ ያና ገራል ።

አንቀጽ ፡ ፳፬ ።

ለእነዚህ ፡ ለሁለቱ ፡ ከፍሎችም ፡ ሐዋርያው ፡ ጳውሎስ ፡ በሮም ፡ መልእክቱ ፡ በ፲፬ኛው ፡ ምዕ ራፍ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አመለከተ ። ሃይማኖተ ፡ ደካማ ፡ የሆነውን ፡ ሰው ፡ ቻሉት ። አጽናኑትም፡ በልባችሁም ፡ ተጠራጣሪዎች ፡ አትሁኑ ። ሁሉን ፡ ሊበሉት ፡ እንደሚገባ ፡ የሚያምን ፡ ሰው ፡ ሁሉን ፡ ይብላ ። የሚጠራጠር ፡ ግን ፡ እንደፈቃዱ ፡ ቅጠል ፡ ይብላ ። ሁሉን ፡ የሚበ ላው ፡ የማይበላውን ፡ አይንቀፈው ። የማይበላ ውም ፡ በሚበላው ፡ አይፍረድበት ። እግዚአብ ሔር ፡ በእርሱ ፡ ዘንድ ፡ አንዳለ ፡ እነሆ ፡ ታውቋ ልና ። እኔ ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ምንም ፡ ርኩስ ፡ ምግብ ፡ እንደሌለ ፡ እምናለሁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ርኩስ ፡ እንደሆነ ፡ የሚጠራጠር ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ገጹሉ ፡ ነውና ፡ ለእርሱ ፡ ብቻ ፡ ርኩስ ፡ ይሆንበታል ። ለሰው ፡ ክፉ ፡ የሚሆንበት ፡ ግን ፡ እየተጠራጠረ ፡ መብ ላቱ ፡ ነው ። እየተጠራጠሩ ፡ መብላት ፡ የሚ ኮን ፡ ከሆነስ ፡ ሥጋ ፡ አንብላ ፡ መይንም ፡ አን

ስለ ፡ መብልና ፡ ልብስ ፡ ስለቤትም ።

ጠጣ ። ወንድሞቻችን ፡ የሚጠራጠሩበትንም ፡ ሌላ ፡ ሥራ ፡ እናምጣ ። የሚጠራጠር ፡ ግን ፡ እየተጠራጠረ ፡ ቢበላ ፡ ይፈረድበታል ። ይህን ፡ አምኖ ፡ አላደረገውምና ። በሃይማኖት ፡ ያልተ ደረገ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአት ፡ ነው ። (ሮሜ ፲፬ ፡ ፩ - ፳፫) ።

አንቀጽ ፳፭

በሃይማኖት ፡ ጸንተን ፡ የምንኖር ፡ እኛም ፡ የተ ጠራማሪዎችን ፡ ደካማነት ፡ ልንታገሥ ፡ ይገባ ናል ። ዳግመኛም ፡ ለቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ በላ ከው ፡ በመጀመሪያው ፡ መልእክቱ ፡ በ፯ኛው ፡ ከፍል ፡ እንዲህ ፡ አለ ። እንሆ ፡ ሥራው ፡ ሁሉ ፡ ይገባኛል ። ነገር ፡ ግን ፡ ማንም ፡ በእኔ ፡ ላይ ፡ እንዲሰለጥንብኝ ፡ አላደርግም ። መብል ፡ ለሆድ ፡ ሆድም ፡ ለመብል ፡ ዝግጁ ፡ ነው ። (፩ኛ ፡ ቆሮ ፡ ፮ ፡ ፲፪) ። በዘጠንኛውም ፡ ከፍል ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ለማያታት ፡ የተሠዋውንም ፡ ስለመብላት ፡ ጣዖት ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ምንም ፡ እንዳያደለ ፡ እኛ ፡ እናውቃለን ። ከአንድ ፡ ከእግ ዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ በቀር ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ እን ደሌለ ፡ እናውቃለን ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ማወቅ ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡ የለችም ። መብል ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አያቀርበንም ። እኛ ፡ ስለበላን ፡ የሚጨመርልን ፡ ስላልበላንም፡ የሚጐድልብን ፡ የለምና ። ሥልጣናችሁ ፡ (ፍላ ጐታችሁ) ፡ ለተጠራጣሪዎች ፡ እንቅፋት ፡ እን ዳይሆን ፡ ዕወቁ ፡ ተጠንቅቁ ። እንደዚሁም ፡ መብል ፡ ወንድሜን ፡ የሚያስት ፡ ከሆነ ፡ ወን ድሜን ፡ እንዳላስት ፡ ሥጋ ፡ ለዘውትር ፡ አል በላም ። (፩ኛ ፡ ቆሮ ፡ ፰ ፡ ፩ - ፲፫) ። በ፰ኛውም፡ ከፍል ፡ እንዲህ ፡ አለ ። እነሆ ፡ ሥራው ፡ ሁሉ ፡ ይገባኛል ። ነገር ፡ ግን ፡ ሁሉ ፡ የሚጠቅመኝ ፡ አይደለም ። ሥራው ፡ ሁሉ ፡ ለእኔ ፡ የተገባ ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሥራው ፡ ሁሉ ፡ የሚዘጅ ፡ የሚጠቅም ፡ አይደለም ። በ፲በያ ፡ የሚሸጡትን፡ ሁሉ ፡ ብሉ ። ነገር ፡ ግን ፡ ስለዚህ ፡ ሰው ፡ ተጠራ ጣሪነት ፡ እትመራመሩ ። ምድር ፡ በመላዋ ፡ የእ ግዚአብሔር ፡ ናትና ። ካላመኑት ፡ ወገን ፡ የጠ ራችሁ ፡ እንድ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ልትሄዱም ፡ ብትወዱ ፡ ሳትመራመሩ ፡ ያቀረቡላችሁን ፡ ሁሉ ፡ ብሉ ። ይህ ፡ ለጣያት ፡ የተሠሞ ፡ ነው፡ ቢላችሁ ፡ ግን ፡ ስለነገራችሁ ፡ አትብሉ ። (፩ኛ ፡ ቆሮ ፡ ፲ ፡ ፳፫ - ፳፱) ። ለጢሞቴዎስም ፡ በጻፈው በ፭ኛው ፡ ከፍል ፡ እንዲህ ፡ ብሏል ። ለሚሞቱም ፡

አንቀጽ ፡ ፳፫ ።

እግዚአብሔር ፡ ሠናይ ፡ ሙእቱ ፡ ወአልቦ ፡ ሙስ ቱቱ ፡ ምንትኒ ፡ ምኑን ፡ ሰበ ፡ ተመክፍም ፡ በእ ኲቱት ፡ መኑስ ፡ ይትቋደስ ፡ በቃሰ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ወበጸሎት ።

፳፪፤ በስ ፡ ሃወጂቱ ፡ ወኢያርነፀስ ፡ ቀሲስ ፡ መኤጲስ ቆጶስ ፡ ምንተኒ ፡ እምነ ፡ መባልዕት ፡ ነስሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ጸእሙ ፡ ዘየሐርምዎ ፡ ባሕቲቶሙ ፡ በእንተ ፡ እግዚአብሔር ። ወይደልዎሙ ፡ ለመ ሣሒውያን ፡ ወለካህናት ፡ እስ ፡ እምሙስቡ ቶሙ ፡ ወፈድፋደሰ ፡ ለመነኮሳት ፡ ከመ ፡ ኢይ ጸመዱ ፡ ለዝንቱ ፡ ለብዝኀ ፡ ጸታ ፡ መባልዕት ፡ ዘዘዚአሁ ፡ መኢትፍግዕት ፡ በጣዕሙ ፡ ወዒ ናሁ ፡ ወልምላሚሁ ፡ መጎብሩ ፡ ዘይኤኒ ። አላ ፡ ይሴስዩ ፡ ለበቍዔት ፡ በዘይቀውም ፡ ሥጋ ፡ ጎዳጠ ፡ መዋዕለ ፡ ወዘተረክበ ፡ ለብዙሃን ፡ በመካናተ፡ሆሙ ፡ ወዘመናተ፡ሆሙ ። ወእግዚእ ነሂ ፡ ይቤ ፡ ምንትኑ ፡ ተደልዎ ፡ ወአስተሐ ምሞ ፡ በግብር ፡ ብዙኀ ፡ በዝንቱ ፡ ዓለም ። ወዘ ይትፈቀድሰ ፡ ኅቡዕ ፡ ጎዳጥ ፡ ሙእቱ ፡ መጽዬ ፡ ሙእቱ ። ወሐዋርያውኒ ፡ ተለም ፡ ወይቤ ፡ አዘ ለን ፡ እምነመ ፡ ረኩበን ፡ ሲሳየን ፡ ወዓራዘን ። ወእግዚእነሂ ፡ ካዕበ ፡ ይቤ ፡ ተዓቀቡ ፡ እምጽ ንብ ፡ ወስካር ፡ ወመሀበ ፡ ብዕዓን ፡ ለርኁባን ፡ ወለፅሙአን ፡ በእንተ ፡ ጽድቅ ፡ ወረሰየ ፡ እሜቶሙ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ።

፳፫፤፩ ወበእንተ ፡ አልባስኒ ፡ ናሁ ፡ ተንግረ ፡ በእንተ አሠሙ ፡ በበገጹ ፡ ዘይከውን ፡ እምእሠመ ፡ መከልኦ ፡ እምቀጠንት ፡ ዘያሠረግውዎሙ ፡ በጎ ብራት ፡ ዘገለፉ ፡ ቦሙ ፡ ወከመ ፡ ይኩን ፡ ለመ ልእክተ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ልብስ ፡ በዓዓ ፡ ድልው ። ወከመሂ ፡ ኢይልበሳ ፡ አንስት ፡ አል ባሰ ፡ እያው ፡ ወእደውኒ ፡ አልባሰ ፡ አንስት ፡ ወኢያደዩ ፡ እደው ፡ ሕልቀታተ ፡ ውስተ ፡ እፃ ብዓሆሙ ፡ ወኢአንስት ፡ ከመ ፡ ኢይልበሳ ፡ መርቀ ፡ ዘተገብረ ፡ በልብስ ፡ ዘያስተጌክሕ ።

ስለ ፡ ሥብልና ፡ ልብስ ፡ ስለቤትም ።

ኑና ፡ ጽድቅን ፡ ለሚያሠቁ ፡ ሰምች ፡ ለጥቅ ምና ፡ ለምስጋና ፡ እግዚአብሔር ፡ የፈጠራቸ ውን ፡ ምግባች ፡ እየተመ ፡ ነቃ ፡ ነገርን ፡ ይናገ ራሉ ። እግዚአብሔር ፡ የፈጠረው ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ በምስጋና ፡ ከተመገቡት ፡ ርስሰት ፡ የሌ ለበት ፡ ንጹሕ ፡ ነውና ። ሁሉም ፡ በእግዚአብ ሔር ፡ ቃልና ፡ በጸሎት ፡ ይቀደሳል ። (፩ኛ ፡ ጢሞ ፡ ፬ ፡ ፫-፭)።

፳፫፤ በስ ፡ ሃይ ፡ እነርሱ ፡ ብቻ ፡ ስለእግዚአብሔር ፡ ብለው ፡ ከሚከለክሉት ፡ በቀር ፡ ቁሱ ፡ ኢጲስቆ ጶስ ፡ ከመባልዕት ፡ ወገን ፡ ሁሉ ፡ ማንኛውንም ፡ መብል ፡ ርኩስ ፡ ነው ፡ ኢይበል ። ከእነርሱ ፡ ወገን ፡ ለሚሆኑ ፡ ለምእመናንና ፡ ለካህናቱ ፡ ይልቁንም ፡ ለመነኰሳት ፡ ዓይነቱ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሰሚሆን ፡ ብዙ ፡ ምግብ ፡ ተገገሮች ፡ እንዳሉሆኑ ፡ ይገባቸዋል ። በጣዕሙ ፡ በመዓዛዉ ፡ በአለ ላለት ፡ በሚያስት ፡ መልኩ ፡ እንዳይደሰቱ ፡ መሆን ፡ ይገባቸዋል ። ሥጋ ፡ ለጥቂት ፡ ወራት ፡ ይቆም ፡ ዘንድ ፡ ለሚቢቅ ፡ ያህል ፡ ይመገቡ ፡ እንጂ ። ለብዙዎች ፡ ሰዎች ፡ በዘመናቸውና ፡ በዕ ታቸው ፡ የተገኘውን ፡ ይመገቡ ፡ እንጂ ። ጌታ ችንም ፡ እንዲህ ፡ ብሏል ። በዚህ ፡ ዓለም ፡ ለብዙ ሥራ ፡ መዘጋጀትና ፡ መጨነቅ ፡ ምንድን ፡ ነው ? ለእርሱስ ፡ የሚያሻው ፡ ጥቂት ፡ ነው ። ያውም ፡ እንደ ፡ ነው ፡ አለ ። (ማቴ ፡ ፮፤ ፳፭ ። ሉቃ ፡ ፲ ፡ ፵፩-፵፪) ። ሐዋርያውም ፡ ምግባችን ንና ፡ ልብሳችንን ፡ ካገኘን ፡ ይበቃናል ፡ በማ ለቱ ፡ መሰለው ። (፩ኛ ፡ ጢሞ ፡ ፮ ፡ ፰) ። ዳግመ ኛም ፡ ጌታችን ፡ ከስካርና ፡ ከጥጋብ ፡ ተጠበቁ ፡ አለ ። (ሉቃ ፡ ፮ ፡ ፳፭ ። ማቴ ፡ ፳ ፡ ፵፪ -፵) ። ስለጽድቅ ፡ ብለው ፡ ለሚራቡና ፡ ለሚጠሙ ፡ ብፅ ዕናን ፡ ሰጠ ። ዋጋቸውንም ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያ ትን ፡ አደረገ ። (ማቴ ፡ ፭ ፡ ፮ ። ሉቃ ፡ ፮ ፡ ፳፩) ።

፳፫፤፩ ስለልብሶችም ፡ ብያይነት ፡ እነሆ ፡ ተንገረ ። በቀለም ፡ ያስጌጧቸውን ፡ ልብሶች ፡ ከመል ልበስ ፡ ከለከለ ። ለቤተ ፡ መቅደስ ፡ ማገልገያ ፡ ነሮ ፡ ልብስ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ያጣባል ። ሴቶች ፡ የወንዶችን ፡ ልብስ ፡ ወንዶችም ፡ የሴቶችን ፡ ልብስ ፡ እንዳይለብሱ ፡ ወንዶች ፡ በማቶቻቸው ፡ የምንዝር ፡ ጌጥ ፡ ቀለበት ፡ እንዳያደርጉ ፡ ሴቶ ችም ፡ ከወርቅ ፡ የተሠራ ፡ የሚያስመካ ፡ መርቀ ፡ ዘቦ ፡ ማምጃ ፡ እንዳይለብሱ ፡ ከለከለ ።

ከፍትሐ ነገሥት የተወሰደ

አንቀጽ ፡ ፴ወ፭ቱ ፡

በእንተ ፡ ዘይደሉ ፡ ተናግሮቱ ፡ በዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ እምብሉይ ፡ ወሐዲስ ፡ ካልእ ፡ እምዘተነግረ ፡ ውስተ ፡ አንቀጽ ፡ በበገጹ ።

ፈቐደ፩ኛ መሰብ ፡ ኮነ ፡ ብእሲ ፡ ፍሑረ ፡ በነፍስ ፡ ወሥጋ ፡ ደለወ ፡ ከመ ፡ ይሥርዮ ፡ ለሞተ ፡ ጌተ ፡ ሕገንተ ። ተጸግዎ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ለእፈጽሞተ ፡ ምግባራቲሁ ፡ እሰ ፡ በክሡት ፡ እንተ ፡ ሀለወት ፡ በእባላቲሁ ፡ ዘእፍኣ ። ወካልኢ ፡ ሕግ ፡ ለእፈጽሞተ ፡ ምግባራቲሁ ፡ ዘውስተ ፡ እንተ ፡ ሀለዎ ፡ በሕሊናሁ ፡ ወጎይጎቲሁ ፡ ወርክ በታዕቲሁ ፡ ዘውስተ ።

ፈቐደ፪ኛ ወተጸግዎ ፡ ሕግ ፡ ይተውም ፡ በሥርዓተ ፡ ሕግ ፡ ተጸግዎ ፡ ዘውእቱ ፡ ሕገ ፡ ርትዕ ፡ ይትዐወቅ ፡ አረት ፡ ወተሠርየ ፡ በውስቱ ፡ ነጎኔያት ፡ ሥጋውያት ፡ ዘያስተርእዩ ፡ በእንተ ፡ ምግባራት ፡ ሥጋውያት ፡ ዘበሙ ፡ ይደሉ ፡ ናስትሕ ፡ በነገ ፡ ፈታሕት ፡ ዘከመ ፡ ተቀሰ ፡ ተታሲ ፡ ወተ ፈድዮ ፡ ዕዳ ፡ እምነ ፡ ሰራቂ ፡ ወዘቢጠ ፡ ዐማኒ ፡ ወዘተነግረ ፡ በእንተአሁ ፡ ካልእ ፡ እምዝንቱ ። ወነሰሉ ፡ ዘተነግረ ፡ በውስቱ ፡ ከመ ፡ ያብጽሕ ኀበ ፡ ዝንቱ ፡ ወከመ ፡ ይፀመዱ ፡ ቦቱ ፡ በምግባር ፡ ሥነፈሳዊ ፡ ከመ ፡ ሙሴ ፡ መኤልያስ ፡ ትሩፋን ፡ ምግባር ።

ፈቐደ፫ኛ መዳግማዊሰ ፡ መንፈሳዊ ፡ ውእቱ ፡ ተዋም ፡ በሕግ ፡ ይኄሬዎ ፡ ወውእቱ ፡ ሕገ ፡ ፍጹሚ ፡ ወተሠርዐ ፡ በውስቱ ፡ ሕግ ፡ ልዘናሚ ፡ ወተዐርዐ ፡ በውስቱ ፡ ሕግ ፡ ልዘናዊ ፡ በእንተ ፡ ምግባራት ፡ ዘውስተ ፡ በይነ፫ሥጽ ፡ ዑቡ ፡ ነፍሰ ፡ ሰብእ ፡ በውስተ ፡ ነፍሰ ፡ ማእከሌሁ ፡ መማእከለ ፡ ፈጣሪው ፡ በሥምረተ ፡ ርእሱ ፡ ዘከመ ፡ ተከልአ ፡ እመዓት ፡ ወእምነጽር ፡ በፍትወት ፡ መእፍትሮተ ፡ ወር ፡ መሠርጾ ፡ ለዘእበሰ ፡ ወተወ

አንቀጽ ፡ ፴፭ ።

በእንቀጽ ፡ ውስተ ፡ በየወገኑ ፡ ከተነገረው ፡ ሌላ ከብሉይና ፡ ከሐዲስ ፡ መጥቶ ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ሊናገሩት ፡ ስለሚገባው ፡ ይናገራል ።

ፈቐደ፩ኛ ሰው ፡ ከነፍስና ፡ ከሥጋ ፡ የተፈጠረ ፡ እንደ ፡ መሆኑ ፡ ሁለት ፡ ሕጎች ፡ ሊሠሩለት ፡ ተገባ ። መጀመሪያው ፡ በሕዋሳቱ ፡ እፍኣ ፡ ያለች ፡ በግልጽ ፡ የሚሠሩ ፡ ሥራዎችን ፡ ለማስፈጸም ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ሁለተኛውም ፡ ሕግ ፡ በሐሳቡና ፡ በጎይሉ ፡ በውስጥም ፡ በሚያገኙት፡ ነገሮች ፡ ያሉትን ፡ የውስጥ ፡ ሥራዎችን ፡ ለማስፈጸም ፡ ነው ።

ፈቐደ፪ኛ መጀመሪያው ፡ ሕግ ፡ በመጀመሪያው ፡ ሕግ፡ ሥርዓት ፡ ይጸናል ። ይኸውም ፡ የቀና ፡ ሕግ ፡ ነው ። አረት ፡ እንደሆነች ፡ ይታወቃል ። ስለ ፡ ሥጋውያት ፡ ሥራዎች ፡ የሚገልጹ ፡ ሥጋውያት ፡ ትጣቶችም ፡ በውስጡ ፡ ተሠሩ ። በዳኞች ፡ ዘንድ ፡ ፍርድ ፡ የሚገባቸው ። ይኸውም ፡ ነፍሰ ገዳይን ፡ እንደመግደል ፡ ከሌባም ፡ ገንዘብን ፡ እንደመከፈል ፡ ዓመፀኛንም ፡ እንደመግረፍ ፡ ያለ ፡ ነው ። ከዚህም ፡ ሌላ ፡ ስለእርሱ ፡ የተነገረው ፡ ነው ። በውስጡ ፡ የተነገረው ፡ ሁሉ ፡ ወደዚህ ፡ ያደርስ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። በሥራ ፡ ፍጹማን ፡ እንደሆኑ ፡ እንደ ፡ ሙሴና ፡ እንደ ፡ ኤልያስ ፡ በመንፈሳዊ ፡ ሥራም ፡ ዕሙዳን ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ፈቐደ፫ኛ ሁለተኛው ፡ ግን ፡ መንፈሳዊ ፡ ነው ። በኋለኛው ፡ ሕግ ፡ መጽናት ፡ ነው ። እርሱም ፡ የመጨረሻ ፡ ሕግ ፡ ነው ። ሰው ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ በእርሱና ፡ በፈጣሪው ፡ መካከል ፡ ራሱን ፡ በራሱ ፡ ስለሚያሥጥባቸው ፡ ውስጣውያን ፡ ሥራዎች ፡ ልዑናዊ ፡ ሕግ ፡ በውስጡ ፡ ተጽፏል ። ይኸውም ፡ ከቅጣና ፡ በፍትወት ፡ ከማየት ፡ እንደመከልከል ፡ ጠላትን ፡ እንደመው

— ፪፻፹፯ —

አንቀጽ ፡ ፴፭ ።

ስለ ፡ ብሉይና ፡ ሐዲስ ።

ትቦ ፡ እምጽጋብ ፡ ወስካር ፡ መእትሕቶ ፡ ርእስ ፡ ለነሶሱ ፡ ሰብእ ፡ ወዛቲ ፡ ይእቲ ፡ እምኮነኔያት ፡ እንተ ፡ ባቲ ፡ ይፈትሕ ፡ ሰብእ ፡ ላዕለ ፡ ነፍሱ ፡ በሥምረተ ፡ ልቡ ፡ ዘያፈትዶ ፡ ይኩን ፡ ብእሲ ፡ ፍጹመ ፡ መኢኮነት ፡ ይእቲ ፡ እምኮነኔያት ፡ እንተ ፡ ይፈትሑ ፡ ባቲ ፡ መኳንንት ፡ ላዕለ ፡ ሰብእ ፡ በግብር ።

ደድ ፡ የበደልን ፡ ይቅር ፡ እንደማለት ፡ ከጥጋብና ፡ ከስካር ፡ እንደመጠበቅ ፡ ራስንም ፡ ለሰውሁሉ ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ እንደማድረግ ፡ ያለ ፡ ነው ። ይችውም ፡ ከትጣቶች ፡ ወገን ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ሊሆን ፡ የወደደ ፡ ሰው ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ በሰውነቱ ፡ ላይ ፡ ሰው ፡ የሚፈርድባት ፡ ናት ። መኳንንት ፡ በግድ ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ከሚፈረጁ፡ትው ፡ ትጣቶች ፡ ወገን ፡ አይደሉችም ።

ፈቐደ፫ኛ መኢተሠርየ ፡ በደኑሪዊ ፡ ሕግ ፡ አብጥሎቱ ፡ ለዘተነግረ ፡ በሕግ ፡ ቀዳማዊ ፡ እስመ ፡ ይቤ ፡ እግዚእን ፡ "ኢመጻእኩ ፡ ከመ ፡ እሥዐር ፡ ለሕግ ፡ አላ ፡ ከመ ፡ እፈጽሞ ።" ወይእዜኒ ፡ እን ከሰ ፡ ኢተሐገገ ፡ እስርዖት ፡ ፍትሐሙ ፡ ለፈታሕት ። ወበእንተዝ ፡ ተጽሕፈ ፡ ውስተ ፡ ዓሥር ፡ ምዕራፍ ፡ ዘድስት ፡ ፍሑን ፡ ሥረዩ ፡ ኃጣውሊ ፡ አኃዊክሙ ፡ እኮ ፡ ዘንብል ፡ ዘንተ ፡ ለፈታሕት ። ወስምዐ ፡ ኮነ ፡ በውስተ ፡ ዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ ወካልኡኒ ፡ ላዕለ ፡ ብዙኀ ፡ እምፍት ሐታት ፡ በዘነበረ ፡ እምሄ ፡ ውስተ ፡ አረት ፡ ወለእመ ፡ ተደርሰ ፡ ደለወ ፡ ከመ ፡ ይንበር ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ በስሉ ፡ ዘንበረ ፡ ውስተ ፡ ዘቀዳሚ ፡ ሕግ ፡ እምኀበር ፡ ለፈታሕት ፡ በእንተ ፡ ፈቂሕ ፡ ዘቦቱ ፡ ይፈትሑ ፡ ላዕለ ፡ ሰብእ ፡ በእንተ ፡ ምግባራት ፡ ግሁዳት ። ወበዝኡ ፡ ዘተነግረ ፡ በሕግ ፡ ደኃራዊ ፡ እምነ ፡ ገሥጾት ፡ ብእሲ ፡ በሕሊናሁ ፡ በዝኡ ፡ ከብር ፡ ሀሎ ፡ በእንቀጸ ፡ ዚአሁ ።

ፈቐደ፬ኛ ወናሁ ፡ ተነግረ ፡ በዝንቱ ፡ አንቀጽ ፡ እምነ ፡ ውእቱ ፡ ቃላት ፡ ፍሉጣት ፡ ካልእ ፡ እምዘ ፡ ተነግረ ፡ በእናትዮ ። ለቀዳማዊሰ ፡ እምቅድመ ፡ ተናግሮቱ ፡ ንበል ፡ ከመ ፡ ሕግ ፡ ቀዳማዊ ፡ ሰበ መጽአ ፡ ሕግ ፡ ደኃራዊ ፡ ኢጸገበ ፡ ሕግ ፡ ቀዳማዊ ፡ በዝሰንታሁ ፡ ወኢበጠሰ ፡ ዝሰንታሁ ፡ አላ ፡ ኀበ ፡ ፈቂ ፡ ከፍል ፡ ተከፍለ ። ጸዳሰ ፡ ከፍል ፡ ተርፈ ፡ ኀበ ፡ ሀላዊው ፡ እስመ ፡ በዝሉ ፡ ጊዜ ፡ ዙኀኔ ፡ ፍትሑ ፡ ሀልው ፡ ዘኢይትማሰል ፡ ምስለ ፡ ካልኣኒሁ ፡ እምግባራተ ፡ ትሩፋት ፡ ዘውእቱ ፡ እምልኮ ፡ ፈጣሪ ፡ ዘእንበለ ፡ ፍጡራን ፡ ወተከልአ ፡ እምተቲል ፡ ወዝሙት ። ወጸዳኢ ፡ ከፍል ፡ ተፀርዐ ፡ በምልኡ ፡ እስመ ፡ ኀብረ ፡ ቀዊም ፡ ቦቱ ፡ ተፀርዐ ፡ በምልኡ ፡ ወዘይትፈቀድ ፡ እምኔሁ ፡ ከነ ፡ ዘከመ ፡ ሕርመተ ፡ ሐረውያ ፡ እስመ ፡ መፍቅድ ፡ እምኔሁ ፡ ውስተ

ስለ ፡ ብሉይና ፡ ሐዲስ ።

ደድ ፡ የበደልን ፡ ይቅር ፡ እንደማለት ፡ ከጥጋብና ፡ ከስካር ፡ እንደመጠበቅ ፡ ራስንም ፡ ለሰውሁሉ ፡ ዝቅ ፡ ዝቅ ፡ እንደማድረግ ፡ ያለ ፡ ነው ። ይችውም ፡ ከትጣቶች ፡ ወገን ፡ ፍጹም ፡ ሰው ፡ ሊሆን ፡ የወደደ ፡ ሰው ፡ በራሱ ፡ ፈቃድ ፡ በሰውነቱ ፡ ላይ ፡ ሰው ፡ የሚፈርድባት ፡ ናት ። መኳንንት ፡ በግድ ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ከሚፈረጁ፡ትው ፡ ትጣቶች ፡ ወገን ፡ አይደሉችም ።

ፈቐደ፫ኛ በፊተኛው ፡ ሕግ ፡ የተነገረውን ፡ ግፍረስ ፡ በኃለኛው ፡ ሕግ ፡ አልተጸፈም ። ጌታችን ፡ ሕግን ፡ ልፈጽመው ፡ እንጂ ፡ ልሽረው ፡ አል መጣሁም ፡ ብሏልና ። (ማቴ ፡ ፭ ፡ ፲፯) ። እን ግዲያውስ ፡ ባሪም ፡ የጻዮንን ፡ ፍርድ ፡ መሻር ፡ አልታዘዘም ። ስለዚህ ፡ በድስት ፡ በ፲ኛው ፡ ምዕራፍ ፡ ተጽፏል ። የመንድሞቻችሁን ፡ በይል ፡ ፈጥናችሁ ፡ ይቅር ፡ በሉ ። ይህንም ፡ ለጻዮች ፡ የምንናገር ፡ አይደለንም ። በዚህም ፡ ውስጥ ፡ መጽሐፍ ፡ ምስክር ፡ ሆነ ። ሌላውም ፡ ከርሰቀ ፡ ወጥቶ ፡ በአሪት ፡ በተጻፈው ፡ ከፍርድ ፡ ወገን ፡ በብዙ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ተገለጸ ፡ ሥራዎችም ፡ ጻዮች ፡ ከሥራ ፡ ወገን ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ ስለሚፈርዱበት ፡ ፍርድ ፡ በቀደመው ፡ ሕግ ፡ በተጸፈው ፡ ሁሉ ፡ ድርሰት ፡ ቢደረስ ፡ ከዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ጋራ ፡ ሊቀመጥ ፡ ተገባ ። በሥራው ፡ ሁሉ ፡ በሐሳቡ ፡ ሰውን ፡ ከመገሠጽ ፡ የተነሣ ፡ በኋለኛው ፡ ሕግ ፡ የተጸፈው ፡ ሁሉ ፡ በእርሱው ፡ አንቀጽ ፡ አለ ።

ፈቐደ፬ኛ በየአንቀጹ ፡ ከተነገረው ፡ ሌላ ፡ ልዩ ፡ ከሆኑ ፡ ቃላት ፡ መጥቶ ፡ እነሆ ፡ በዚህ ፡ አንቀጽ ፡ ተነገረ ። የመጀመሪያውን ፡ ሕግ ፡ ከመናገሩ ፡ አስቀድሞ ፡ እንደ ፡ መጀመሪያው ፡ ሕግ ፡ ኋለኛው ፡ ሕግ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ የፊተኛው ፡ ሕግ ፡ በፄ ፡ ከፍል ፡ ተከፈለ ፡ እንጂ ፡ መላውም ፡ አልተሻረም ። መላውም ፡ አልጸናም ፡ እንበል ። እንደ ኛው ፡ ከፍል ፡ በለበት ፡ ጸና ። ከትሩፋት ፡ ሥራዎች ፡ ወገን ፡ ከሌሎች ፡ ጋራ ፡ የማይመሳሰል ፡ የኅብረ ፡ ቅባት ፡ ውልጊዜ ፡ ይሥራልና ። ይኸውም ፡ ከፍጡራን ፡ ለይቶ ፡ ፈጣሪን ፡ ማምለክ፡ ከመሠየሉና ፡ ከመሰሰንም ፡ መከልከል ፡ ነው ። ይኸውም ፡ ከከፍል ፡ በሙሉ ፡ ተሻረ ። በእርሱ ፡ ጸንቶ ፡ መኖር ፡ በሙሉ ፡ ተሻጽልና ። ከእርሱ ፡ የሚሻውም ፡ ከዕሪያ ፡ እንደመከልከል ፡ ያለ ፡ ነበር ። በተደመው ፡ ሕግ ፡ ከእርሱ ፡ የሚሻው ፡

— ፲፱፱፯ —

አንቀጽ ፡ ፭፩ ።

ስለ ፡ ብሉይና ፡ ሐዲስ ።

ሕግ ፡ ቀዳሚ ፡ ኮነ ፡ ከመ ፡ ኢይደመሩ ፡ ሕዝበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስለ ፡ አሕዛብ ፡ እሉ ፡ ኢያመልክዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘበጎበሮሙ ፡ ሀሎ ፡ ብዙኃ ፡ አሕርው ፡ ከመ ፡ ኢይትመየጡ ፡ ኀበ ፡ አምልኮቶሙ ፡ ወልማዳቲሆሙ ፡ እኪት ።

፭፲፭፻፷፭ ወሶበ ፡ ሰደኑ ፡ እሊን ፡ ላዕለ ፡ ዝሉ ፡ አሕዛብ ፡ ወኢተርፉ ፡ ዘእንበለ ፡ ጎዳጣን ፡ ዐላውያን ፡ በፈቃድ ፡ አምላክዊ ፡ ደሰወ ፡ ፈቂድ ፡ ኀበ ፡ ተጋብኦቶሙ ፡ ለመሃይምናን ፡ ወደለወ ፡ አፅርአቶ ፡ ለዘይከልእ ፡ ወሰዘይክልእሎሂ ። ወፎጹ ፡ ከፍል ፡ ኮነ ፡ ፍጹመ ፡ በተመስኮ ፡ ላዕሌሁ ፡ ዘከመ ፡ ኀቢረ ፡ ሠናይ ፡ ለፍቁር ፡ ወለጸላእት ፡ ካዕበ ፡ ወሕጹጽሰ ፡ ዘኮነ ፡ ሕጹጸ ፡ እምፍጻሜ ፡ ኮነ ፡ ፍጹመ ፡ ዘከመ ፡ ኀቢረ ፡ ሠናይ ፡ በዕሰተ ፡ ሰንበታት ፡ ዘተእዘዘ ፡ ቀዳሚ ፡ ጎዲን ፡ ዙሉ ፡ ግብር ፡ ውስቴቶን ። ወፎጹ ፡ ክፍል ፡ ኮነ ፡ ሥጋዌ ፡ ወፈለሰ ፡ ኀበ ፡ ግብር ፡ መንፈሳዊ ፡ ወኮነ ፡ ሀየንተ ፡ እንጽሐ ፡ ሥጋ ፡ በማያት ፡ ወደ ማት ፡ አንጽሐ ፡ ነፍስ ፡ በንስሓ ፡ ወሥርዓታቲሃ ። ወሀየንተ ፡ ተስፋ ፡ መንግሥተ ፡ ምድር ፡ ወሠናያቲሃ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ወዘለዓለም ፡ ተድላሃ ።

፭፲፭፻፷፱ ወይእዜኒ ፡ ኢያትፈቀዳ ፡ በዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ ዙሉን ፡ ትእዛዛት ፡ እለ ፡ ቀደማ ። ወዘይትፈቀድሰ ፡ እምብሔረ ፡ አሪት ፡ ዳግማዊ ፡ ዘይቤ ፡ ቃሉ ፡ ለልዑል ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ እነ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክከ ፡ ኢትግበር ፡ ለከ ፡ አምላከ ፡ ዘእንበሌየ ። ወኢትግበር ፡ ለከ ፡ ግልፈኖቲ ፡ ወኢአምሳላተ ፡ ዘውስተ ፡ ሰማይ ፡ ዘላዕሉ ፡ ወኢዘውስተ ፡ ምድር ፡ ዘታሕቱ ፡ ወኢትስግድ ፡ ሎሙ ፡ ወኢታምልኮሙ ። እስመ ፡ እነ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክከ ። "ኢትዮሐል በስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጣሪከ ፡ በሐሰት ፡ እስመ ፡ ኢያንጽሖ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዘይዮሐል ፡ ስሞ ፡ በሐሰት ። "ወአክብር ፡ አባከ ፡ ወእመከ ፡ ከመ ፡ ትርከብ ፡ ሠናየ ፡ ወይኑኅ ፡ መዋዕሊከ ። "ኢትትቅል ፡ ወኢትዘሙ ፡ ኢትስርቅ ፡ ወኢትኩን ፡ ስምዐ ፡ በሐሰት ፡ ላዕለ ፡ ቢጽከ ። ወኢትፍቱ ፡ ቤተ ፡ ካልእከ ፡ ኢ ፡ ብእሲቶ ፡ ወኢገብሮ ፡ ወኢ ፡ አመቶ ፡ ወኢ ፡ እንስሳሁ ፡ ወኢ ፡ ዙሉ ፡ ዘአጥረቦ ፡ ቢጽከ ።

ስለ ፡ ብሉይና ፡ ሐዲስ ።

የእግዚአብሔር ፡ ወገኖች ፡ እግዚአብሔርን ፡ ከማያመልኩት ፡ በእነርሱ ፡ ዘንድ ፡ ብዙ ፡ ዕረያ ፡ ካላቸው ፡ ከአሕዛብ ፡ ጋራ ፡ እንዳይገናኙ ፡ ነበርና ። ወደአምልኮታቸውና ፡ ወደክፉ ፡ ልማዳቸው ፡ እንዳይመለሱ ።

